ተ

ተ ፤ ፳፱ኛ ፣ ፊደል ፣ በግእዝ ፣ አልፍ ፣ ቤት ፣ በአበገደ ። በፊደልነት ፣ ስሙ ፣ ታው ፤ አኃዝ ፣ ሲኾን ፣ ተ—፬፻ ፣ ይባላል ።

ተ ፤ የከና ፣ የጠ ፣ ተወራራሽ ። እስኪ ፣ እስቲ ፤ እስክ ፣ እስት ፤ ከየት ፣ ተየት ፤ ወጠረ ፣ ወተረ ፤ ቀበጠጠ ፣ ቀበተተ ።

ተ ፤ የመደረግና ፣ የመደራረግ ፣ ልማድ ። ጣፈ ፣ ተጣፈ ፣ ተጣጣፈ ፤ ላከ ፣ ተላከ ፣ ተላላከ ። በአዐ ፣ በሚነሣ ፣ ግስ ፣ በመደረግ ፣ ብቻ ፣ ራብዕ ፣ ይኾናል ። አመነ ፣ ታመነ ፤ ዐወቀ ፣ ታወቀ ።

ቱ ፤ እንስትን ፣ ከተባት ፣ ለመለየት ፣ የሚ ነገር ፣ ዝርዝር ። ፈረስ ፣ ፈረሲቱ ፤ በግ ፣ በጊቱ ፤ ፍየል ፣ ፍየሊቱ ። በራብዕና ፣ በኃምስ ፣ በሳብዕ ፣ በሚጠርስ ፣ ስም ፣ ግን ፣ ዪቱ ፣ ይላል ። ቷን ፣ ዋን ፣ ተመልከት ።

ቲ ፤ ምእላድ ። ወጕል ፣ ወጕለቲ ፤ ፉን ፣ ፉነቲ ።

ታ ፤ በራብዕ ፣ በሚጠርስ ፣ የጇና ፣ የ፫ ፤ ፌ ደል ፣ ግስ ፣ ለሩቅ ፣ ሴት ፣ የቦዝ ፣ ዝርዝር ። በላ ፣ በልታ ፤ ቀና ፣ ቀንታ ፤ ሠራ ፣ ሠርታ ፤ ዘነጋ ፣ ዘነ ግታ ፤ ዘረጋ ፣ ዘርግታ ። መጠረሻው ፣ ራብዕ ፣ ባል ኾነ ፣ ግስ ፣ ሲገባ ፤ ሰጠ ፣ ሰጥታ ፤ ቀረ ፣ ቀርታ ፣ ይላል ።

ታ ፤ ምእላድ ። ፍችው ፣ ግለት ። እግዚአ ፣ እግዚአታ ፤ ሃሌ ፣ ሃሌታ ፤ አወን ፣ አወንታ ፤ አል ፣ አሉታ ፤ ይሉኝ ፣ ይሉኝታ ።

ታ ፤ በግልስ ፣ ቅጽል ፣ መጨረሻ ፣ እየገባ ፣ እንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ለሴት ፣ መለዮ ፣ ቅጽል ፣ በቂ ፣ ይኾናል ። የፈሲታ ፣ ተቈጠታ ፤ ጠፍር ፣ በሲታ ፣ ብትኼድ ፣ ልጓም ፣ በሲታ ፣ መጣች ። ሣቂታ ፣ ሰፊታ ፣ እንዲሉ ። የሳቢ ፣ ዘርም ፣ ምእላድ ፣ ሲኾን ፤ ረሳ ፣ ርሳታ ፤ ረዳ ፣ ርዳታ ፤ ዘነጋ ፣ ዝንጋታ ፤ ቸለለ ፣ ቸልታ ፤ ቀረ ፣ ቅርታ ፤ ዋለ ፣ ውለታ ፤ ቀደደ ፣ ቅዴታ ፤ ሰማ ፣ ስሞታ ፣ እያለ ፣ ይነገራል ።

ታ ፤ (ትማ ፣ ሐባ) ፤ የሩቅ ፣ ሴት ፣ ነባር ፣ እንቀጽ ፤ ናት ፣ ነች ። ተአምራትስ ፣ ይህታ ፤ ሰን በትን ፣ መሻር ፣ ይህታ ፣ እንዲሉ ፣ የሐዲስ ፣ ተር ጓሞች ። ዳግመኛም ፣ ይህች ፣ ናት ፣ ተብሎ ፣ ይተ ረጐማል ።

ቷ ፤ የሩቅ ፣ ሴት ፣ ዝርዝር ። ላሚቷ ፣ በጊቷ ።

ቷ ፡ አለ ፤—ተበጠሰ ፤—(ቷቷ) ።

ቼ ፤ ምእላድ ። ምናምን ፡ ምናምንቼ ።

ት ፤ ለቅርብ ፣ ወንድ ፣ ለቅርብ ፣ ሴትና ፣ ለሩቅ ፣ ሴት ፣ ለቅርቦች ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ የጎ ላፊ ፣ ትንቢት ፣ መነሻ ፣ ይኾናል ። (ማሰረጃ) ፣ ትጥ ፋለኽ ፣ ትጥፊያለሽ ፣ ትጥፋለች ፣ ትጥፋላችኹ ፤ በትእዛዝም ፣ ለሩቂቱ ፣ ሴት ፣ ብቻ ፣ ትጣፍ ፣ እያለ ፣ ይገባል ። በአዐ ፣ በሚነሣ ፣ ግስ ፣ ግን ፣ ኹሉም ፣ ራብዕ ፣ (ታ) ፣ ይኾናል ። በርስዎታም ፣ ለቅርብ ፣ ሴት ፣ የአንቀጽ ፣ ዝርዝር ፣ ሲኾን ፤ እንኳዕ ፣ ከዘ መን ፣ እዘመን ፣ አደረሰዎት ፣ ይላል ።

ት ፤ በራብዕ ፣ ለሚጠርስ ፣ ግስ ፣ የዘር ፣ ምእላድ ። ገባ ፣ መግባት ፤ ዘጋ ፣ መዝጋት ፤ ዘረጋ ፣ መዘርጋት ፤ ቀባ ፣ መቀባት ፤ ዘራ ፣ መዝራት ። አን ዳንዴም ፣ በግእዝ ፣ በሚጠርስ ፣ ግስ ፣ ምእላድ ፣ ሲኾን ፤ አየ ፣ ማየት ፤ ደረጀ ፣ መደርጀት ፤ ሰጠ ፣ መስጠት ፣ ይላል ።

ት ፤ ጥራነት ፣ ባለው ፣ ስም ፣ ማፍ ፣ እየ ተጨመረ ፣ ለሴት ፣ ዝርዝር ፣ ይኾናል ። ማሞ ፣ ማሚት ፤ ልጅ ፣ ልጅት ፤ ወንድ ፣ ወንዲት ፤ ዐጅሬ ፣ ዐጅሪት ፤ ዝንጀሮ ፣ ዝንጀሪት ።

ት ፤ በትንቢት ፣ መነሻ ፣ እየገባ ፣ በቂ ፣ ይኾ ናል ። ትለብሰው ፣ የላት ፤ ትከናነበው ፣ አማራት ። ይኸውም ፣ በየም ፣ ፈንታ ፣ የተነገረ ፣ ነው ።

ት ፤ ለሩቅ ፣ ሴት ፣ የአንቀጽ ፣ ዝርዝር ። እሱ ፣ እሷን ፣ ዐወቃት ።

ቶ ፤ መጨረሻው ፣ ራብዕ ፣ በኾነና ፣ ባል ኾነ ፣ የጇና ፣ የ፫ ፣ ፊደል ፣ ግስ ፣ ለሩቅ ፣ ወንድ ፣ የቦዝ ፣ ዝርዝሩ ፣ ገባ ፣ ገብቶ ፤ ወጣ ፣ ወጥቶ ፤ በላ ፣ በልቶ ፤ ጠጣ ፣ ጠጥቶ ፤ ሸኘ ፣ ሸኝቶ ፤ ሰጠ ፣ ሰጥቶ ፤ ዘነጋ ፣ ዘንግቶ ፤ ዘረጋ ፣ ዘርግቶ ።

ተባ ፤ (ተብዐ ፡ ጠብዐ) ፤ ጨከነ ፣ ጠነ ከረ ፣ ወንድ ፣ ወጣው ።

ተባ ፤ (በልጎ) ፤ ተሞረደ ፣ ሰላ ፤ ፈጠነ ።

ትብ ፤ (ትቡዕ) ፤ የተባ ፤ ስል ፣ ፈጣን ፣ ጠንካራ ፣ ቢላዋ ፣ መዋረቢያ ፣ ማንኛውም ፣ መሣ ሪያ ፤ እንደበት ።

ተባት ፤ (ተባዕት) ፤ ወንድ ፣ ሴትን ፣ የሚ ያሶልድ ።

ተባትና ፡ እንስት ፤ (ተባዕት ፡ ወእን ስት) ፤ ወንዴና ፣ ሴቴ ፤ ደንጊያ ፣ ዐፈር ፣ ውሃ ፣ ዕንጨት ፣ እንሰሳ ፣ አውሬ ፣ ወፍ ፣ ሰው ፤ ወይም ፣ ሌላ ፣ ፍጥረት ፣ (ዘፍጿ ፤ ፪ ። ማር፤ ፣ ፮) ።

ተባት ፤ ቍልፍ ፤ ወንዴ ፣ ቍልፍ ፣ ከሴ ቴው ፣ ጋራ ፣ የሚገጥም ። ሴቴው ፣ የሐር ፣ ጸድ ፣ ነው ።

ትባት ፤ (ትብዕ) ፤ ስለት ፣ ሹለት ፣ ጥን ካሬ ፣ ፍጥነት ።

መትባት ፤ መጠንከር ፣ መስላት ፣ መፍ ጠን ።

መትቢያ ፤ መጠንከሪያ ፡ መስሊያ ፡ መፍጠኛ ።

አተባ ፤ (**አትብዐ**) ፤ ሞረደ ፡ ጨው ፡ ነሰነሰ ፡ እውሃ ፡ አገባ ፡ ነከረ ፡ አጠነከረ ፡ አሰላ ፡ አሾለ ።

አትቢ ፤ ያተባ ፡ የሚያተባ ፤ አስሊ ፡ ነካሪ ፡ አጠንካሪ ፡ ባለጅ ፡ ጠይብ ።

ማትባት ፤ መንከር ፡ ማጠንከር ፡ ማስላት ፡ ማሾል ።

ማትቢያ ፤ ሞረድ ፡ ጨው ፡ ውሃ ፡ መሳል ።

አተባብ ፤ አፈጣጠን ፤ መትባት ።

ቱባ ፤ (**ዐረ ፡ ቱባዕ**) ፤ ከልስ ፡ ያይዶለ ፡ ጥሩ ፡ ጥይት ።

ቱባ ፤ ሙሉ ፡ የባሕር ፡ ድር ፡ ማግ ፡ ጥለት ፡ ሐር ፡ ጕድለት ፡ የሌለበት ።

ቱቦ ፤ ከስሚንቶና ፡ ከአሸዋ ፡ የተበጀ ፡ አሸንዳ ፤ ሰፊና ፡ ጠባብ ፡ ቦምባ ፤ የውሃ ፡ መውረጃ ፡ ቆካ ። ቱቦ ፡ ጣሊያንኛ ፡ ነው ።

(ጥቤ) **ትቤ** ፤ ያገር ፡ ስም ።

ታበበ ፤—ትዝብትን ፡ ፈራ ፤—(**አበበ**) ።

ታበየ ፤—ተደገፃ ፤—**ዐበየ** ።

ትቢያ ፤ ዐሲራ ፡ ብናኝ ፡ ደቃቅ ፡ ዐፈር ፡ አሸዋ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፴፰ ። መዝ፩ ፡ ፱) ። በግእዝ ፡ ተቤላ ፡ ጸበል ፡ ይባላል ።

ታቦር ፤ ጌታችን ፡ የአምላክነቱን ፡ ክብር ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የገለጠበት ፡ ተራራ ፡ በምድረ ፡ እስራኤል ፡ ያለ ።

ተቤተ ፤—ኰራ ፤—**ዐበየ** ።

ትቢት ፤—ዅራት ፤—**ዐበየ** ።

ቱቢት ፤ (**ዐረ ፡ ቱቤት**) ፤ ጥቍር ፡ የሐዘን ፡ ልብስ ፤ ሥሥ ፡ ካባ ፡ ከባሕር ፡ የመጣ ።

ታቦት ፡ (**ቶች**) ፤ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ የተጻፉባቸው ፡ ኹለት ፡ ጽላቶች ፡ በውስጢ ፡ ያሉባት ፡ ሣጥን ፡ በወርቅ ፡ የተለበጠች ፤ ጽላቱ ፡ ከእብነ ፡ በረድ ፡ ታቦቲቱ ፡ ከማይንቅዝ ፡ ዕንጨት ፡ ነው ፡ የተቀረጹት ፤ ኹሉም ፡ የሙሴ ፡ ሥራዎች ፡ ናቸው ። ጽላት ፡ እንደ ፡ መጣፍ ፤ ታቦት ፡ እንደ ፡ ማኅደር ፡ (ኢያ፫ ፡ ፤፩ ፡ ፤፯) ።

ታቦቲቱ ፤ **ታቦቷ** ፤ ያች ፡ ታቦት ፡ (፪ዜና ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፭) ።

ታቦት ፤ ቁመቱ ፡ እንድ ፡ ክንድ ፡ ተስንዝር ፡ ጕኑ ፡ እንድ ፡ ክንድ ፤ ውፍረቱ ፡ ሦስት ፡ ጣት ፡ የሾነ ፡ የክርስቲያን ፡ ጽላት ፤ ታቦት ፡ መባልን ፡ ከሣጥኑ ፡ ወስዷል ። ስመ ፡ አምላክ ፡ አልፋ ፡ ወያ ፤ የመልአክ ፡ የነቢይ ፡ የቅድስት ፡ ማርያም ፡ የሐዋርያ ፡ የጻድቅ ፡ የሰማዕት ፡ ስም ፡ ታቦተ ፡ እገሌ ፡ እየተባለ ፡ በላዩ ፡ ይጸፍበታል ፤ በየግእዝኑ ፡ ሣፍ ፡ የአርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ ሥዕል ፡ ይቀረጽበታል ። ከግብጽ ፡ መጥተው ፡ በአኵስም ፡ የነበሩት ፡ መዣመሪያዎቹ ፡ ታቦቶችም ፡ ታቦተ ፡ ማርያምና ፡ ታቦተ ፡ ሚካኤል ፡ ናቸው ።

ታቦት ፤ ጌታ ፡ መኰንን ፡ ባለቤት ። ታቦተ ፡ መልካም ፡ ዐጸደ ፡ ክፉ ፡ እንዲሉ ። ዐጸድ ፡ የተባለ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ነው ።

ታቦት ፤ በራስ ፡ ላይ ፡ የተማነ ፡ እጅ ፡ በሽ ፡ ኵቻ ፡ ጊዜ ፡ መደሸን ፡ የሚረታ ፤ ትርፍ ፡ ተምሳሌት ።

ታቦትኛ ፤ የታቦት ፡ አካኼድ ።

ታቦት ፡ አነገሠ ፤ በወረብ ፡ በዘፈንና ፡ በልልታ ፡ በከበሮ ፡ በጸናጽል ፡ በጭብጨባ ፡ አከበረ ፤ በቤተ ፡ ክሲያን ፡ ዙሪያ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ አዞረ ።

ታቦት ፡ ወጣ ፤ ነገሠ ፤ ዑደት ፡ ተደረገ ።

ታቦት ፡ ዘፋኝ ፤ ለ ፡ ስለ ፡ የቀረው ፡ ነው ፤ ለታቦት ፡ ስለ ፡ ታቦት ፡ የሚዘፍን ፡ የታቦት ፡ ዘፋኝ ።

ታቦተ ፡ ሕግ ፤ በውስጢ ፡ ሕግ ፡ ያለባት ፡ ታቦት ።

ታቦተ ፡ ሙሴ ፤ የሙሴ ፡ ታቦት ።

ታቦተ ፡ ጽዮን ፤ በዳዊት ፡ ዐምባ ፡ የነበረች ፡ ታቦት ። ነብሪድ ፡ ይሥሐቅ ፡ ግን ፡ አኵስም ፡ መጥታለች ፡ ይላል ።

ታቦት ፡ ተሸካሚ ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ ታቦት ፡ የሚይዝ ፡ ቄስ ፡ መነኵሴ ።

ትቤት ፤ በሺን ፡ አገር ፡ በሂማልያ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡ ረኽም ፡ ተራራ ፡ የመነኰሳት ፡ መኖሪያ ፡ ደብር ፡ ቅዱስን ፡ የመሰለ ። ጌታችንም ፡ ባ፲፪ ፡ ዓመቱ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እንዳስተማረ ፡ የሚያስረዳ ፡ በሺን ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ የብራና ፡ ጽሕፈት ፡ በገዳሙ ፡ ይገኛል ፡ ይባላል ።

ተበተበ ፤ጠመጠመ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ አሰረ ፤ አረተ ፡ አከተ ።

ተበተበ ፤ ዐዘመ ፡ ደገመ ። አሰረ ፡ ብለኸ ፡ አሰርኩሽን ፡ እይ ።

ተበተበ ፤ ወረረ ፡ ያዘ ፡ ከበበ ።

ተብታቢ ፡ (ዎች) ፤ የተበተበ ፡ የሚተበትብ ፤ አሳሪ ፡ አስማተኛ ፡ ጕንዳን ፡ ዕከክ ።

ትብተባ ፤ ጥምጠማ ፡ አሰራ ።

መተብተብ ፤ መጠምጠም ፡ ማሰር ፤ መውረር ፡ መከበብ ።

መተብተቢያ ፤ ጠፍር ፡ ገመድ ፡ ልጥ ፡ ዐረግ ፡ ገበ ፡ ሰይጣናዊ ፡ ድጋም ።

ተባተበ ፤ ጠማጠመ ፡ መላልሶ ፡ አሰረ ።

ተባተበ ፤ ደጋገመ ።

መተባተብ ፤ መጠማጠም ፡ መደጋገም ።

አስተበተበ ፤ አስጠመጠመ ፡ አሳሰረ ።

አስተበተበ ፤ አስደገመ ።

አስተበተበ ፤ አስወረረ ፡ አስከበበ ።

አስተብታቢ ፤ ያስተበተበ ፡ የሚያስተበትብ ፤ አሳሳሪ ።

ማስተብተብ ፤ ማስጠምጠም ፡ ማሳሰር ፡ ማስደገም ።

ማስተብተቢያ ፤ ማስጠምጠሚያ ።

ተተበተበ ፤ ተጠመጠመ ፤ ታሰረ ፡ ማሰሪያው ፡ ሰውየው ።

ተተበተበ ፤ ታዘመ ፡ ተደገመ ፡ አስማቱ ።

ተተበተበ ፤ ተወረረ ፡ ተያዘ ፡ ተከበበ ፡ ሥጋው ፡ ሰውነቱ ።

ተተብታቢ ፤ የሚተበተብ ።

ተበተበ ፤ **ተብታባ** ፤ ኩልታፋ ፡ ለንባዳ ፡ አፈ ፡ አስር ፤ ወንዱን ፡ አንቺ ፡ ሴቷን ፡ አንተ ፡ የሚል ፡ መሣቂያ ።

ትብትብ ፤ የተተበተበ ፡ ጥምጥም ፡ ውስብስብ ፡ አስርስር ፡ እርት ፡ እክት ፡ ኗኅብ ፡ ሐዋጅ ፡ ሸክ) ።

ትብትብ ፤ ያረቄ ፡ አሸንዳ ።

ትብትብ ፤ ዝብዝብ ፡ ነገር ፤ ፪ኛው ፡ ት ፡ ይጠብቃል ።

ትብትባት ፤ **ትብትቦሽ** ፤ ጥምጥማት ፡ አስራት ።

ተተባተበ ፤ ተጠላለፈ ፡ ተጠማጠመ ፡ ተሳሰረ ፡ ተያያዘ ፡ ተወሳሰበ ፡ (ዕብ፲፪ ፡ ፭) ።

መተባተብ ፤ መጠላለፍ ፡ መተሳሰር ።

አተባተበ ፤ አጠላለፈ ፡ አስተሳሰረ ፡ አያያዘ ፡ አወሳሰበ ።

ማተባተብ ፤ ማጠላለፍ ፡ ማስተሳሰር ።

ተበተበኩሽ ፤ (**አሰርኩሽ ፡ ተበተበኩሽ**) ፤ አሰረን ፡ አይ ።

አንተበተበ ፤ በቀላል ፡ ቄላ ፡ (ተቄላ) ።

አንተብታቢ ፤ ያንተበተበ ፡ የሚያንተበትብ ።

እንትብትብ ፤ የተንተበተበ ፡ ቄሎ ።

ማንተብተብ ፤ መቀሳት ።

ተንተበተበ ፤ ተቄላ ።

መንተብተብ ፤ መቄላት ።

ተንተባተበ ፤ ድዳ ፡ ለንባዳ ፡ ኾነ ፤ አንደበቱ ፡ ተርበተበተ ።

ተንተባታቢ ፤ የሚንተባተብ ።

መንተባተብ ፤ መኰላተፍ ።

መንተባተቢያ ፤ መኰላተፊያ ።

አንተባተበ ፤ ለንባዳ ፡ አደረገ ፤ አኰላተፈ ።

ማንተባተብ ፤ ማኰላተፍ ።

ተብተብ ፡ አለ ፤ ቸኰለ ።

አተባተብ ፤ አጠላለፍ ፤ መተብተብ ።

ተጋ ፤ (**ተግሀ**) ፤ ሠጋ ፡ እንቅልፍ ፡ ዐጣ ፤ ነቃ ፡ ዐሰበ ፤ ከስንፍና ፡ ራቀ ።

ተጊ ፤ የሚተጋ ፡ የሚያስብ ፤ ተጣጣሪ ።

ትጉ ፡ (ጎች ፡ ዎች) ፤ **ትጉህ**) ፤ የተጋ ፡ የሠጋ ፤ ሥግ ፡ ንቅ ፡ ዐሳቢ ፡ (ምሳ፲፫ ፡ ፱) ።

ትጉነት ፤ **ትጉህነት** ፤ ትጉ ፡ መኾን ።

ትጋት ፤ (**ትግሀት**) ፤ ንቃት ፡ እንቅልፍ ፡ ማጣት ፡ (ኢሳ፶፭ ፡ ፯ ። ሉቃ፪ ፡ ፵) ። ሲበዛ ፡ ትጋቶች ፡ ይላል ፡ (መዝ፷፫ ፡ ፭) ።

መትጋት ፤ መሥጋት ፡ መንቃት ፡ ማሰብ ።

መትጊያ ፤ መሥጊያ ፡ መንቂያ ፡ ማሰቢያ ።

አተጋ ፤ (**አትግሀ**) ፤ አሠጋ ፡ አነቃ ፡ ጉተ ጉተ ፡ ዕረፍት ፡ ነሣ ፡ (መክ፭ ፡ ፲፫) ።

አትጊ ፤ (**አትጋሂ**) ፤ ያተጋ ፡ የሚያተጋ ፤ አሠጊ ፡ ጉትጎች ።

ማትጋት ፤ ማሥጋት ፡ መጉተጉት ።

ማትጊያ ፤ ማሥጊያ ።

አተጋጋ ፤ አነቃቃ ፡ አሳሰበ ።

ማተጋጋት ፤ ማነቃቃት ፡ ማሳሰብ ።

ማተጋጊያ ፤ ማሳሰቢያ ።

አስተጋ ፤ ትጉህ ፡ አስደረገ ።

ተታጋ ፤ (**ተታግሀ**) ፤ ትጋትን ፡ ተሰጣጠ ።

አታጋ ፤ (**አስተታግሀ**) ፤ (ጥን) አነቃቃ ።

አታጊ ፤ ያታጋ ፡ የሚያታጋ ፤ አነቃቂ ።

ማታጋት ፤ ማነቃቃት ።

ማታጊያ ፤ ማነቃቂያ ።

አተጋግ ፤ አሠጋግ ፤ መትጋት ።

ተግ ፤ **ቱግ** ፤—ቦግ ፤—ተገተገ ።

ትግ ፤—ብልጭ ፤—ተገተገ ።

ተገበ ፤ (**ጠገበ**) ፤ ወለሰ ፡ ዐፈነ ፤ ዝናሙ ፡ ከፋ ፤ አካፋ ፡ ችፍችፍ ፡ አለ ።

ተግብ ፤ ነፋስና ፡ ብርድ ፡ ውሽንፍር ፡ ያለው ፡ ወሲስ ፡ ዐፈና ።

ተግብ ፡ ኾነ ፤ ቀዘቀዘ ፡ በረደ ፡ ተማነ ፡ ከበደ ፡ ከረመቱ ።

መተግብ ፤ መወለስ ፡ ማፈን ፡ መቀዝቀዝ ።

መተግቢያ ፤ መወለሻ ፡ መቀዝቀዣ ።

አተጋገብ ፤ አቀዛቀዝ ፤ መተገብ ።

ተገድራ ፤—ተቀጽላ ፤—ገደረ ።

ታገለ ፤—ተናነቀ ፤—ዐገለ ።

ትጉልጉል ፤—የተጣበበ ፤—ጉለጉለ ።

ተጉላላ ፤—ተንገላታ ፤—ጉላ ።

ተጕለት ፤—ያገር ፡ ስም ፤—ጕለተ ።

ተጕመለለ ፤—ተቈነነ ፤—ጕመለለ ።

ተጕማማ ፤—ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ተወራ ፤—(ጕማ) ።

ተገነ ፤ (ጸቈነ) ፤ ዐጠረ ፡ ቀጠረ ፡ ጀጕለ ፡ ጋረደ ፡ ከለለ ፡ ዐቀበ ። ጠነነን ፡ እይ ።

ተጋኘ ፤ የተገነ ፡ የሚተግን ፤ ጀጓይ ።

ተገን ፤ (ጸቈን) ፤ ጀጕል ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ ከለላ ፤ በተገን ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሞቃት ፡ ስፍራ ። ዓለም ፡ ጥበብ ፡ ጨለማ ፡ ተገን ፡ እንዲሉ ።

ተገን ፤ ግንብ ፡ ከፍተኛ ፡ ምድር ።

ተገኔ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ የኔ ፡ ተገን ፡ ማለት ፡ ነው ።

መተገን ፤ መጀጕል ፡ መከለል ፡ ማቀብ ።

መተገኛ ፤ መጀጕያ ፡ መከለያ ፡ ማቀቢያ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ።

አስተገነ ፤ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ አሠራ ፡ አስጀጕለ ፡ አስጋረደ ፡ አስከለለ ።

አስተገነ ፤ አስጠጋ ፡ አስጠለለ ።

ማስተገን ፤ ማስጀጕል ፡ ማስከለል ።

ተተገነ ፤ ታጠረ ፡ ተቀጠረ ፡ ተጀጕለ ፡ ተከለለ ፡ ታቀበ ፤ የተከል ፡ ቦታ ፡ በካብና ፡ በንጨት ።

ተተገነ ፤ ተጠጋ ፡ ተጠለለ ፤ የሰው ።

ትግን ፤ የተተገነ ፡ የተጀጕለ ።

(ጥተ) **መተግን ፤** መጀጕል ፡ መከለል ፤ መጠጋጋት ፡ መጠለል ።

መተገኛ ፤ መጠጊያ ፡ መከለያ ፡ ተገን ።

አተጋገን ፤ አጀጓጕል ፤ 'መተገን ። ችግኝን ፡ እይ ፤ የተገነ ፡ ዘር ፡ ነው ።

ታገሠ ፤—ቻለ ፤—(ዐገሠ) ።

ተገረ ፤ ወደ ፡ ዛፍ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ተገረ ፤ ነገደ ፡ ወጥቶ ፡ ወርዶ ። ችገረን ፡ ተመልከት ።

ተገረ ፤ ተቈጣ ፡ ግልፍተኛ ፡ ኹነ ፤ ገዘፈ ።

ትግሬ ፤ ከሐማሴን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ፡ ያገርና ፡ የነገድ ፡ ስም ፤ ቈላ ፡ ምድር ፡ ሐባብ ፤ በመረብ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ከምጥዋ ፡ እስከ ፡ ተከዚ ፡ የሚገኝ ፡ ወረዳ ፡ ኹሉ ። የነገድ ፡ ስም ፡ ሲኾን ፡ ነጋዴ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ባላገሮቹም ፡ ታችኛውን ፡ ትግረ ፡ ላይኛውን ፡ ትግራይ ፡ ይሉታል ። በግእዝ ፡ ግን ፡ ደጋውም ፡ ቈላውም ፡ ጥንድነት ፡ ትግሬ ፡ ይባላል ።

ትግሬ ፤ የትግሬና ፡ የትግራይ ፡ ሰው ፡ (ዐማርኛ) ።

ትግሬ ፤ የቋንቋ ፡ ስም ፤ ግእዝን ፡ መደብ ፡ አድርጎ ፡ ከዐረብና ፡ ከዐብራይስጥ ፡ ከሱርስት ፡ የሚገኘም ፡ የሐባብ ፡ ልሳን ።

ትግሮች ፤ የትግሬ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የትግሬ ፡ ተወላጆች ፡ ትግሪኛ ፡ የሚናገሩ ፡ ነገዶች ፡ ደገኞችና ፡ ቈለኞች ።

ትግሪኛ ፤ (ትግራይ) ፤ የቋንቋ ፡ ስም ፤ የትግሬ ፡ ወገን ፡ ልሳን ፡ ከግእዝና ፡ ካማርኛ ፡ የሚገጥም ።

ትግሬ ፤ (ቲግራ) ፤ በጠግሮስ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ የሚኖር ፡ ታላቅ ፡ ነብር ፡ ቍጡ ፡ ጎይለኛ ። ባላገርም ፡ በበረሓ ፡ ትግሬ ፡ የምትባል ፡ አውሬ ፡ አለች ፡ እያለ ፡ ያወራል ። . . . . . .

. . . . . .

. . . . . .



ትግሬ ፡

ትግሪዳ ፡ (ታ) ፤ መንገድገድ ፡ መፍገም ፡ ፍግምግምታ ።

ትግሪት ፤ የበረሓ ፡ ሠሥ ፡ ዲግዲግ ፡ እንሹ ።

ትግሪት ፤ ዛር ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ዐዶ ፡ ከቢር ።

ትግሪት ፤ ቍጣ ፡ ወፈፍታ ።

ትግሪታም ፤ (ቲግራዊ) ፤ ቍጣም ፡ ወፈፍታም ።

ትግሪተኛ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ቍጡ ፡ ወፈፍተኛ ።

ተግታ ፤—ቦግታ ፤—ተገተገ ።

ተገተገ ፤ (ተተገ) ፤ ገረፈ ፤ በእሳት ፡ ተኰሰ ።

ተግታጊ ፤ የተገተገ ፡ የሚተግትግ ፤ ገራፊ ።

ትግተጋ ፤ ገረፋ ፡ ትኵሳ ።

መተግተግ ፤ መግረፍ ፡ መተኰስ ።

መተግተጊያ ፤ መግረፊያ ፡ መተኰሻ ፡ ጅራፍ ፡ መዳብ ።

አስተገተገ ፤ አስገረፈ ፤ አስተኰሰ ።

ማስተግተግ ፤ ማስገረፍ ፡ ማስተኰስ ።

ማስተግተጊያ ፤ ጊዜ ፡ አደባባይ ።

ተተገተገ ፤ ተገረፈ ፤ ተተኰሰ ።

ትግትግ ፤ የተተገተገ ፡ የተገረፈ ፤ ግርፍ ።

መተግተግ ፤ መገረፍ ።

አንተገተገ ፤ (ነቲግ ፡ ነትግ) ፤ አብረቀረቀ ፡ አብለጨለጨ ፡ ቦግ ፡ ቦግ ፡ አደረገ ፡ አበራ ።

ማንተግተግ ፤ ማብረቅረቅ ፡ ማብራት ።

ተንተገተገ ፤ ተብረቀረቀ ፡ ተብለጨለጨ ፤ ብልጭልጭ ፡ አለ ፤ በራ ።

ትንታግ ፡ (ነች) ፤ ክፋይ ፤ ቀጭ ፡ ጎይ ለኛ ፡ ተናጋሪ ፡ ሰው ፡ (ምሳሯኔ ፡ ፲ኛ) ።

ትንትግ ፡ ትንትግ ፡ አለ ፤ ቶሎ ፡ ሎቶ ፡ ተቈጣ ።

መንተግተግ ፤ መብረቅረቅ ፡ መብለጭለጭ ።

መንተግተጊያ ፤ መብረቅረቂያ ።

ተግ ፤ ቦግ ፡ ብልጭ ፡ ቆም ።

ተግ ፡ አለ ፤ ቦግ ፡ አለ ፤ በራ ፤ ቆመ ።

ተግ ፡ ተግ ፡ አለ ፤ ቦግ ፡ ቦግ ፡ አለ ።

ተግታ ፤ ቦግታ ፤ መቆም ።

ቱግ ፤ ተግ ።

ቱግ ፡ አለ ፤ በፍጥነት ፡ ነደደ ፤ ተቈጣ ።

ቱግታ ፤ የችቦ ፡ አበራር ።

ትግ ፤ ብልጭ ።

ትግ ፡ ትግ ፡ አለ ፤ ተንተገተገ ።

አተጋተግ ፤ አገራረፍ ፤ መተግተግ ።

ተጅ ፡ አይጡ ፤—የበረ ፡ ስም ፤—ወጣ ።

ታደገ ፤—አዳነ ፤ ተመለሰ ፤—ዐደገ ።

ትድግና ፤—ማዳን ፤—ዐደገ ።

ታዲያ ፤ ታዲያስ ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ ኀይለ ፡ ቃል ። ተዚያ ፡ ወዲያ ፡ ማለት ፡ ነው ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ትለኛለኽ ፤ ታዲያስ ፡ ምን ፡ ታደርገኛለኽ ።

ተድላ ፤—ድሎት ፤—ደላ ።

ታጀረ ፤—ከበራ ፤—ዐጀረ ።

ቲሃ ፤ (ተዪሀ ፡ ቴሀ) ፤ ችቦ ፡ ዳቦት ፡ ሽጉ ፡ የሞራሮ ፡ መብራት ።

ተወ ፤ ለቀቀ ፡ ጣለ ፡ ፈታ ፡ ገደፈ ፤ ርግፍ ፡ አደረገ ፡ ማረ ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፭፰) ። ተውኸ ፡ ተዉ ፡ ተዋችኹ ፡ ተወች ፡ ተውሽ ፡ ተውኹ ፡ ተውን ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ። (ተረት) ፤ ያምራል ፡ ብሎ ፡ ከተናገሩት ፡ ይከፋል ፡ ብሎ ፡ የተዉት ።

ተወት ፤ ለቀቀ ።

ተወት ፡ አደረገ ፤ ለቀቀ ፡ አደረገ ።

መተው ፤ መልቀቅ ፡ መጣል ፡ (፭ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፭፫) ። መተው ፡ ነገሬን ፡ ከተተው ፡ እንዲሉ ።

መተዊያ ፤ መልቀቂያ ፡ መጣያ ።

አስተወ ፤ አስለቀቀ ፡ አስረገፈ ፡ አስጣለ ፡ አስማረ ፡ (መዝ፻፴፭ ፡ ፮ ። ኢሳ፲፱ ፡ ፭፯ ። ሕዝ፴፬ ፡ ፲) ።

ማስተው ፤ ማስለቀቅ ፡ ማስጣል ።

ማስተዊያ ፤ ማስጣያ ።

ተተወ ፤ ተለቀቀ ፡ ተፈታ ፡ ተገደፈ ፡ ተጣለ ፡ ቀረ ፡ ተማረ ፡ (ነሐኄ ፡ ፱ ። ኢሳ፭፯ ፡ ፲) ።

ተው ፤ ልቀቅ ፡ ጣል ።

ተው ፤ አባክኽ ፤ በል ። ተው ፡ ኺድ ፤ ተው ፡ ተነሥ ፡ ተው ፡ ብላ ።

ተው ፡ ዕንክ ፤ በሬን ፡ ካንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለመከልከል ፡ የሚነገር ፡ ቃል ። ዕንካን ፡ ተመልከት ።

ተዉ ፤ የቅርብ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፤ በርስዎ ታም ፡ የቅርብ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ትእዛዝ ፡ እንቀጽ ።

ተዪ ፡ ተይ ፤ ልቀቂ ፡ ጣዪ ።

ትቶት ፤ ጥሎት ።

ትቶት ፡ ኺዲል ፤ ጣም ፡ የለውም ፡ መጠጡ ።

ቲውሽ ፤ (ተው ፡ ወሽ) ፤ አህያን ፡ ለማገድና ፡ ለመከልከል ፡ የሚባል ፡ ቃል ። እንቱሽን ፡ አስተውል ።

ታው ፤ ስመ ፡ ፊደል ፡ ተ ፤ ትርጓሜው ፡ መጨረሻ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ታዊ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ።

ቴዎድሮስ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ምሥራቃዊ ፡ ስማዕት ፤ (ስንክ ፡ ጥር፲፱) ። በጽርኡ ፡ ቴዎዶርስ ፡ የግዚር ፡ ስጦታ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ቴዎድሮስ ፤ ዐምስቱን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ ያደረጉ ፡ የሐበሻ ፡ ንጉሥ ።

ተዋኔ ፤—ፈላስፋ ፤—ዋኝ ።

ተዋፅኦ ፤—መዋጮ ፤—ወጣ ።

ታዛ ፤—የምድራኽ ፡ ቅይድ ፤—ዐዘለ ።

ትዝ ፤—መታሰብ ፤—ተዘዘ ።

ታዘበ ፤—ጠረጠረ ፤—ዐዘበ ።

ተዘዘ ፤ ታሰበ ፡ ታወሰ ። በትግሪኛ ፡ ግን ፡ ዘነበለ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ትዝ ፤ መታሰብ ።

ትዝ ፡ አለው ፤ ታሰበው ፡ ታወሰው ።

ትዝታ ፤ ዕስብታ ፡ ትውስታ ።

ትዛዝ ፤—በቁሙ ፤—አዘዘ ።

ተዚያ ፤—ከዚያ ፤—ዚያ ።

ታዛይ ፤—ተጨማሪ ፡ ቤት ፤—ዐዘለ ።

ተጣረ ፤—ከሰራ ፤—(ጣረ) ።

ትሑት ፤ (ተሐተ) ፤ ቅን ፡ ገር ፡ ታዛዥ ፡ ተዋራጅ ።

ትሕትና ፤ ትሑትነት ፡ ዝቅታ ፡ የፈቃድ ፡ ውርደት ።

ትሕትናም ፤ ባለትሕትና ፡ ሁራት ፡ አልባ ።

ትኋን ፤—ያልጋ ፡ ተባይ ፤—ተኰነ ።

ታጎሣሥ ፤ (ጎሠሠ) ፤ የወር ፡ ስም ፤ ፱ኛ ፡ ወር ፡ ከመስከረም ። ምስጢሩ ፡ ጌታን ፡ ለመፈለ ግና ፡ ያለበትን ፡ ለመመራመር ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ የሰብአ ፡ ሰገልን ፡ መምጣት ፡ ያሳያል ። ባሳገርም ፡ ትግሥ ፡ ይለዋል ።

ተጠናወተ ፤—ወረደ ፤—(ጠነወተ) ።

ታጠቀ ፤—በወገቡ ፡ አሰረ ፤—(ዐጠቀ) ።

ትያትር ፤ (ትያጥሮን) ፤ የተምሳሊት ፡ ጨዋታ ።

ተካ ፤ (ትግ ፡ ተክአ) ፤ በተወሰደ ፡ በጠፋ ፡ በሞተ ፡ በኼደ ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ ሰጠ ፡ መለሰ ፡ ረጠበ ፡ ከፈለ ፡ ካሰ ፡ ወከለ ፡ (ዘሌጅ፱ ፤ ፲፰) ።

ተካ ፤ ተካልኝ ፤ የሰው ፡ ስም ።

ተኪ ፤ የተካ ፡ የሚተካ ፤ ከፋይ ፡ ወካይ ።

መተካት ፤ መስጠት ፡ መክፈል ፡ መወከል ።

መተኪያ ፤ መክፈያ ፡ መወኪያ ።

መተኪያ ፤ መተኮ ፤ የሰው ፡ ስም ።

መተኪያ ፤ የሴት ፡ ስም ።

አስተካ ፤ አሰጠ ፡ አስከፈለ ፡ አስረጠበ ፡ አስወከለ ።

አስተኪ ፤ ያስተካ ፡ የሚያስተካ ፤ አስከፋይ ።

ማስተካት ፤ ማስከፈል ፡ ማስወከል ።

ማስተኪያ ፤ ማስከፈያ ፡ ማስወኪያ ።

ተተካ ፤ ተወከለ ፤ ተሰጠ ፡ ተከፈለ ፡ ተረጠበ ፡ ስጦታው ፡ ለሰው ፤ ሰውየው ፡ ስጦታን ።

ተተኪ ፤ የሚተካ ፡ የሚወከል ፤ ተወካይ ።

ተተኪነት ፤ ተወካይነት ።

ምትክ ፡ (ክች) ፤ የተተካ ፤ ወኪል ፡ ቶፋ ።

ምትክ ፤ ለውጥ ፡ ፈንታ ፡ ካሳ ።

ምትኩ ፤ የሰው ፡ ስም ።

ምትኬ ፤ የወንድና ፡ የሴት ፡ ስም ። ኩ ፡ የሻች ፤ ኬ ፡ የቋሚ ፡ ዝርዝ ፡ ነው ።

ትኩ ፤ (ትግ ፡ ትኩእ) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ምትክ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(ጥተ) መተካት ፤ መከፈል ፡ መረጠብ ፡ መወከል ።

መተኪያ ፤ መክፈያ ፡ ምትክ ፡ መቀበያ ። መወኪያ ፡ ዘብ ፡ ሥራ ።

አተካክ ፤ አወካከል ፤ መተካት ።

ቲኪ ፤—የጭቃ ፡ ሹም ፡ ተወራጅ ፤—(ቶከቶክ) ።

ቲክ ፤ (ተየከ) ፤ መምላት ፡ መንተርፈፍ ።

ቲክ ፡ አለ ፤ ጢም ፡ አለ ፤ መላ ።

ትክ ፤ (ሰኪው) ፤ መተኰር ፤ ዐይንን ፡ አለ መንቀል ።

ትክ ፡ ብሎ ፡ አየ ፤ (ሰከወ) ፤ ተኰረ ፤ ባለ ማቋረጥ ፡ አስተዋለ ።

ተከዘ ፤ (ተክዘ ፡ ተከዘ) ፤ ዐዘነ ፡ ተቁረ ቈረ ፡ ከደስታ ፡ ከፈገግታ ፡ ራቀ ።

ተከዘ ፤ አዘገመ ፡ ቈየ ። ዐለንጋ ፡ አስቲገዙ ፡ በክርን ፡ ይተክዙ ። እራት ፡ አስቲቀርብ ፡ በጥሬ ፡ ተከዘ ።

ተካኝ ፤ የሚተክዝ ፡ የሚያዝን ፤ ዐዛኝ ፡ ተቁርቋሪ ።

ትክዝ ፤ (ትኩዝ) ፤ የተከዘ ፡ ያዘነ ።

ትክዝ ፡ አለ ፤ ዕዝን ፡ አለ ፤ ዐዘን ፡ ገባው ።

ትክዛ ፤ ፀዘና ፡ መሬት ፡ ቍርቁራ ።

መተከዝ ፤ ማዘን ፡ መቁርቁር ።

መተከዣ ፤ ማዘኛ ፤ በግና ፡ ሙሾ ።

አተከዘ ፤ አስተከዘ ፤ አሳዘነ ፡ ዐዘን ፡ አሳደረ ። አተከዘ ፡ የግእዝ ፤ አስተከዘ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ።

አስተካኝ ፤ ያስተከዘ ፡ የሚያስተክዝ ፤ አሳዛኝ ።

ማስተከዝ ፤ ማሳዘን ።

ማስተከዣ ፤ ማሳዘኛ ።

ትካዜ ፤ ዐዘን ፡ ዐሳብ ፡ እህህታ ፡ ቍዘማ ፡ የለቅሶ ፡ ዜማ ፡ (ሕዝ፴ ፤ ፲፯ ። ፩ሌጥ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

አተካከዝ ፤ አስተዛዘን ፤ መተከዝ ።

ተከዘ ፤ ፈሰሰ ፡ ወረደ ፡ (ግእዝ) ።

ተከዚ ፤ ተከዜ ፤ የዠማ ፡ ስም ፤ ከላስታ ፡ የሚነሣ ፡ ወንዝ ፡ በአትባራ ፡ ከጀቱ ፡ አባዮች ፡ ጋራ ፡ የሚገጥም ፡ ታላቅ ፡ ፈሳሽ ፤ የትግራንና ፡ የበጌምድርን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የሚለይ ፡ ዥረት ። በግእዝ ፡ ሲናበብ ፡ ተከዘ ፡ ይባላል ።

ተከየ ፤—ለገመ ፤—ከየ ።

ተከለ ፤ (ተኪል ፡ ተከለ) ፤ ቸከለ ፡ ቀበቀበ ፡ ከሰመ ፡ እመራት ፡ አገባ ፡ ሻጠ ፡ ወተፈ ፡ ሸጐጠ ፡ አቆመ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፮) ።

ተከለ ፤ ቀላድ ፡ (ምድር) ፡ ሰጠ ። (ውርርድ ፡ ተከለ) ፤ ማር ፡ እሰጥ ፡ አለ ። (ስሙን ፡ ተከለ) ፤ አስጠራ ። (ታቦት ፡ ተከለ) ፤ ቤተ ፡ ከሲያን ፡ ሠራ ።

ተከለ ፤ አጸና ፡ መሠረተ ፡ አለማ ። ግብር ፡ ተከለበት ፤ ሳል ፡ ተከለበት ፡ እንዲሉ ።

ተካይ ፡ (ዮች) ፤ የተከለ ፡ የሚተክል ፤ ቸካይ ፡ ከሳሚ ፡ አቋሚ ፡ (ዮሐ፲፭ ፡ ፩) ።

ተካይ ፡ ነቃይ ፤ ሰውን ፡ በ(ከ)ርስት ፡ በ(ከ) ማዕርግ ፡ የሚተክል ፡ የሚነቅል ፡ ባለሥልጣን ።

ተካይነት ፤ ተካይ ፡ መኾን ።

ተከላ ፤ ትክሎሽ ፤ (ትክለት) ፤ የመትከል ፡ ሥራ ።

ተክል ፡ (ሎች) ፤ ቡቃያ ፡ ችግኝ ፡ ፍሬው ፡ የሚበላና ፡ የማይበላ ፡ ዕንጨት ፤ የሽቱ ፡ ቅጠል ፤

ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ዛፍ ። ተክል ፡ ዘርፍ ፡ ይዞ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፡ ተክለ ፡ ማር ያም ፡ ተክለ ፡ ሥላሴ ፡ ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ እያለ ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡ ይኾናል ።

ተክለ ፡ አልፋ ፤ ባ፲፰፻፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተይዘው ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በፍየል ፡ ዐምባ ፡ ተገርፈው ፡ ምላሳቸው ፡ ተቈርጦ ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ የሞቱ ፡ መናኝ ፡ ሊቅ ፡ መምር ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ በ፲፰፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የነበሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሐዋርያ ፡ ጻድቅ ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ ባ፲፰፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የነገሡ ፡ የላስታ ፡ ንጉሥ ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ ባ፲፰፻፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የነበሩ ፡ ዕጨጌ ።

ተክሌ ፤ ከፊለ ፡ ስም ፤ የኔ ፡ ተክል ፡ ተብሎም ፡ ይተረጐማል ።

ተክልዬ ፤ የኔ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ። ሰነቃ ፡ ብለኸ ፡ ሳንቃን ፡ እይ ።

አትክልት ፤ ተክሎች ።

አትክልተኛ ፡ (ኞች) ፤ ያትክልት ፡ ሠራተኛ ፡ ባላትክልት ፤ ኰትኳች ፡ ዐጋይ ።

አትክልት ፡ ተካይ ፡ (ዮች) ፤ አትክልት ፡ የሚተክል ። ፈረንጆች ፡ ጕርዲኔ ፡ ይሉታል ።

አታክልት ፤ አትክልት ፤ ዛፎች ፡ ዅትዅቶች ። አትክልት ፡ የግእዝ ፤ አታክልት ፡ ያማርኛ ፡ ነው ፤ በባላገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ተክል ፡ ይነገራል ።

መትከል ፤ መቸከል ፡ መከሰም ፡ ማቆም ፡ (መከፎ ፡ ፪) ።

መትከያ ፤ መሸጐሚያ ፡ መከሰሚያ ፡ ማቆሚያ ፡ መደብ ፡ ቅብቅብ ፡ ጕድጓድ ፡ ዶማ ፡ ዐንካሴ ፡ ሜዳ ፡ (ዘፀ፳፯ ፡ ፲፱) ።

መትከያ ፡ መንቀያ ፤ የመንግሥት ፡ መሬት ።

ተካከለ ፤ መላልሶ ፡ ተከለ ።

ተካከለ ፤—ትክክል ፡ ተኳኺነ ፤—አከለ ።

አስተከለ ፤ አስቸከለ ፡ አስከሰመ ፡ አስቆመ ።

አስተከለ ፤ ቀላድ ፡ አሰጠ ።

አስተከለ ፤ አስመሠረተ ፡ አስለማ ።

አስተካይ ፤ ያስተከለ ፡ የሚያስተክል ።

ማስተከል ፤ ማስቸከል ፡ ማስቀብቀብ ፡ ማስቆም ፤ መሬት ፡ ማሰጠት ።

ማስተከያ ፤ ጊዜ ፡ ስፍራ ።

ተተከለ ፤ ተቸከለ ፡ ተቀበቀበ ፡ ተከሰመ ፡ ተሻጠ ፡ ገባ ፡ ተሸጐጠ ፡ ቆመ ፡ (ፉሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፵፱ ። ሕዝ፲፱ ፡ ፲፫ ። ሉቃ፲፯ ፡ ፮ ። ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፭) ።

ተተከለ ፤ ርስት ፡ ተቀበለ ።

ተተከለ ፤ ተመሠረተ ፡ ጸና ፡ ለማ ።

ተተካይ ፤ የሚተከል ፤ ቀዋሚ ።

ትክል ፤ (ትኩል) ፤ የተተከለ ፡ የቆመ ፡ የጸና ። ትክል ፡ ድንጋይ ፡ እንዲሉ ።

ትክለኛ ፡ (ኞች) ፤ ባለመሬት ፤ ቀላድ ፡ ያለው ።

ትክል ፡ አለ ፤ በመሬት ፡ ቆመ ፤ ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ወደቀ ፡ ተደፋ ።

ተታከለ ፤ ተቻከለ ።

ተታከለ ፤ ርስት ፡ ተሰጣጠ ፡ ተቀባበለ ።

አታከለ ፤ አቻከለ ፡ አካሰመ ፤ (አትክልት ፡ መትከልን ፡ ረዳ) ።

አታካይ ፤ ያታከለ ፡ የሚያታክል ።

ማታከል ፤ ማቻከል ፡ ማካሰም ፡ ማቀባቀብ ።

ማታከያ ፤ ማካሰሚያ ።

አትካከል ፤ አቸካከል ፤ መትከል ።

ተኵላ ፡ (ሎች) ፤ ያውሬ ፡ ስም ፤ የበረሓ ፡ ውሻ ፡ የበግ ፡ ያንበሳ ፡ ጠላት ፡ ነጣቂ ። ዐይንን ፡ ተመልከት ።



ተኵላ ፡

ተኹለደሬ ፤ በወሎ ፡ ክፍል ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ስም ።

ተኩልኩሎ ፤—ሕፃናት ፤—ኩለኩለ ።

ተኵለፈለፈ ፤—አደፈ ፤—ኩለፈ ።

ተክሊል ፤—የሐግ ፡ ጋብቻ ፡ ሥርዐት ፤—ከለለ ።

ተከነ ፤ በገነ ፡ ነደደ ፡ ገመነ ፡ ፈላ ፡ በሰለ ፤ ተቈጣ ።

ተካኝ ፤ የሚተክን ፡ ተናዳጅ ።

ተካኝ ፤—የሚካን ፤—ካነ ።

ትክን ፤ የተከነ ፡ የፈላ ፡ የበሰለ ።

ትክን ፡ አለ ፤ እፍታ ፡ አልባ ፡ ኸነ ። ትክን ፡ ያለ ፡ ወጥ ፡ እንዲሉ ።

መትከን ፤ መንደድ ፡ መብሰል ፤ መቈጣት ።

መትከኛ ፤ መብገኛ ፡ መግመኛ ፡ መንደጃ ፡ መቈጫ ።

አተከነ ፤ አበገነ ፡ አናደደ ፡ አቃጠለ ።

አትካኝ ፤ ያተከነ ፡ የሚያተክን ፤ አቃጣይ ፡ አናዳጅ ።

አትክን ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ልብ ፡ አብሣን ።

ማትከን ፤ ማብገን ፣ ማግመን ።
ማትከኛ ፤ ማግመኛ ፣ ማናደጃ ፣ ማስቈማ ።
አትከነከነ ፤ (ከነከነ) ፤ አብሰለሰለ ፣ አግመነመነ ፤ በልብ ፣ ውስጥ ፣ አጒላላ ።
ማትከንከን ፤ ማብሰልሰል ።
ተትከነከነ ፤ ተብሰለሰለ ፣ ተናደደ ።
መትከንከን ፤ መብሰልሰል ፣ መናደድ ።
መትከንከኛ ፤ መናደጃ ፣ መቈማ ።
አተካከን ፤ አበጋገን ፤ መትከን ።
ተካነ ፤—ዲያቆን ፣ ኾነ ፤—ካነ ።
ተኰነ ፤ ኾነ ፣ ተገኘ ፣ ተፈጠረ ፤ የትኂን ።
ትኳን ፤ ትኂን ፣ (ኖች) ፤ የተባይ ፣ ስም ፤ በቤት ፣ ውስጥ ፣ በጣራ ፣ በግድግዳ ፣ ባልጋ ፣ በማንኛውም ፣ መኝታ ፣ ላይ ፣ ኹኖ ፣ የሰውን ፣ ገላ ፣ የሚቀነቅን ፣ የሚበላ ፣ የሚልጥ ፣ የሚያቃጥል ፣ የሚያንገበግብ ፤ ግማታም ፣ ፍጥረት ። (ተረት) ፤ እኔን ፣ ቢወዱኝ ፣ ወዳፍንጣቸው ፣ ወሰዱኝ ፤ አንቺን ፣ ቢጠሉሽ ፣ አጥመዝምዘው ፣ ጣሉሽ ፣ አለቻት ፣ ትኂን ፣ ቍንጣን ። የቤቴ ፣ መቃጠል ፣ ለትኂኑ ፣ በጀው ።



ትኂን ፣

ትኳናም ፤ ትኂን ፣ ያለበት ፣ የበዛበት ፣ ቈጥ ፣ ምንጣፍ ።
መትኰን ፤ ትኂን ፣ መኾን ።
መትኰኛ ፤ የፀሐይ ፣ የእሳት ፣ ሙቀት ፣ መበቅ ።
አተኰነ ፤ ትኂን ፣ አፈራ ፣ አበጀ ።
ማተኰን ፤ ማፍራት ፣ ማበጀት ፣ ትኂንን ።
አተኳኰን ፤ የትኂን ፣ አፈጣጠር ፤ መተኰን ።
ተኰፋነነ ፤—ኰራ ፤—(ኰፈነነ) ።
ተከረ ፤ (ተከነ) ፤ ተጨቀጨቀ ፣ ተነዘነዘ ።
ተካራ ፤ ተኻራ ፤ አተካራ ።
ትካር ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ አሳሳኝ ፣ ነገር ።
መትከር ፤ መነዘነዝ ።
አተከረ ፤ ጨቀጨቀ ፣ ነዘነዘ ።
አትካሪ ፤ ያተከረ ፣ የሚያተክር ፤ ነዝናዥ ።
አትከር ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ ጨቅጫቃ ፣ ነዝናዛ ፣ ልብ ፣ አውልቅ ።
አተካራ ፤ አተኻራ ፤ ንዝንዝ ፣ ጭቅጭቅ ።
አተካራም ፤ ጭቅጭቃም ፤ ልብ ፣ አቍሰል ።
አተካረኛ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ።
ማትከር ፤ መንዝነንዝ ፣ መጨቅጨቅ ።
ማትከሪያ ፤ መንዝነንዣ ፣ ምክንያት ።
አተካከር ፤ አነዛነንዝ ፤ ማትከር ።
ተኰረ ፤ ለበመ ፣ አስተዋለ ፤ ዐይኑን ፣ ጣለ ፣ ትክ ፣ ብሎ ፣ አየ ፣ ተመለከተ ፣ ዐወቀ ፤ አነጣጠረ ።
ተኳር ፣ (ሮች) ፤ የተኰረ ፣ የሚተኰር ፤ ልበኛ ፣ ለባሚ ፣ አስተዋይ ፣ አነጣጣሪ ።
ተኳርነት ፤ ተኳር ፣ መኾን ።
ትኰራ ፤ ምልከታ ።
መተኰር ፤ ማስተዋል ፣ መለበም ።
አተኰረ ፤ ተኰረ ።
አተኳሪ ፤ ተኳር ።
ማተኰር ፤ መተኰር ።
አስተኰረ ፤ አስመለከተ ።
ተተኰረ ፤ ታየ ፤ ዐይን ፣ ተጣለበት ።
ትኵር ፤ የተተኰረ ፣ ባለማቋረጥ ፣ የታየ ።
ትኵር ፣ ብሎ ፣ አየ ፤ ተኰረ ።
ተተኳኰረ ፤ ተፋጠጠ ፤ በትኰራ ፣ ተያየ ።
አተኳኰር ፤ የጥንቃቄ ፣ አስተያየት ፤ መተኰር ።
ተኸሬ ፤ በመረራ ፣ የሚዘራ ፣ ስንዴ ፣ ስም ።
ተካሪስ ፤ አተካሪስ ፤ በቀሚስ ፣ ላይ ፣ የተሰፋ ፣ ድንድን ፣ መታጠቂያ ። አባ ፣ ብለኸ ፣ አባ ፣ ወራን ፣ እይ ።
ተኰሰ ፤ ለኰሰ ፣ ለበለበ ፣ አቃጠለ ፣ ፈጀ ፣ ቤትን ፣ ደንን ፣ ድምርን ፣ አፍን ፣ የዐይን ፣ ሥርን ፣ ከንድን ፣ የሌባን ፣ ግንባር ፣ ዐዲስ ፣ ቍስልን ፣ ዕባጭን ፣ ሽሐኝን ።
ተኰሰ ፤ አሰማ ፣ ድም ፣ አደረገ ፣ ጠመን ዣን ፣ መድፍን ፣ ሽጕጥን ።
ተኰሰ ፤ ሰፋ ፣ ነጠላን ፣ ቅጥልጥል ፣ ደበሎን ።
ተኰሰ ፤ ዳመጠ ፣ ቀጥ ፣ ለጥ ፣ አደረገ ፣ አስተካከለ ፣ የታጠበ ፣ ልብስን ።
ተኰሰ ፤ ካሰ ፣ ቀቅ ፣ ከፈሰ ፣ ላቈሰለው ፣ ሰው ።
ተኰሰ ፤ የግንብን ፣ ደንጊያ ፣ መጋጠሚያ ፣ በኖራ ፣ በስሚንቶ ፣ ላከከ ፣ ቀባ ፣ ገጠመ ።
ተኰሰ ፤ መላ ፣ ፈጸመ ፣ ጕዳይን ፣ (ገቢር) ።
ተኰሰ ፤ ሞቀ ፣ ወበቀ ፣ ፀሐዩ ፣ (ተገብሮ) ፣ (ዘፍ፲፰ ፣ ፩ ። ፩ሳሙ ፣ ፲፩ ፣ ፱ ፣ ፲፩) ።
ተኰሰ ፤ ነደደ ፣ ተቃጠለ ፣ እሳቱ ፣ ቍጣው ፣ (ኢዮ፵፪ ፣ ፯) ።
ተኳሽ ፣ (ሾች) ፤ የተኰሰ ፣ የሚተኰስ ፣ የማይስት ፣ አነጣጣሪ ፤ ለኳሽ ፣ አቃጣይ ። ፍጥም ፣ አፍራሽ ፣ ቤተ ፣ ክሲያን ፣ ተኳሽ ፣ እንዲሉ ።

ተኳሽነት ፤ ለኳሽነት ።

ተኳሳ ፤ ሙቀታም ፣ ወበቃም ፣ ስፍራ ፤ የሚ ፋጅ ፣ የሚያቃጥል ፣ በርበሬ ፣ ሰናፍጭ ፣ ፈጠ ፤ የመ ሰለው ፣ ዥሉ ።

ተኵስ ፤ የዐይን ፣ የከብት ፣ የገላ ፣ ጠባሳ ፤ የሌባ ፣ ምልክት ፤ የነፍጥ ፣ ድምጥ ።

ተኵስ ፤ ከቀኝ ፣ ወደ ፣ ግራ ፣ የተሰፋ ፣ የን ጠላ ፣ ጠርዝ ፣ ስፌት ። ተኵስ ፣ ስፌት ፣ እንዲሉ ።

ትኩሳ ፤ ልብለባ ፣ ዳመጣ ።

መተኰስ ፤ ማቃጠል ፣ መለብለብ ፣ መዳ መጥ ፣ መካስ ።

መተኰሻ ፤ ማቃጠያ ፣ መለብለቢያ ፣ ቁላፋ ፣ ብረት ፣ ጉባ ፣ መዳብ ፣ የሪያ ፣ ጥርስ ፣ ፈልቅ ፣ ካውያ ፤ መካሻ ፣ የቀቅ ። (መስቀል ፣ መተኰሻ) ፤ መስከረም ፣ ፲፯ኛ ፣ ቀን ፤ ድምር ፤ ወይም ፣ ስፍራው ።

ተኳኰሰ ፤ ለባለበ ።

መተኳኰስ ፤ መለባለብ ።

አተኰሰ ፤ አሞቀ ፣ አወበቀ ።

ማተኰስ ፤ ማሞቅ ፣ ማወበቅ ።

አስተኰሰ ፤ አስለኰሰ ፣ አስለበለበ ።

አስተኰሰ ፤ ቃታን ፣ አሳበ ።

አስተኰሰ ፤ አስዳመጠ ፣ ቀጥ ፣ አስደረገ ።

አስተኰሰ ፤ አስካሰ ፣ አስቀበለ ፣ ካሳን ።

አስተኰሰ ፤ አስላከከ ፣ አስቀባ ፣ አስገጠመ ።

አስተኰሰ ፤ አስሞቀ ፣ አስወበቀ ።

አስተኳሽ ፤ ያስተኰሰ ፣ የሚያስተኰስ ፤ አ ስለኳሽ ፣ የተኰሰ ፣ አዛዥ ።

አስተኳሽነት ፤ አስተኳሽ ፣ መኾን ።

ማስተኰስ ፤ ማስለኰስ ፣ ማስለብለብ ፣ ማስ ዳመጥ ።

ማስተኰሻ ፤ ጊዜ ፣ ስፍራ ፣ ጠረጴዛ ።

ተተኰሰ ፤ ተለኰሰ ፣ ተለበለበ ፣ ተቃጠለ ፣ (ኢሳ፵፫ ፣ ፪) ።

ተተኰሰ ፤ ፍሽ ፣ ተሰማ ፣ ጥይቱ ።

ተተኰሰ ፤ ተካሰ ፣ ተቀበለ ።

ተተኰሰ ፤ ተዳመጠ ፣ ቀጥ ፣ አለ ።

ተተኰሰ ፤ ተላከከ ፣ ተገጠመ ፣ ተቀባ ።

ተተኰሰ ፤ መላ ፣ ተፈጸመ ፣ ተጨረሰ ።

ትኵስ ፤ ትኩስ ፤ የተተኰሰ ፤ ሙቅ ፣ ላበት ፣ እንፋሎት ፣ ያልተለየው ፣ (ኤሳሙ ፣ ፳፭ ፣ ፮) ። ትኵስ ፣ እንጀራ ፣ ትኵስ ፣ በድቍስ ፣ ትኵስ ፣ ዳቦ ፣ ትኵስ ፣ ደም ፣ እንዲሉ ።

ትኵስ ፣ ቅቤ ፤ ዐዲስ ፣ ለስታ ፣ ለጋ ፣ ቅቤ ። (በትኵሱ) ፤ ሳይበርድ ፣ ሳይቈይ ።

ትኵሳት ፤ ወበቅ ፣ ሙቀት ፣ ሐሩር ፤ ንዳድ ፣ የወባ ፣ የምች ፣ በሽታ ፣ (ዘፍጽ ፣ ፳፪ ። መዝ፪ ፣ ፭ ። ኤር፲፯ ፣ ፳) ።

ትኵሳታም ፤ ወባም ፣ ንዳዳም ፤ ትኵሳተ ፣ ብዙ ።

(ጥት) መተኰስ ፤ መለኰስ ፣ መቃጠል ።

መተኰሻ ፤ መለኰሻ ፣ መቃጠያ ።

ተታኰሰ ፤ ተላኰሰ ።

ተታኰሰ ፤ በጥይት ፣ በእሳት ፣ ተማታ ፣ ተ ዋጋ ፣ ተቋላ ፣ ተጣበሰ ።

መታኰስ ፤ መላኰስ ፣ መዋጋት ።

መታኰሻ ፤ መዋጊያ ፣ ዕርድ ፣ ምሽግ ፣ ዐ ምባ ፣ ኰረብታ ።

ተተኳኰሰ ፤ ተለኳኰሰ ፣ ተለባለበ ።

አታኰሰ ፤ አላኰሰ ፣ አለባለበ ።

አታኰሰ ፤ አዋጋ ፣ አጋደለ ።

አታኳሽ ፤ ያታኰሰ ፣ የሚያታኵስ ፤ አዋጊ ።

ማታኰስ ፤ ማላኰስ ፣ ማዋጋት ።

ማታኰሻ ፤ ጦርነት ፤ የጦር ፣ ሜዳ ።

አተኳኰሰ ፤ አለኳኰሰ ፣ አቀጣጠለ ፣ አያያዘ ።

ማተኳኰስ ፤ ማለኳኰስ ፣ ማቀጣጠል ።

አተኳኰስ ፤ አለኳኰስ ፤ መተኰስ ።

ትከሻ ፤ (ተኬሳ) ፤ ጫንቃ ፤ ዕድል ።

ትከሻ ፣ ወረደው ፤ ተቀጨ ፣ ታመመ ።

ትከሻም ፤ ዕድላም ፣ ክቡር ፣ ከባድ ፣ ሰው ።

ታከተ ፤ (ተከተ) ፤ ለፋ ፣ ደከመ ፣ ሰነፈ ፣ ሰለቸ ፣ (ኤሳሙ ፣ ፯ ፣ ፳) ።

ይታክቱ ፤ የወንድና ፣ የሴት ፣ ስም ።

ታካች ፣ (ኾች) ፤ የታከተ ፣ የሚታክት ፤ ሰነፍ ፣ (ምሳ፮ ፣ ፮ ፣ ፱) ።

ታካችነት ፤ ታካች ፣ መኾን ፤ ስንፍና ፣ ደ ካማነት ።

ታካታ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፣ ለታካች ፤ ደካማ ።

መታከት ፤ መልፋት ፣ መድከም ፣ መስነፍ ፣ (መክ፤ ፲፳) ።

መታከቻ ፤ መድከሚያ ፣ መስነፊያ ፤ ከባድ ፣ ሥራ ፣ መንገድ ።

አታከተ ፤ አለፋ ፣ አደከመ ፣ አሰነፈ ፣ አሰ ለቸ ፣ (ሚል፪ ፣ ፲፯ ። ማቴ፳፮ ፣ ፫) ።

አታካች ፤ ያታከተ ፣ የሚያታክት ፤ አድካሚ ፣ አስናፊ ።

ማታከት ፤ ማልፋት ፣ ማድከም ፣ ማስነፍ ።

ማታከቻ ፤ ማድከሚያ ፣ ማስነፊያ ።

ትካት ፤ ፈት ፣ ቀድሞ ፣ ዱሮ ፣ ጥንት ። ሰብአ ፣ ትካት ፣ እንዲሉ ።

ትክቶ ፤ ግዳጅ ፣ በየወሩ ፣ ከሴቶች ፣ የሚፈስ ፣ ደም ። ትካትና ፣ ትክቶ ፣ የግእዝ ፣ ቃል ፣ ነው ።

አተካከት ፤ አደካከም ፤ መታከት ።

ታከተ ፤—ታረተ ፤—አከተ ።

ተከተከ ፤ ጠቀጠቀ ፣ ወጋ ፣ በላ ።

ተከተከ ፤ ክፉኛ ፣ አሳለ ።

ተክታኪ ፤ የተከተከ ፣ የሚተክትክ ፤ ጠቅ ጣቂ ።

መተክተክ ፤ መጠቅጠቅ ፣ መውጋት ፣ መብ ላት ።

መተክተኪያ ፤ መጠቅጠቂያ ፣ መውጊያ ፣ የወፍ ፣ ያሞራ ፣ እፍ ፣ መስቄር ።

ተተከተከ ፤ ተጠቀጠቀ ፣ ተወጋ ፣ ተበላ ።

ትክትክ ፤ (ቅጽል) ፤ የተተከተከ ፤ ጥቅጥቅ ፣ ውግ ።

(ጥክክ) **ትክትክ** ፤ (ስም) ፤ የሕፃን ፣ ጉንፋን ፣ ሳል ።

ትክትክ ፣ አለ ፤ ሳለ ፣ ኡሁ ፣ ኡሁ ፣ አለ ።

አንተከተከ ፤ (አንሳዕበዐ) ፤ አሞቀ ፣ አ ፈላ ፣ አነፈረ ፣ አንጠቀጠቀ ፣ (ኢዮ፵፩ ፣ ፳፫) ። በተገ ብሮንትም ፣ ይፈታል ።

አንተክታኪ ፤ ያንተከተከ ፣ የሚያንተክትክ ፤ አፍሊ ።

እንትክትክ ፤ የተንተከተከ ፤ ሙቅ ።

ማንተክተክ ፤ ማሞቅ ፣ ማፍላት ፣ ማንፈር ።

ማንተክተኪያ ፤ ማፍሊያ ፣ ዕንጨት ፣ አ ላት ፣ ማሰሮ ፣ ድስት ።

ተንተከተከ ፤ ሞቀ ፣ በጣም ፣ ፈላ ፣ ነፈረ ፣ ተንጠቀጠቀ ።

መንተክተክ ፤ መሞቅ ፣ መፍላት ፣ መን ፈር ።

መንተክተኪያ ፤ መፍሊያ ፣ መንፈሪያ ፣ ጊዜ ፣ ምድጃ ፣ መጣሪያ ።

አተካተክ ፤ አጠቃጠቅ ፤ መተክተክ ።

(ቶከቶከ) ፤ አቶከቶከ ፤ ከሰው ፣ በታች ፣ ኹኖ ፣ ድምፁን ፣ በማሳነስ ፣ ተናገረ ፤ ነገርን ፣ ደገፈ ፣ እሥር ፣ እሥር ፣ አለ ፤ አሾከሾከ ፣ አሳበቀ ።

አቶክቷኪ ፤ ያቶከቶከ ፣ የሚያቶከቱክ ፤ አሾ ክሿኪ ።

ማቶክቶክ ፤ ማሾክሾክ ፣ ማሳበቅ ።

ማቶክቶኪያ ፤ ማሾክሾኪያ ፣ ማሳበቂያ ።

ቱኪ ፤ (ኳደራ) ፤ የጭቃ ፣ ሹም ፣ ተወ ራጅ ፣ ተከታይ ፣ ዕግት ፣ ተሸካሚ ።

ተከተለ ፤—ለጠቀ ፤—(ከተለ) ።

ተላ ፤ (ዕብ ፣ ቱሎዕ) ፤ ኾነ ፣ ተገኘ ፣ ተፈ ጠረ ፣ ተፍለከለከ ፣ ተርመሰመሰ ፣ ወጣ ፤ የትል ፣ (ዘፀ፯፤ ፳ ። ዘጉ፮ ፣ ፳፪) ።

ትል ፣ (ሎች) ፤ ብል ፣ ነቀዝ ፣ ተምች ፣ ግንደ ፣ ቁርቍር ፣ ቅንቡርስ ፣ መሰክ ፣ ሹሽ ፣ ኮሶ ፣ አሙኝት ፤ የመሰለው ፣ ኹሉ ። የሥጋ ፣ ትል ፣ የዘ መድ ፣ ጥል ። እበት ፣ ትል ፣ ይወልዳል ፣ እንዲሉ ።



ትል ፣

ትላም ፤ ትል ፣ ያለበት ፣ የበዛበት ፣ ባለትል ፤ አመንዝራ ።

ትላትል ፤ የትል ፣ ትል ፤ ብዙ ፣ ዐይነት ፣ ትል ።

ትላበራ ፤ (ትግ ፣ ሚሕ) ፤ ትል ፣ አበራ ፤ ሌሊት ፣ የሚያበራ ፣ ትል ፣ ኤሌትሪክ ፣ ያለው ፤ ወ ፍም ፣ ያበራል ።

ትሉ ፤ ያ ፣ ትል ፤ የርሱ ፣ ትል ።

ትሉ ፣ የማያንቀላፋ ፤ **እሳቱ ፣ የማይ ጠፋ** ፤ ገሃነመ ፣ እሳት ።

ትሉ ፤ (ትብሉ) ፤ ትናገሩ ። እናንተ ፣ እን ዲህ ፣ ትሉ ፣ የለምን ።

ትልት ፤ መትላት ።

ትልት ፣ አለ ፤ ተላ ።

መትላት ፤ ትል ፣ መኾን ።

መትሊያ ፤ ሙቀት ።

አተላ ፤ አወጣ ፣ አፍለከለከ ፣ አርመሰመሰ ፣ ትልን ። (ዘጉ፮ ፣ ፳፫) ። ዕጭን ፣ አስተውል ።

አተላ ፤ አበዛ ፣ አተረፈ ፣ አፈደፈደ ።

አትሊ ፤ ያተላ ፣ የሚያተላ ።

ማትላት ፤ ማውጣት ፣ ማፍለከለክ ።

ማትሊያ ፤ ጊዜ ፣ ስፍራ ።

አተላል ፤ የትል ፣ ተፈጥሮ ፣ አኳኋን ፤ መ ትላት ።

ቱሊ ፤ ተረፈ ፣ ዙሰሕ ። ቱኒን ፣ እይ ።

ቱሊያም ፤ ቱሊ ፣ ያለበት ፣ ባለቱሊ ።

ታለ ፣ አይሰጥ ፤ የሀብታም ፣ ንፋግ ፤ የሰረ ሰር ፣ ዐጥንት ።

ትሊ ፤ መዝመሪያ ፣ የመጣ ፣ ሥሥ ፣ አቡጀዲ ።

ቶሎ ፤ (ተለወ) ፤ ንኡስ ፣ አገባብ ፤ ፈጥኖ ፣ ቸኮሎ ። ቶሎ ፣ መጣ ፤ ቶሎ ፣ ኼደ ። በደለ ፣ ብለኽ ፣ ተበደለን ፣ እይ ።

ቶሎ ፣ ቶሎ ፤ ፈጥኖ ፣ ፈጥኖ ፣ ወዲያው ፣ ወዲያው ።

ተልባ ፤ (ተላቤ) ፤ የቅመም ፣ ስም ፤ ቅባት ነትና ፣ ማላጋነት ፣ ያለው ፣ ቅመም ፣ ከማር ፣ ጋራ ፣

የሚጠጣ ። ማርና ፡ ተልባ ፡ እንዲሉ ። ደረጠን ፡ ተመልከት ። (ቢከፍቱ ፡ ተልባ) ፤ በሸንጎ ፡ ተግ ደርዳሪ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ጦም ፡ ዐዳሪ ።



ተልባ ፡

ተልባ ፤ ውለ ፡ ቢስ ፡ የማይታመን ፡ ሰው ፡ ተንሸራታች ። እከሌ ፡ ተልባ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ።

ተልብማ ፤ ተልባ ፡ መሳይ ፡ ቀለመ ፡ ተልባ ፡ መልክ ፡ ተልባ ፡ እባብ ፡ ቦረቦሮ ፤ ሌላውም ፡ ነገር ፡ ዅሉ ።

ተልባ ፡ እግር ፤ (የተልባ ፡ እግር) ፤ ከተልባ ፡ ልጥ ፡ የተሠራ ፡ ክታን ፤ ጥሩ ፡ ልብስ ። በግእዝ ፡ ዐጌ ፡ ይባላል ፡ (ኢሳ፳ ፡ ፳፫) ። ፈረንጆ ችም ፡ ሊኖ ፡ ይሉታል ።

ተልባ ፡ ድርጥ ፤ (የተልባ ፡ ድርጥ) ፤ በውሃ ፡ የታሸ ፡ የተልባ ፡ ልጭጥ ። ደረጠ ፡ ብለኸ ፡ ድርጥን ፡ እይ ።

ተልባ ፡ ውሃ ፤ በጕጕም ፡ ከፍል ፡ የሚገኝ ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ።

ተልባ ፡ መጠጥ ፤ የተልባ ፡ መጠጥ ፤ ያቶ ፡ በዛብኽ ፡ ጦር ።

ተልባ ፡ ማሳ ፤ በውስጡ ፡ ብር ፡ ያለበት ፡ ግምጃ ፡ የለበሰ ፡ ገበቴ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ሐና ፡ ቀማኞችን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ የሚካኤል ፡ ታቦት ፡ ነው ፡ ብለ ውታል ።

ተልባ ፡ ተልቢቱ ፤ ተረታዊ ፡ የሴት ፡ ስም ።

ተለዘ ፤ (ትግ ፡ በጣ) ፤ ደከመ ። ጠለሰን ፡ አስተውል ።

ትልዝ ፤ የተለዘ ፡ የደከመ ።

ትልዝ ፡ አለ ፤ ድክም ፡ አለ ፡ ነዲዱ ፡ መብራቱ ።

ተልካሳ ፤—ሰነፍ ፤—ለከሰ ።

ተልከሰከሰ ፤—ረከሰ ፤—ለከሰ ።

ተልኰሰኰሰ ፤—ተላወሰ ፤—ለኰሰ ።

ተለለ ፤ (ጸሊል ፡ ጸለለ ፤ ተንካፈፈ) ፤ ጠለለ ፡ ጠራ ፡ ጥሩ ፡ ኾነ ።

ተለለ ፤ ፈሰሰ ፡ ወረደ ። እንባው ፡ ተለል ፡ አለ ፡ እንዲሉ ።

ተለለ ፤ አመመ ፡ በገረ ፡ አሠመረ ።

ተለል ፤ መትለል ።

ተለል ፡ አለ ፤ መጥለል ፡ ዠመረ ፤ ፈሰሰ ፡ አለ ።

ተለላ ፤ እመም ፡ ገዝም ፡ ቃዳ ።

መትለል ፤ መጥለል ።

መትለያ ፤ መጥለያ ።

አተለለ ፤ (አጽለለ) ፤ አጠራ ፡ አጠለለ ።

አተለለ ፤ አወረደ ፡ አፈሰሰ ።

አትላይ ፤ ያተለለ ፡ የሚያተል ፤ አጥላይ ።

ማትለል ፤ ማጥለል ።

ማትለያ ፤ ማጥለያ ።

ተለለ ፤ (ጸልሎ ፡ ጸለለ ፤ አጠለመ ። ተጸለለ ፤ ጠለመ) ፤ አላዋቂ ፡ ኾነ ።

ተላላ ፤ (ጽሉል) ፤ ድል ፡ ሞኝ ፡ ደንቈሮ ፡ ዝንጉ ። (ተረት) ፤ የዝንብ ፡ ተላላ ፡ ካንድ ፡ በሬ ፡ ደም ፡ ይቀርባታል ።

ተላሌ ፤ የተላላ ፡ ወገን ። የተደበቀን ፡ ዕቃ ፡ ማግኘት ፡ ያልቻለውን ፡ ሰው ፤ ተላሌ ፡ ሆይ ፡ እንዲል ፡ የማሲንቆ ፡ ምት ።

ተለል ፡ ተለል ፡ አለ ፤ ተላላ ፡ ሞኞሞኝ ፡ ኾነ ።

(ታለለ) ፤ ዕብ ፡ ታላል) ፤ **አታለለ** ፤ ደለለ ፡ ሸነገለ ፡ አሞኘ ፡ አዘነጋ ፡ አቈለ ፡ በነገር ፡ በስብከት ፡ (ኤር፳ ፡ ፯ ። ዘካ፲፫ ፡ ፭) ። በውስጥ ፡ ሞቃ ፡ እበት ፡ ዐመድ ፤ በላይ ፡ ማር ፡ ቅቤ ፡ ዶቄት ፡ አድርጎ ፡ ሼጠ ፡ ለወጠ ።

አታላይ ፤ ያታለለ ፡ የሚያታልል ፤ ደላይ ፡ ሸንጋይ ፡ ዋሾ ፡ ቀጣፊ ፡ መልቲ ። አታላይ ፡ ሴባ ፡ እንዲሉ ።

አታላዮች ፤ የሚያታልሉ ፤ ሸንጋዮች ፡ መልቲዎች ፡ (ሮሜ፮ ፡ ፴) ።

አታላይነት ፤ አታላይ ፡ መኾን ።

ማታለል ፤ መደለል ፡ መሸንገል ፡ ማሞኘት ፡ ማቈል ።

ማታለያ ፤ መደለያ ፡ መሸንገያ ፡ ማሞኛ ፡ የተንኰል ፡ ዘዴ ።

ተታለለ ፤ ተደለለ ፡ ተሸነገለ ፡ ተሞኘ ፡ ቈለ ፡ ደነቈረ ፡ ዘነጋ ፡ (ኤር፵ ፡ ፮ ። ፭ጢሞ ፡ ፪ ፤ ፲፬) ።

ተታላይ ፡ (ዮች) ፤ የሚታለል ፡ የሚደለል ፤ ተደላይ ።

ተታላይነት ፤ ተታላይ ፡ መኾን ፤ ሞኝነት ፡ ንዝህላልነት ።

መታለል ፤ መደለል ፡ መሞኘት ፡ መዘንጋት ፡ (ኢሳ፶ ፤ ፯ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ።

መታለል ፤—በደም ፡ መነከር ፤—ዐለለ ።

መታለያ ፤ መደለያ ፣ መሞኛ ።

መታለያ ፤ የቀበሌ ፣ ስም ፤ ባዲስ ፣ ዓለም ፣ አቅራቢያ ፣ ያለ ፣ ያቦ ፣ አጥቢያ ። በጋልኛ ፣ ግን ፣ መታላ ፣ ይባላል ፤ ቀጥታ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ታለለ ፤—በደም ፣ ተነከረ ፤—ዐለለ ።

ተለመ ፤ (ተሊም ፣ ተለመ) ፤ ዕርሻ ፣ ዝመረ ፣ ዐረሰ ፣ አንድ ፣ ፈር ፣ አወጣ ፣ ቦደነ ፣ ገመሰ ።

ተለመ ፤ ያዘ ፣ ለከፈ ፣ በሽታ ፣ ሰውን ።

ተላሚ ፣ (ዎች) ፤ የተለመ ፣ የሚተልም ፤ ዝማሪ ፣ ዐራሽ ።

ተለማ ፤ ትልሚያ ፤ ዝመራ ።

ትለም ፤ ጠሚት ፣ ዕርፍና ፣ ሙጭ ፣ የሚኾን ፣ ዕንጨት ፣ ወንዴና ፣ ሴቴ ።

ትለም ፤ የቅርብ ፣ ወንድ ፣ ትእዛዝ ፣ አንቀጽ ።

መትለም ፤ መዝመር ፣ ማረስ ፣ መግመስ ።

መትለሚያ ፤ መዝመሪያ ፣ ጊዜ ፣ ስፍራ ።

ተላለመ ፤ ዝማመረ ፣ ዐራረሰ ።

መተላለም ፤ መዝግመር ።

አስተለመ ፤ አዝመረ ፣ አሳረሰ ፣ አስገመሰ ።

አስተላሚ ፤ ያስተለመ ፣ የሚያስተልም ፤ አሳራሽ ።

ማስተለም ፤ ማዝመር ፣ ማሳረስ ።

ማስተለሚያ ፤ ማዝመሪያ ፣ ማሳረሻ ።

ተተለመ ፤ ተዝመረ ፣ ታረሰ ፣ ተዐደነ ፣ ተገመሰ ።

ተተለመ ፤ በበሽታ ፣ ተያዘ ፣ ተለከፈ ።

ተተላሚ ፤ የሚተለም ፤ ተዝማሪ ።

ትልም ፤ የተተለመ ፤ ዝምር ፣ ፈር ፣ ቡደን ።

ትልሞች ፤ ፈሮች ፣ የርሻ ፣ ውጥኖች ፣ (ኢዮ ፴፩ ፡ ፴፰) ።

መተለም ፤ መዝመር ፣ መታረስ ።

መተለሚያ ፤ መዝመሪያ ፣ መታረሻ ፣ ረፋድ ፣ ጊዜ ።

ተታለመ ፤ ተዝመረ ።

መታለም ፤ መዝመር ።

መታለሚያ ፤ መዝመሪያ ፣ (መትለሚያ) ።

አታለመ ፤ አዝመረ ፣ ፈር ፣ አዋጣ ።

አታላሚ ፤ ያታለመ ፣ የሚያታልም ።

ማታለም ፤ ማዝመር ፣ ፈርን ።

ማታለሚያ ፤ ማዝመሪያ ።

አተላለመ ፤ አዝማመረ ፣ አስተራረሰ ።

ማተላለም ፤ ማዝግመር ፣ ማስተራረስ ።

አተላለም ፤ አስተራረስ ፤ መትለም ።

ታልማ ፤–ታናሽ ፣ አንዠት ፤–ለማ ።

ትሎማ ፤ የጋላ ፣ ስምና ፣ ነገድ ።

ትላንት ፤ ትናንት ፤ (ትማልም) ፤ ንኡስ ፣ አገባብ ። የጊዜ ፣ ስም ፤ የዛሬ ፣ ተቀዳሚ ፣ ቀን ።

ትላንትና ፤ ትናንትና ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ ና ፣ ምእላድ ፣ ነው ። (ግዋም) ፤ ትላንትና ፣ ማታ ፤ ዛሬ ፣ ሌሊት ፣ በልሜ ፤ ምሰሶው ፣ ተሰብሮ ፣ እባሕር ፣ ላይ ፣ ቆሜ ። ከ ፣ መነሻ ፣ ጕኖት ፣ በዘርፍነት ፣ ሲነገር ፤ ከትላንት ፣ በስቲያ ፣ ከትላንት ፣ ወዲያ ፣ ይላል ። እስተን ፣ ተመልከት ።

ተለቀ ፤—ትልቅ ፣ ኾነ ፤—ላቀ ።

ታላቅ ፤ ትልቅ ፤—የበለጠ ፤—ላቀ ።

ተሊስ ፤ የሰሌን ፣ ምንጣፍ ።

ቱልት ፣ (ዶች) ፤ የቅጠል ፣ ስም ፤ ሥሩ ፣ ዐለንጋ ፣ የሚመስል ፣ ማላጋ ፣ ቅጠል ። ጠንዳዮች ፣ የምድር ፣ ዐለንጋ ፣ ይሉታል ።



ቱልት ፣

ትሎት ፤ (ተለወ ፣ ትልወት) ፤ መጻሪያ ፤ ሴት ፣ ልጅ ፣ ስትዳር ፣ አባቷ ፣ የሚሰጣት ፣ እሽክር ፣ ገረድ ፣ ወንድና ፣ ሴት ፣ አገልጋይ ፣ ከብት ፣ ተከትሏት ፣ ስለሚኼድ ፣ ትሎት ፣ ተባለ ፤ ትርጓሜውም ፣ መከተል ፣ ነው ። (የፈርዖን ፣ ፀዋጅ) ፤ ወንድ ፣ ወንዱ ፣ ለሞት ፤ ሴት ፣ ሴቱ ፣ ለትሎት ።

ተለተለ ፤ (ትግ ፣ ተልተለ ፤ ሸደሸደ) ፤ ፈታ ፣ ተረተረ ፣ መዘዘ ፤ ያዲስ ፣ ልብስን ፣ ማግ ፣ ከድር ፣ ለየ ፣ አወጣ ። ሥሩ ፣ ተለለ ፣ ነው ።

ተለተለ ፤ ቀደደ ፣ ሠነጠቀ ፣ በጣ ፣ ቅሪላን ፣ ጕሮን ፣ ፈትን ። ዘለዘለንና ፣ ተነተነን ፣ እይ ።

ትልታይ ፣ (ዮች) ፤ የተለተለ ፣ የሚተለትል ፤ ተርታሪ ፣ ሠንጣቂ ።

ትልተላ ፤ ትርተራ ፣ ልየታ ፣ ሥንጠቃ ።

መተልተል ፤ መፍታት ፣ መተርተር ፣ መቅደድ ፣ መሠንጠቅ ፣ መብጣት ፣ መለየት ።

መተልተያ ፤ መፍቻ ፣ መተርተሪያ ፣ መሠንጠቂያ ፣ መቅደጃ ፣ መርፌ ፣ ቢላዋ ።

ተላተለ ፤ ፈታታ ፣ ቀዳደደ ፣ ለያየ ።

መተላተል ፤ መቀዳደድ ፣ መለያየት ።

አስተለተለ ፤ አስፈታ ፣ አስተረተረ ፣ አስመዘዘ ፣ አስለየ ።

አስተለተለ ፤ አስቀደደ ፡ አሠነጠቀ ፡ አስ በጣ ።

አስተልታይ ፤ ያስተለተለ ፡ የሚያስተለትል ።

ማስተልተል ፤ ማስቀደድ ፡ ማስተርተር ፡ ማስለየት ።

ማስተልተያ ፤ ማስተርተሪያ ፡ ማስቀደጃ ፡ ማሠንጠቂያ ፡ ስለት ።

ተተለተለ ፤ ተፈታ ፡ ተተረተረ ፡ ተመዘዘ ፡ ተለየ ፡ ወጣ ።

ተተለተለ ፤ ተቀደደ ፡ ተሠነጠቀ ፡ ተበጣ ።

ትልትል ፤ የተተለተለ ፤ ትርትር ፡ ሽማ ፤ ብጥ ፡ ቅድ ፡ ሥንጥቅ ፡ ገላ ።

ትልታይ ፤ ከድር ፡ የወጣ ፡ ማግ ፤ ከማግ ፡ የተለየ ፡ ድር ።

ትልትላት ፤ ብጥታት ፡ ሥንጥቃት ።

አተላተለ ፤ አተራተረ ፡ አማዘዘ ።

አተላተለ ፤ አቃደደ ፡ አሠናጠቀ ፡ አባጣ ።

ማተላተል ፤ ማተራተር ፡ ማቃደድ ።

አተላተል ፤ አተራተር ፤ መተርተር ።

ቱልቱላ ፤ ከቀንድ ፡ ከንሓስ ፡ የተበጀ ፡ ታናሽ ፡ የድምፅ ፡ መሣሪያ ፡ ውስጠ ፡ ክፍት ፤ ሰው ፡ መጥሪያ ፡ መሰብሰቢያ ።



ቱልቱላ ፡

ታሞ ፤—ተራራ ፤—ተመመ ።

ትም ፡ አለ ፤—ቀጎልቀጎል ፡ ሮጠ ፤—ተመመ ።

ቱምቢ ፤ የግንብ ፡ ጠርዝና ፡ ማእዘን ፡ ያዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ማስተካከያ ፡ ብረት ፤ ወይም ፡ ርሳስ ፡ ጫፉ ፡ በቀጪን ፡ ገመድ ፡ የተያዘ ።



ቱምቢ ፡

ቴምብር ፤ ማኅተም ፤ የማኅተም ፡ ሥዕል ፡ የዓለም ፡ ነገሥታት ፡ በደብዳቤ ፡ ማኅደር ፡ ላይ ፡ የሚ ለጥፉት ። ቴምብር ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ነው ።

ቴምብሮች ፤ ኹለትና ፡ ከኹለት ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ብዙዎች ።

ትምቡሼ ፤—ልዝብ ፤—ትንቡሼ ።

ተመግ ፤—ልል ፡ ኾነ ፤—ተመከ ።

ተማጠነ ፤—ተጠጋ ፤—ዐጠነ ።

ተመከ ፤ ላላ ፡ ተሰጐደ ፡ ተሠረጐደ ፤ ሥዕል ፡ ተቀበለ ፡ ታተመ ።

ትምክ ፤ የተመከ ፤ ልል ፡ ስጕድ ፡ ሥርጕድ ።

ትምክ ፡ አለ ፤ ሥርጕድ ፡ አለ ፤ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፤ ትክክልነትን ፡ ዐጣ ።

አተመከ ፤ ሰጐደ ፡ ሠረጐደ ።

አትመከመከ ፤ አድበሰበሰ ፤ ሳያሰማ ፡ ተና ገረ ። መከመከን ፡ እይ ።

ማትመከመክ ፤ ማድበስበስ ።

ተትመከመከ ፤ ተድበሰበሰ ፡ ነገሩ ፤ እሳት ፡ ጨሰ ፡ ሳይነድ ፡ እንደ ፡ መቅረት ።

ትምክምክ ፤ የተትመከመከ ፤ ድብስብስ ።

ትምክምክ ፡ አለ ፤ ተትመከመከ ።

መትመከመክ ፤ መድበስበስ ።

ተመከ፤–በንድ፡ነገር፡ታመነ፤–(መክ)።

ተመከነ፤–ተደረገ፡ ምክንያቱ፤–(መ ከን) ።

ተመመ ፤ (ደመመ) ፤ ድም ፡ ድም ፡ አለ ፤ ጮኸ ፡ ናረ ፡ ተሰማ ፡ በሩቅ ፡ ነጋሪቱ ፡ ጕርፋ ፡ (ኤርፀፅ ፡ ፀፅ ። ሕዝፃፒ ፡ ፪) ።

ተመመ ፤ ተጨረሰ ፤ ተቁለቁለ ።

ተማሚ ፤ የሚተም ። ዐማ ፡ ብለኸ ፡ ተማ ማን ፡ አስተውል ።

ተመማ ፤ ጩኸት ፡ ንረት ፡ (ኢዮፀ፯ ፡ ፪) ።

መትመም ፤ መጮኽ ፡ መናር ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፀ) ።

መትመሚያ ፤ መጮኺያ ፡ ዘፈን ፡ እስከ ስታ ፡ ክረምት ።

አተመመ ፤ አጮኸ ፡ አናረ ።

አትማሚ ፤ ያተመመ ፡ የሚያተም ፤ ከበሮ ፡ መቺ ።

አታሞ ፡ (ዎች) ፤ የከበሮ ፡ ቁጥ ፡ አማሪት ።

አታሞ ፤ አፉ ፡ በለፋ ፡ ቁዳ ፡ የተለጕመ ፡ (የታሰረ) ፡ እንስራ ፡ ጎንቦ ።

አታሞ ፡ ዋሻ ፤ እረኞች ፡ ደበሎ ፡ ጠቅለው ፡ በውስጡ ፡ ሲመቱ ፡ እንደ ፡ አታሞ ፡ የምትጮኽ ፡ ዋሻ ። ይህችውም ፡ በሳይኛው ፡ ወግዳ ፡ ክፍል ፡ ጐሽ ፡ ውሃ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ትገኛለች ።

ታሞ ፤ በመርሐ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ተራራ ፡ ባለዋሻ ።

አስተመመ ፤ አስጮኸ ።

ትም ፡ አደረገ ፤ በፍጥነት ፡ ፈጸመ ፡ ጨረሰ ፡ እኽልን ፡ ገንዘብን ።

ትም ፡ አለ ፤ ቍልቍል ፡ ኼደ ፡ ወረደ ፡ ሮጠ ።

አተማመም ፤ አጨጫጨ ፤ መትመም ።

ተማም ፤ (ዐረ) ፤ ልክ ፡ ትክክል ፡ ፍጹም ።

ተመን ፤ ዘንዶ ፡ (ግእዝ) ።

ተሙን ፤ (ዐረ ፡ ሱሙን) ፤ የገንዘብ ፡ ስም ፤ የዱሮ ፡ መሐልቅ ፡ አላድ ፡ ሳይመጣ ፡ የነበረ ፤ ባንድ ፡ ብር ፡ ኹለት ፡ ይመነዘራል ። የብር ፡ ስምንተኛ ፡ ማለት ፡ ነው ። መሐልቅም ፡ በተሙን ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ ተተካ ፡ ተሙን ፡ ይባላል ። (ማስረጃ) ፡

ተሙን ፡ ተቤሳ ፤ ፩ ፡ መሐልቅ ፡ ካ፩ ፡ ቤሳ ።

ተመናኘ ፤—ያላሳብ ፡ ተዳደለ ፤—ናኘ ።

ተመናሸ ፤—ተዋጋ ፤—መንሸ ።

ተመጻደቀ ፤—በገዛ ፡ አፉ ፡ ተመሰገነ ፤—ጸደቀ ።

ተምር ፡ (ሮች) ፤ የዘንባባ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፤ ጣፋጭ ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ሴቱ ፡ ዘንባባ ። ዕንጨቱም ፡ ፍሬውም ፡ ተምር ፡ ይባላል ።



ተምር ፡

ታምር ፤—ድንቅ ፤—አመረ ።

ተመረኰዘ ፤—ተደገፈ ፤—ምርኵዝ ።

ትምርት ፤—በቁሙ ፤—(ማረ) ።

ተመሰ ፤ ደበሰ ፡ ደመሰ ።

አትመሰመሰ ፤ አድበሰበሰ ፡ አድመሰመሰ ፡ አመቀመቀ ፡ አርበተበተ ።

ማትመስመስ ፤ ማድበስበስ ።

ተትመሰመሰ ፤ ተድበሰበሰ ፡ ተድመሰመሰ ፡ ተርበተበተ ፤ መለስ ፡ ቀለስ ፡ አለ ።

ተመስማሳ ፤ ትምስምስ ፤ የተትመሰመሰ ፡ የሚትመሰመስ ፤ ርብትብት ።

መትመስመስ ፤ መድበስበስ ።

መትመስመሻ ፤ መድበስበሻ ።

ቶማስ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ካሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ አንዱ ።

ተምሸከሸከ ፤—ተበጣጠሰ ፤—(መሸከ) ።

ተምች ፡ (ኞች) ፤ ጥቅር ፡ ትል ፡ በር ፡ ናሴ ፡ የጤፍ ፡ ፀር ።

ተምች ፡ መታ ፤ ብዙውን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ተምች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ደበደበ ፡ ገደለ ።

ቱማታ ፤ የብዙ ፡ ሰው ፡ ጩኸት ፡ ፍጅት ፡ ውካታ ፡ ጫጫታ ።

ቱማታ ፤ የጨበጣ ፡ ውግ ፤ ወግቶ ፡ ማሸቀንጠር ።

ቱማታ ፡ ገዳይ ፤ በቱማታ ፡ የሚገድል ፡ ሐርበኛ ፤ እንዳቶ ፡ በዛብኽ ፡ ያለ ፡ ጨካኝ ፡ ጉበዝ ።

ተመተመ ፤ (ተመመ) ፤ መታ ፡ ለተመ ፡ ገጨ ፡ ወጋ ።

ተመተመ ፤ ደመደመ ፡ አስተካከለ ፡ ልጥፍን ፡ በጭድ ።

ተመተመ ፤ በእጅ ፡ አባበለ ፡ ሕፃንን ፡ በቅሎን ፡ ፈረስን ።

ተመተመ ፤ አበሰለ ፡ አመጠጠ ፡ እሳት ፡ ንፍሮን ።

ተመተመ ፤ ዝም ፡ በል ፡ አትናገር ፡ አለ ። አንዱ ፡ የሥጋ ፡ ቤት ፡ ባልደረባ ፡ ባቡጀዲ ፡ የተሸፈነ ፡ ሥጋ ፡ ሰርቆ ፡ ሲኼድ ፡ ዐጤ ፡ ምኒልክን ፡ እሰገነት ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ቢያያቸው ። አፉን ፡ በእጁ ፡ ተመተመ ፤ እሳቸውም ፡ ዛቁና ፡ ኺድ ፡ አሉት ።

ተመተመ ፤ አረመደ ።

ተምታሚ ፡ (ዎች) ፤ የተመተመ ፡ የሚተመትም ፤ ለታሚ ፡ ደምዳሚ ።

ተምትም ፤ ለትም ፡ ግጭ ።

ተምትሚ ፤ የሰው ፡ ስም ።

ትምተማ ፤ ልተማ ፡ ድምደማ ።

መተምተም ፤ መምታት ፡ መለተም ፡ መግጨት ፡ መውጋት ፡ መደምደም ፡ ማባበል ፡ ማምጠጥ ።

መተምተሚያ ፤ መለተሚያ ፡ መግጫ ፡ መደምደሚያ ፡ ቀንድ ፡ ሉሕ ።

ተማተመ ፤ ለታተመ ።

አስተመተመ ፤ አስመታ ፡ አስለተመ ፡ አስገጨ ፡ አስወጋ ።

አስተመተመ ፤ አስደመደመ ።

ማስተምተም ፤ ማስለተም ፡ ማስገጨት ፡ ማስደምደም ።

ተተመተመ ፤ ተመታ ፡ ተለተመ ፡ ተገጨ ፡ ተወጋ ።

ተተመተመ ፤ ተደመደመ ።

ተተመተመ ፤ ተረመደ ።

ትምትም ፤ የተተመተመ ፤ ልትም ።

ትምትም ፤ በልጥፍና፥ በልስን ፥ መካከል ፥ ያለ ፥ የምርግ ፥ ሥራ ። ጕርሥን ፥ እይ ።

ትምትም ፥ አደረገ ፤ ድም ፥ ድም ፥ አደ ረገ ።

ተተማተመ ፤ ተላተመ ፥ ተጋጨ ፥ ተዋጋ ።

ተተማታሚ ፤ የሚተማተም ፤ ተላታሚ ፥ አውራ ፥ በግ ።

መተማተም ፤ መላተም ፥ መጋጨት ፥ መ ዋጋት ።

መተማተሚያ ፤ መላተሚያ ፥ መዋጊያ ፥ ቀ ንድ ፥ ግንባር ፥ ሜዳ ።

አተማተመ ፤ አላተመ ፥ አጋጨ ፥ አዋጋ ።

አተማተመ ፤ አደማደመ ።

አተማታሚ ፤ ያተማተመ ፥ የሚያተማትም ፤ አላታሚ ፥ አዋጊ ፤ ቲቲቲ ፥ ባይ ፥ እረኛ ።

ማተማተም ፤ ማላተም ፥ ማዋጋት ።

ማተማተሚያ ፤ ማጋጫ ፥ ማዋጊያ ።

ተምተም ፤ ችኰላ ፥ ፍጥነት ፥ ተፍተፍ ።

ተምተም ፥ አለ ፤ ቸኰለ ፥ ፈጠነ ፤ በብዙ ፥ ስፍራ ፥ ፈለገ ፤ አተፈተፈ ።

አተማተም ፤ አለታተም ፤ መተምተም ።

ትማትም ፥ (ሞች) ፤ የተከል ፥ ስም ፤ ክብ ፥ እንክብል ፥ ቀይ ፥ ፍሬ ፤ ወጥ ፥ የሚኾን ፥ ዐረ ግማ ፥ ተክል ፤ ኹለተኛ ፥ ስሙ ፥ ያቡን ፥ ወጥ ፥ ነው ።

(ቶመቶመ) ፤ አቶመቶመ ፤ አጕረመ ረመ ፥ አጕተመተመ ።

አቶምታሚ ፤ ያቶመቶመ ፥ የሚያቶመቱም ፤ አጕረምራሚ ።

ማቶምቶም ፤ ማጕረምረም ።

ማቶምቶሚያ ፤ ማጕረምረሚያ ።

ተነ ፤ (ከነ) ፤ መነሻነትንና ፥ እንድነትን ፥ የሚያሳይ ፥ ደቂቅ ፥ አገባብ ፥ ኹኖ ፥ ከነ ፥ በገባበት ፥ ይገባል ።

ተነከሌ ፤ ርሱ ፥ ተነከሌ ፥ እያንስም ።

ተነከታቴው ፤ ተነመጨረሻው ።

ተነነፍሱ ፤ ሳይሞት ፥ በሕይወት ፥ ሳለ ። የሰከረው ፥ ዓሣ ፥ ተነነፍሱ ፥ ተያዘ ።

ተን ፤ አን ፥ በገባበት ፥ በደጊመ ፥ ቃል ፥ ግስ ፥ መነሻ ፥ እየተነገረ ፥ የመደረግ ፥ ልማድ ፥ ይኾናል ። (ማስረጃ) ፥ በገበገ ፥ ተንበገበገ ፤ በለበለ ፥ ተንበለ በለ ፤ ገደገደ ፥ ተንገደገደ ፤ ነጠበ ፥ ተንጠባጠበ ፤ ደፈደፈ ፥ ተንደፋደፈ ፤ ቀጠቀጠ ፥ ተንቀጠቀጠ ፤ (ቀለቀለ) ፥ ተንቀለቀለ ፤ ሰረሰረ ፥ ተንሰረሰረ ።

ተኛ ፤ ተጋደመ ፥ ተዘረጋ ፥ ተዘረረ ፤ ጐኑ ፥ ምድር ፥ ነካ ፥ (ፎሳሙ ፥ ፫ ፥ ፱ ። ፩ነገ ፥ ፲፱ ፥ ፩ ፥ ፯) ። (ተረት) ፤ ቢተኙ ፥ ነገር ፥ ያገኙ ፤ ቢነሡ ፥ ነገር ፥ ይረሱ ። ቢተኙ ፥ ነገር ፤ ቢቈዱ ፥ አገር ።

ተኛ ፤ ዐረፈ ፥ ሞተ ፥ (፩ቆሮ ፥ ፲፭ ፥ ፮ ፥ ፲፰) ።

ተኛ ፤ በግብር ፥ ዐወቀ ፥ ተገናኘ ፥ ሴትን ። (ግጥም) ፤ ካንተ ፥ ተኝታ ፥ ሌላ ፥ ታማራት ፤ በል ፥ ተነሣና ፥ በዱላ ፥ በላት ።

ተኛ ፤ የቅርብ ፥ ወንድ ፥ ትእዛዝ ፥ አንቀጽ ፤ ተጋደም ፥ እንቅልፍ ፥ ይውሰድኽ ፥ (ፎሳሙ ፥ ፫ ፥ ፯ ፥ ፱) ።

መተኛት ፤ መኛት ፤ መጋደም ፥ መዘረር ፥ (ዮሐ፲፩ ፥ ፲፫) ።

መተኛት ፤ ከሴት ፥ መገናኘት ፥ (ዘፍ፴፬ ፥ ፯) ።

መተኛ ፤ መኝታ ፤ መጋደሚያ ፥ ዐልጋ ፥ መደብ ፥ ቄጥ ፥ ምንጣፍ ፥ ማታ ።

መኝታ ፥ ቤት ፤ የሚተኛበት ፤ የመኝታ ፥ ቤት ። የላይኛው ፥ በበቂነት ፤ ይህ ፥ በቅጽልነትና ፥ በዘርፍነት ፥ መነገሩን ፥ አስተውል ።

አተኛ ፤ አስተኛ ፤ አጋደመ ፥ (መክ፭ ፥ ፲፪) ።

አስተኚ ፤ ያስተኛ ፥ የሚያስተኛ ፤ አንጣፊ ፥ ጋራጅ ፥ አጋዳሚ ።

አስተኚነት ፤ አስተኚ ፥ መኾን ።

ማስተኛት ፤ ማጋደም ።

ማስተኛ ፤ ማጋደሚያ ፥ ጊዜ ፥ ስፍራ ።

ተተኛኛ ፤ ተዋደቀ ፤ በግብረ ፥ ሥጋ ፥ ተገ ናኘ ፥ ተዋወቀ ።

ትኝት ፤ ረብ ፥ ጋደም ።

ትኝት ፥ አለ ፤ ውድቅ ፥ አለ ።

ተኝቶ ፤ ተጋድሞ ፥ ተዘርሮ ። (ተረት) ፤ የሰው ፥ በልቶ ፥ አያድሩም ፥ ተኝቶ ።

አተኛኘት ፤ አስተኛኘት ፤ አገዳደም ፥ መተኛት ።

ተኛ ፤ (ዊ) ፤ በስም ፥ ማፍ ፥ እየታከለ ፥ ወገን ፥ ቅጽልነትን ፥ ያሳያል ። (ማስረጃ) ፥ ገበያ ፥ ገበያተኛ ፤ ዋና ፥ ዋኝተኛ ፤ ኅያ ፥ ኅያተኛ ፤ ነገር ፥ ነገረተኛ ፥ ቀለብ ፥ ቀለብተኛ ። ምስጢሩም ፤ ሲሠራ ፥ የዋለ ፥ የኖረ ፥ ማታ ፥ መጋደሙን ፥ መጨረሻ ፥ ዕረፍቱን ፥ (ሞቱን) ፥ ያሳያል ። ብዙ ፥ ጊዜም ፥ ኛ ፥ ከተ ፥ እየተለየ ፥ ብቻውን ፥ ይነገራል ፤ ኛን ፥ ተመ ልከት ።

ቱኒ ፤ ፈስ ። ዘሩ ፥ ተነነ ፥ ነው ።

ቱኒ ፤ ፈሪ ፥ ቡከን ።

ቱኒያም ፤ የቱኒ ፥ ባሉቱኒ ፤ ፈሳም ።

ትን ፤—ባፍንጫ ፥ መውጣት ፤—ተ ነነ ።

ተነባ ፤ ተነበየ ፤—ትንቢት ፥ ተና ገረ ፤—(ነበየ ፤ ነባ) ።

ቱንቢ ፤—አድማስ ፤—ቱምቢ ።

ትንባኾ ፤ የተከል ፣ ስም ፤ ሰው ፣ ኹሉ ፣ ልጥልጡን ፣ ባፉ ፣ የሚጮርሠው ፣ ሥንቅኑን ፣ ባፍንጣው ፣ የሚምገው ፣ ጪሱን ፣ የሚጠጣው ፣ ቅጠል ። ባረብኛ ፣ ትንባክ ፣ ይባላል ።

ትንባኺም ፤ ትንባኾ ፣ ጠጪ ፣ ባለትንባኾ ፤ ሱረታም ። አምልኮ ፣ ባዕድ ፣ ከሌለበት ፣ ትንባኾ ፣ መጠጣት ፣ አያስኬንንም ።

ትንቢለል ፤—የሴት ፣ ስም ፤—ቦለለ ።

ተንቤን ፤ በትግሬ ፣ ክፍል ፣ ያለ ፣ አገር ።

ተንቤን ፤ በተንቤን ፣ ውስጥ ፣ የሚሠራ ፣ ቀይ ፣ ቄርበት ፣ ነት ።

ተንቤኔ ፣ (ኖች) ፤ የተንቤን ፣ ሰው ፣ የተንቤን ፣ ተወላጅ ፤ ትግሬ ።

ተንበረከ ፤— ያዲስ ፣ ግንብ ፣ ል ባስ ፤—በረከ ።

ትንቡሼ ፤—ድንቡሎ ፤—በሸበሸ ።

ተንበሸበሸ ፤—ተንቀባረረ ፤—በሸበሸ ።

ትንቢት ፤—ንግርት ፤—(ነበየ) ፤ ተነ በየ ።

ትናጋ ፤ ላንቃ ፣ ያፍ ፣ ውስጥ ፣ ላይኛው ፣ ክፍል ፣ (ኢዮኤ ፣ ፲፫ ። መዝ፻፴፮ ፣ ፮ ። ሰቈ፬ ፣ ፬ ። ሕዝ ፣ ፳፮) ።

ትናግ ፤ (ስናግ ፣ ስናቅ ። ትግ ፣ ትንሐግ) ፤ ከጕረሮ ፣ ወደ ፣ ሰርን ፣ የትንፋሽ ፣ መውጣ ፣ ኹለት ፣ ቀዳዳ ። ተና ፣ ሰ ፣ ገና ፣ ቀ ፣ መወራረሳቸውን ፣ ልብ ፣ አድርግ ።

ተንገችገች ፤—ዘከዘከ ፣ አለ ፤—(ገች ገች) ።

ተንክ ፤ አተንክ ፤ የውሃ ፣ ገበሎ ።


ተንክ ፤ ሐሩር ፣ ፈል ፣ አስራቦ ፣ ሰውን ፣ የሚነድፍበት ፣ ጊዜ ። ጠንቅን ፣ እይ ።

አተንክ ፣ (ኮች) ፤ ፈጣን ፣ ክፉ ፣ ጠንቀኛ ፣ ተንኰለኛ ።

ታኺካ ፣ (ዎች) ፤ ጋዝ ፣ ዘይት ፣ ነፍት ፣ ቤንዚን ፣ ሌላም ፣ ቅባት ፣ በያይነቱ ፣ ከውጭ ፣ አገር ፣ የሚመጣበት ፣ ሥሥ ፣ ቄርቄሮ ። ትንሹ ፣ ጣሳ ፣ ይባላል ።

ታኺካ ፤ የወርቅ ፣ ሰሌዳ ፣ (ዘዐሸጭ ፣ ፴፮ ፣ ፴፰) ።

ታንኳ ፣ (ዎች) ፤ ከቀርከሓና ፣ ከሸን በቆ ፣ ከደንገል ፣ የተበጀ ፣ የባሕር ፣ መንገደኛ ፣



ታንኳ ፣

በላዩ ፣ ተቀምጦ ፣ የሚሻገርበት ፣ (ማቴ፱ ፣ ፳፩ ፣ ፳፪) ። ፍልኳንና ፣ ጀልባን ፣ አስተውል ።

ታንክ ፣ (ኮች) ፤ የመር ፣ መሣሪያ ፣ መኪና ፣ በጦርነት ፣ ሰዓት ፣ ብዙ ፣ ጥይት ፣ የሚተኵስ ፣ የዐረር ፣ ጋን ። ባ፲፱ኛው ፣ ሴክል ፣ በትልቁ ፣ ጦርነት ፣ ጊዜ ፣ ያወጡት ፣ እንግሊዝና ፣ ፈረንሳይ ፣ ናቸው ፣ ይባላል ።

ታንከኛ ፣ (ኞች) ፤ ታንክ ፣ ነጂ ፣ ባለታንክ ፤ ተኳሽ ።

ተንኰለ ፤ (ጠነቈለ) ፤ መጥፎ ፣ ሠራ ፣ አደረገ ፣ በረቂት ፣ (ግብ ፣ ሐዋ፮ ፣ ፲፱) ።

ተንኰል ፤ ክፉ ፣ ጥበብ ፣ ምክር ፣ ደባ ፣ (ማር፯ ፣ ፳፪) ።

ተንኰሉ ፤ የሰው ፣ ስም ፤ ሴት ፣ በባሏ ፣ ቤት ፣ መኖር ፣ ሳትፈልግ ፣ ልጅ ፣ የወለደች ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ ተንኰሉ ፣ ትለዋለች ፤ የሉ ፣ ዝርዝርነት ፣ ፈጣሪን ፣ ያያል ።

ተንኰለኛ ፣ (ኞች) ፤ ጥበበኛ ፣ መሠሪ ፣ ሰው ፤ መኼጃው ፣ የማይታወቅ ፣ እባብ ።

ተንኰለኛነት ፤ ተንኰለኛ ፣ መኾን ።

ተንኰለ ፣ ቢስ ፤ ተንኰሉ ፣ አጥፊ ፣ ጉጂ ፣ ኖኾን ።

ትንኰላ ፤ የተንኰል ፣ ሥራ ፣ ክፋት ።

አስተንኰለ ፤ ተንኰል ፣ አስተማረ ፣ አሠራ ።

ተተንኰለ ፤ ኾነ ፣ ተደረገ ፣ ተንኰሉ ፣ ልማዱ ፣ ግን ፣ እንደ ፣ መዋመሪያው ፣ አድራጊነት ፣ ነው ፣ (ዘፍ፴፩ ፣ ፮ ። ዘዳ፲፱ ፣ ፲፭) ።

ተተናኰለ ፤ ተጣላ ፣ ጐዳ ፣ ተጠናወተ ።

ተተናኳይ ፣ (ዮች) ፤ የተተናኰለ ፣ የሚተናኰል ፤ ተጠናዋች ።

ተተናኳይነት ፤ ተተናኳይ ፣ መኾን ።

መተናኰል ፤ መጣላት ፣ መጠናወት ።

መተናኰያ ፤ መጭኛ ፣ መጠናወቻ ።

ተተነኳኰለ ፤ ተንኰል ፣ ተሠራራ ፣ ተጐዳዳ ።

ተተነኳኳይ ፤ የተተነኳኰለ ፣ የሚተነኳኰል ።

መተነኳኰል ፤ መጐዳዳት ።

መተነኳኰያ ፤ መጐዳጃ ።

አተነኳኰለ ፤ አጐዳደ ፤ መተናኰል ።

ተንከራ ፤ ጠንካራ ፣ ዕንቊ ፣ (ግእዝ) ።

ተነከረ ፤ ጠነከረ ።

ተነከረ ፤—እውሃ ፣ ገባ ፤—ነከረ ።

አስተነከረ ፤ አስጠነከረ ፤ መረመረ ፣ አስረገጠ ፣ ወሬን ፣ ነገርን ። ተና ፣ ጠ ፣ ተወራራሽ ፣ መኾናቸውን ፣ አትርሳ ።

አስተንካሪ ፤ ያስተነከረ ፣ የሚያስተነክር ፤ ነገር ፣ አስረጋዊ ።

ማስተንከር ፤ ማስረገጥ ።
ማስተንከሪያ ፤ ማስረገጫ ።
መስተንከሪያ ፤ (መስከንተሪያ) ፤ እንደ ፡ መነጽር ፡ ያለ ፡ የምድር ፡ መመርመሪያ ፡ የፊት ፡ መሸፈኛ ።
ተንኰሰ ፤ (ነከሰ) ፤ በቀላል ፡ መታ ፡ ነካ ፡ ለኰፈ ።
ተንኳሽ ፡ (ሾች) ፤ የተንኰሰ ፡ የሚተንኰስ ፤ ለኳፊ ።
ተንኳሽነት ፤ ተንኳሽ ፡ መኾን ።
ትንኳሽ ፡ (ሾች) ፤ የቁላ ፡ ቊጣጭ ፡ በነከሰ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚያንገበግብ ።
ትንኰሳ ፤ ልኰፋ ፡ ንክሻ ።
መተንኰስ ፤ መለኰፍ ፡ መንካት ።
መተንኰሻ ፤ መለኰፊያ ፡ መንኪያ ።
ተነኳኰሰ ፤ ለኳኰፈ ።
መተነኳኰስ ፤ መለኳኰፍ ።
አስተነኰሰ ፤ አስለኰፈ ፡ አስነካ ።
ማስተንኰስ ፤ ማስለኰፍ ፡ ማስነካት ።
ተተነኰሰ ፤ ጥቂት ፡ ተመታ ፡ ላመል ፡ ተለኰፈ ፡ ተነካ ።
ትንኰስ ፤ የተተነኰሰ ፡ የተለኰፈ ፤ ልኰፍ ።
ትንኰስ ፡ አደረገ ፤ ተነኰሰ ።
ተተናኰሰ ፤ ተላኰፈ ፡ ተናካ ።
መተናኰስ ፤ መላኰፍ ።
አተነኳኰሰ ፤ አለኳኰፍ ፤ መተንኰስ ።
ተነነ ፤ (ተኒን ፡ ተነ) ፤ በነነ ፡ ጨሰ ፡ ተበተነ ።
ተናኝ ፤ የሚተን ፤ በናኝ ።
ተን ፤ የጉም ፡ የጪስ ፡ ብናኝ ፡ (ግእዝ) ። ቱኒን ፡ እይ ፤ የዚህ ፡ ዘር ፡ ነው ።
መትነን ፤ መብነን ፡ መጨስ ።
መትነኛ ፤ መብነኛ ፡ መጨሻ ።
ትን ፤ ብን ፡ ባፍንጫ ፡ መውጣት ።
ትን ፡ አለ ፤ ብን ፡ አለ ፤ ወደ ፡ ስናቅ ፡ ወጣ ፡ ሰረነቀ ፡ ዐነዘዘ ፡ ትንፋሹ ፡ መጠጡ ።
ትንታ ፤ ብንታ ፡ ንዛዥ ።
ትንኝ ፡ (ኞች) ፤ ትንንያ) ፤ የተንቀሳ



ትንኝ ፡

ቃሽ ፡ ስም ፤ ሲኼድ ፡ በክንፍ ፡ የሚተን ፡ ቊጣጭ ፡ የሚያሸልና ፡ ከዚያም ፡ የሚበልጥ ፡ (ማቴ፳፫ ፡ ፳፬) ። ትንኝም ፡ ለሆዱ ፡ ዝኆንም ፡ ለሆዱ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወረዱ ፡ እንዲሉ ።
ትንንን ፡ አለ ፤ እንደ ፡ ትንኝ ፡ ሮጠ ፡ ሕፃኑ ።
አተነነ ፤ አበነነ ፡ አጨሰ ።
አትናኝ ፤ ያተነነ ፡ የሚያተን ፤ አብናኝ ።
ተኖ ፤ በኖ ፡ ጨሰ ፡ ተበትኖ ። ሰይጣን ፡ እንደ ፡ ጪስ ፡ ተኖ ፡ እንደ ፡ ጉም ፡ በኖ ፡ ጠፋ ።
አተናነን ፤ አበናነን ፤ መትነን ።
ትናንት ፤ ትናንትና ፤ ትላንት ፤ ትላንትና ።
ተነሣ ፤—ብድግ ፡ አለ ፤—ነሣ ።
ተንሣይ ፤—ትንሣኤ ፤—ነሣ ።
ተነፈገ ፤—ገማ ፤—ነፈገ ።
ተነፈገ ፤—ተሠሠተ ፤—ነፈገ ።
ትንፋግ ፤—መጥፎ ፡ ሽታ ፤—ነፈገ ።
ትንፋገን ፤—ወረዘት ፤—ነፈገ ።
ተነፈሰ ፤—እፎይ ፡ አለ ፤—ነፈሰ ።
ታናሽ ፤ ትንሽ ፤—በቁሙ ፤—አነሰ ።
ተናሸረ ፤—ተማረረ ፤—ነሸረ ።
ተንታ ፤ በወሎ ፡ ክፍል ፡ ያለ ፡ አገር ።
ትንታግ ፤—ክፋይ ፤—ተገተገ ።
ተነተነ ፤ (ነተነ ፤ ተንተነ) ፤ ለየ ፡ ከፈለ ፡ መደበ ፡ ደለደለ ፡ ቈነነ ፡ ዐደለ ። ተለተለ ንና ፡ ሰነሰነን ፡ ሸነሸነን ፡ ተመልከት ።
ተንታኝ ፡ (ኞች) ፤ የተነተነ ፡ የሚተንትን ፤ ከፋይ ፡ ዐዳይ ።
ትንተና ፤ ልየታ ፡ ከፈላ ፡ ምደባ ።
መተንተን ፤ መከፈል ፡ መመደብ ፡ ማደል ።
መተንተኛ ፤ መከፈያ ፡ ማደያ ፡ እጅ ፡ ርዐ ፡ መቀነን ፡ ካራ ።
ተናተነ ፤ ለያየ ፡ ከፋፈለ ።
መተናተን ፤ መለያየት ፡ መከፋፈል ።
አስተነተነ ፤ አስለየ ፡ አስከፈለ ፡ አስመደበ ፡ አስደለደለ ፤ አስቈነነ ፡ አሳደለ ።
አስተነተነ ፤ (አስተሐመመ) ፤ ተጋ ፡ ዐሰበ ፤ ነገርን ፡ በልቡ ፡ አወጣ ፡ አወረደ ፡ ጥቂቱን ፡ ብዙ ፡ ለማድረግ ፡ ለማብቃቃትና ፡ ሥራን ፡ ኹሉ ፡ ለማከናወን ።
አስተንታኝ ፡ (ኞች) ፤ ያስተነተነ ፡ የሚያስተነትን ፤ ትጉህ ፡ ዐሳቢ ፡ እንቅልፍ ፡ የለሽ ፤ የገዳም ፡ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ መጋቢ ።
ማስተንተን ፤ ማስለየት ፡ ማስከፈል ፡ ማስመደብ ፡ ማሰብ ።
ማስተንተኛ ፤ ጊዜ ፡ ስፍራ ።

ተተንተን ፤ ተለየ ፥ ተከፈለ ፥ ተመደበ ፥ ተደለደለ ፤ ተቈነነ ፥ ታደለ ።

ትንትን ፤ የተተነተነ ፥ የተከፈለ ፤ ክፍል ፍል ።

ትንትናት ፤ የመተንተን ፥ ዅኔታ ።

ተተናተነ ፤ ተጋራ ፥ ተካፈለ ፥ ተከፋፈለ ፤ ተዳረሰ ፥ ተዳደለ ።

ተተናታኝ ፤ የሚተናተን ፥ ተካፋይ ።

መተናተን ፤ መካፈል ፥ መከፋፈል ።

መተናተኛ ፤ መካፈያ ፥ መከፋፈያ ።

አተናተነ ፤ አካፈለ ፥ አከፋፈለ ።

አተናታኝ ፤ ያተናተነ ፥ የሚያተናትን ፤ አ ከፋፋይ ።

ማተናተን ፤ ማካፈል ፥ ማከፋፈል ፥ ማዳ ረስ ።

ማተናተኛ ፤ ማካፈያ ፥ ማከፋፈያ ።

አተናተን ፤ አከፋፈል ፤ መተንተን ።

ተንተራሰ ፤—ራሱ ፥ ተደገፈ ፤—ራሰ ፤ ራሰ ።

ተሣለቀ ፤—አላገጠ ፤—(ሠለቀ) ።

ትሣሥ ፤— የወር ፥ ስም ፤— ታኅሳ ሣሥ ።

ተሠራጨ ፤—ተሰማራ ፤—(ሠረጨ) ።

ተፋ ፤ (ተፍአ) ፤ ምራቁን ፥ በምድር ፥ ላይ ፥ አሳረፈ ፤ እከ ፥ እንትፍ ፥ አለ ፤ ከሆድ ፥ አው ጥቶ ፥ ጣለ ፥ (ዮናኀ ፥ ፪፩) ።

ተፋ ፤ ቀረሸ ፥ አወጣ ፥ አስታወከ ፥ አስመ ለሰ ። (ተረት) ፤ አልጠግብ ፥ ባይ ፥ ሲተፋ ፥ ያድ ራል ። (ምድር ፥ ተፋችው) ፤ አሽቀነጠረችው ፤ ሽቅብ ፥ ወረወረችው ። (ምን ፥ ምድር ፥ ተፋሽ) ፤ አወጣሽ ።

ተፊ ፤ (ተፋኢ) ፤ የተፋ ፥ የሚተፋ ፤ አስ ታዋኪ ።

ተፊታ ፤ የምትተፋ ፥ ሴት ።

መትፋት ፤ መቀርሸት ፥ ማስታወክ ፥ ማስ መለስ ።

መትፊያ ፤ ማስታወኪያ ፥ ወሟት ፥ ስፍራ ።

አስተፋ ፤ (አትፍአ) ፤ አስቀረሸ ፥ አስ ወጣ ።

አስተፋ ፤ በፍጥነት ፥ አስመጣ ፥ አስከፈለ ።

አስተፊ ፤ ያስተፋ ፥ የሚያስተፋ ። (ደም ፥ አስተፈ) ፤ ሊበሉት ፥ የማይገባ ፥ እንጉዳይ ።

አስተፊታ ፤ የምታስተፋ ፥ ሴት ።

ማስተፋት ፤ ማስቀርሸት ፥ ማስዉጣት ።

ማስተፊያ ፤ ማስወጫ ፥ ማስመጫ ።

ቴፌ ፤ የወተት ፥ መናጫ ፥ ቀዳዳ ፥ ውታፍ ፥ በነቀሉት ፥ ጊዜ ፥ በነፋስ ፥ ጎይል ፥ ወተት ፥ ወይም ፥ ቅቤ ፥ የሚተፋ ።

ቲፍ ፤ መተንፈስ ፥ መምላት ፤ ሲተነፍሱ ፥ ባፍንጫ ፥ ርጥበት ፥ ማውጣት ።

ቲፍ ፥ አለ ፤ በትንፋሽ ፥ ድምፅ ፥ አሰማ ፤ ተጠነቀቀ ፥ ፍየሉ ።

ቲፍ ፥ አለ ፤ መላ ፥ ጠም ፥ አለ ፥ ተርፎ ፥ እስኪፈስ ። ቴፈን ፥ እይ ።

ተቲፋ ፤ ተቀረሸ ፥ ወጣ ፥ ተመለሰ ።

ትፍ ፤ (ትፍአ) ፤ የተተፋ ።

ትፍታ ፤ አክታ ፥ ምራቅ ።

እንትፍ ፤ መትፋት ።

እንትፍ ፥ አለ ፤ ተፋ ።

እንትፍታ ፤ እንትፍ ፥ ማለት ፤ ትፍታ ፥ (ኢዮ፱ ፥ ፯) ።

እንትፍ ፥ እንትፍ ፥ አለ ፤ መረቀ ፤ ጥላቻውን ፥ ተወ ።

እንትፍትፍ ፥ አለ ፤ ገዘኒ ፥ ከማሁ ።

ትፋት ፤ (ትፋእ) ፤ ቅርሻት ፥ ምላሽ ፥ (ምሳ ፳፯ ፥ ፲፩ ። ኢሳ፲፱ ፥ ፲፬ ። ኤርማ፳ ፥ ፳፯) ። (ተረት) ፤ ልጅ ፥ የቈሎ ፥ ትፋት ፥ ያምረዋል ።

ትፋታም ፤ ባለትፋት ፤ ቅርሻታም ።

አተፋፍ ፤ አቀረሻሸት ፤ መትፋት ።

ተፊ ፤—ፈጣን ፤—ተፈተፈ ።

ታፋ ፤ ከጭን ፥ በላይ ፥ ከቂጥ ፥ አጠገብ ፥ በስተጉን ፥ ያለ ፥ ገላ ፤ ሠርጓዳው ፥ የሙሐይት ፥ መ ካከል ። አንቀጹ ፥ ተፈተፈ ፥ ነው ።

ቴፈ ፤ (ተየፈ) ፤ መላ ፥ ተንሣ ፥ ተንሳፈፈ ፥ ተንካፈፈ ። ቴፈና ፥ ተፋ ፥ በምስጢር ፥ ይገጥማሉ ። የቴፈ ፥ ሥር ፥ በግእዝ ፥ ተፈየ ፥ ነው ።

አቴፈ ፤ አንሣ ፥ አንሳፈፈ ፥ አንካፈፈ ።

አቴፈው ፤ አንሳፈፈው ።

ማቴፍ ፤ ማንሣት ፥ ማንሳፈፍ ።

ማቴፈያ ፤ ማንሳፈፈያ ፥ ጊዜ ። ቲፍን ፥ ተመልከት ፤ የቴፈ ፥ ዘር ፥ ነው ።

ቶፋ ፥ (ፎች) ፤ ሸክላ ፥ ባሬታ ፥ ሴቶች ፥ ጢትና ፥ ማታ ፥ ግብር ፥ ውሃ ፥ ይዘው ፥ የሚወጡ



ቶፋ ፥

በት ። አንቀጹ ፥ ወተፈ ፥ ነው ። ቻለ ፥ ብለኸ ፥ አይቻልን ፥ አስተውል ።

ቶፋ ፤ ወኪል ፣ ምትክ ፣ ተጠሪ ፣ ገባሪ ።

ተፍገመገመ ፤— ተንገዳገደ ፤— ፈገመ ።

ትፋሕ ፤ ፍሬው ፣ ክብ ፣ እንክብል ፣ የኾነ ፣ ጣፋጭ ፣ ተክል ፣ (ምሳ፳፭ ፣ ፲፩ ። ማሕ፪ ፣ ፭) ። በ ግእዝ ፣ ኮል ፣ ይባላል ።



ትፋሕ ፡

ተፍረመረመ ፤—ተፍጨረጨረ ፤—ፈረመ ።

ተፈተፈ ፤ (ፈተፈተ) ፤ በጣ ፣ ፈቃ ፣ ቈረ ፣ ሠነተረ ፤ ላይ ፣ ላዩን ፣ በቅርብ ፣ በቅርብ ፣ ቈረጠ ፣ በፍዋነት ።

ተፍታፊ ፤ የተፈተፈ ፣ የሚተፈትፍ ፤ በጪ ፣ ቈራጭ ።

ትፍተፋ ፤ የመብጣት ፣ የመቈራት ፣ ሥራ ።

መተፍተፍ ፤ መብጣት ፣ መፍቃት ፣ መቈራት ፣ መቍረጥ ።

መተፍተፊያ ፤ መብጫ ፣ መፍቂያ ፣ መቈሪያ ፣ ምላጭ ፣ ሰንጢ ።

ተፈ ፤ ፈጣን ፣ ቀልጣፋ ፣ ሰው ።

ተፍተፍ ፤ ፍዋነት ፣ ችኵላ ።

ተፍተፍ ፡ አለ ፤ ፈጠን ፣ ፈጠን ፣ አለ ።

አተፈተፈ ፤ ቸኰለ ፣ ፈጠነ ፣ ተከተፈተፈ ።

አተፍታፊ ፤ ያተፈተፈ ፣ የሚያተፈትፍ ፤ ተፈ ፣ ከተፎ ።

ማተፍተፍ ፤ መቸኰል ፣ መፍጠን ።

ማተፍተፊያ ፤ መንገድ ፣ ሥራ ።

አስተፈተፈ ፤ አስበጣ ፣ አስፈቃ ፣ አስቈረ ፣ አስቈረጠ ፣ ፈትን ፣ ጎላን ፣ የሚጠበስ ፣ ሥጋን ።

አስተፈተፈ ፤ አስቸኰለ ፣ አጣደፈ ።

አስተፍታፊ ፤ ያስተፈተፈ ፣ የሚያስተፈትፍ ።

ማስተፍተፍ ፤ ማስበጣት ፣ ማስፈቃት ።

ተተፈተፈ ፤ ተበጣ ፣ ተፈቃ ፣ ተቈረ ፣ ተቈረጠ ፣ ተሠነተረ ።

ትፍትፍ ፤ የተተፈተፈ ፤ ብጥ ፣ ፍቅ ፣ የሰው ፣ ፊት ፤ ብርንዶ ።

ትፍትፍ ፤ በኩታና ፣ በቀሚስ ፣ ዳር ፣ የተጣለ ፣ ጥቍርና ፣ ብጫ ፣ ጥለት ።

ትፍትፋት ፤ ብጥታት ፣ ፍቅታት ፣ ቍርታት ።

አተፋተፈ ፤ አጣጣ ፣ አቋረጠ ፣ አሠናተረ ።

አተፋተፍ ፤ አበጣጥ ፤ መተፍተፍ ።

ተጸብአ ፤ (ጸብአ ፣ ተጸብአ) ፤ ሕልመ ፣ ሌሊት ፣ ሶፍያ ፤ ትርጓሜው ፣ መጣላት ፣ መዋጋት ፤ ሩካቤ ፣ ሕልም ።

ተቀበለ ፤—ተረከበ ፤—(ቀበለ) ።

ተቈጣ ፤—ገሠጸ ፤—(ቈጣ) ።

ተቀጸለ ፤—ተቀዳጀ ፤—ቀጸለ ።

ተራ ፤—ረድፍ ፤—ተረረ ።

ተሬ ፤—ተራማ ፤—ተረረ ።

ተር ፤—ቀጥ ፤—ተረረ ።

ቱር ፤ (ሰሪር ፣ ነጺሕ) ፤ መብረር ፣ መንጣት ።

ቱር ፡ አለ ፤ (ሰረረ) ፤ ተነሣ ፣ በረረ ።

ቱር ፡ አለ ፤ እጅግ ፣ ነጣ ፣ ጸዐዳ ፣ ኾነ ፤ ራዛ ፣ መሰለ ።

ታራ ፤ የሰው ፣ ስም ፤ የአብርሃም ፣ አባት ።

ቶራ ፤ (ግእዝ) ፤ ኹለቱ ፣ ቀንዶቹ ፣ ባለ



ቶራ ፡

ብዙ ፣ ባላ ፣ ባልኾ ፣ የኾኑ ፣ የበረዶ ፣ እንስሳ ፣ ወተታም ፣ የዋሊያ ፣ ወገን ፣ (ዘዳ፲፬ ፣ ፭) ።

ቶራ ፤ (ሶር) ፤ የበረሓ ፣ እንስሳ ፣ የዱር ፡



ቶራ ፡

ላም ፣ ያጋዘን ፣ ወገን ፤ ተባቱም ፣ እንስቱም ፡ ቶራ ፡ ይባላል ።

ቶሮች ፤ ኹለትና ፡ ከኹለት ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ብዙዎች ።

ቶራ ፡ መስክ ፤ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ቶራ ፡ ይሰግራበት ፡ የነበረ ፡ መስክ ፤ ባ፲፱፻፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

የርስ ፡ በርስ ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ተደርጎ ፡ ራስ ፡ ሉል ፡ ሰገድና ፡ ፌታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ ጐበና ፡ ሌሎችም ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ከነሰራዊታቸው ፡ የ ሞቱበት ፡ ሚዳ ።

ቶራ ፡ ፈረስ ፤ (ሶር ፡ ወፈረስ) ፤ አ ንደ ፡ ቶራ ፡ ኹለት ፡ ቀንድ ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ ጋ ማና ፡ ጭራ ፡ ያለው ፡ የዱር ፡ እንስሳ ፤ ፈረንጆች ፡ ግኑ ፡ ይሉታል ። (የጥቊሪት ፡ ጊዜ ፡ አዝማሪ) ፤ አ መቤቴ ፡ የቀረዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፤ ቶራ ፡ ፈረስ ፡ መስረር ።



ቶራ ፡ ፈረስ ፡

ተረበ ፤ ቀለደ ፡ አላገጠ ፡ አፌዘ ።

ተረበ ፤ ነደፈ ፡ ጠቅ ፡ አደረገ ፡ ወጋ ።

ተራቢ ፤ የተረበ ፡ የሚተርብ ፤ ቀልደኛ ፡ አላጋጭ ፡ ፌዘኛ ።

ተረብ ፤ ቀልድ ፡ ለግጥ ፡ ፌዝ ።

ተረበኛ ፡ (ኞች) ፤ ተረብ ፡ ወዳድ ፡ ባለ ተረብ ።

ትረባ ፤ መተረብ ።

ተርብ ፡ (ቦች) ፤ የተንቀሳቃሽ ፡ ስም ፤ በ መርዙ ፡ የሚነድፍ ፡ በክንፉ ፡ የሚበር ፡ የውሻ ፡ ንብ ። ሳንጃን ፡ እይ ።



ተርብ ፡

ተርቡት ፤ ጨቅጫቃ ፡ ሴት ፡ አፈኛ ፡ ነገ ረኛ ፡ ሻያ ፡ ቢስ ።

መተረብ ፤ መቀለድ ፡ ማላገጥ ፡ ማፌዝ ።

መተረቢያ ፤ ማላገጫ ፡ ማፌዣ ።

አስተረበ ፤ አስቀለደ ፡ አስፌዘ ።

አስተራቢ ፤ ያስተረበ ፡ የሚያስተርብ ፤ አ ስቀላጅ ።

ማስተረብ ፤ ማስቀለድ ፡ ማስፌዝ ።

ማስተረቢያ ፤ ስፍራ ፡ ጊዜ ።

ተተረበ ፤ ተቀለደ ፡ ተፌዘ ።

ተተረበ ፤ ተነደፈ ፡ ተወጋ ።

አተራረብ ፤ አቀላለድ ፤ መተረብ ።

ተረበ ፤ (ሰረበ) ፤ ፈሰሰ ፡ ወረደ ።

መትረብ ፡ (ቦች) ፤ መስረብ) ፤ አሸንዳ ፤ ውስጠ ፡ ክፍት ፡ የውሃ ፡ መኼጃ ፡ ዕንጨት ፡ ቀር ክሓን ፡ ቀጭልልን ፡ የመሰለ ፤ መፍሰሻ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቶረበ ፤ አራርቆ ፡ ወጋ ፡ ተርታ ፡ ስፌት ፡ ሰፋ ፡ ወሰወሰ ፡ ሸደሸደ ፡ ሸለለ ፡ ሸከሸከ ።

ቶራቢ ፤ የቶረበ ፡ የሚቶርብ ፤ ሸድሻጅ ፡ ሸክሻኪ ።

ቱረባ ፤ ውስወሳ ፡ ሽድሸዳ ።

መቶረብ ፤ መወስወስ ፡ መሸድሸድ ።

መቶረቢያ ፤ መሸድሸጃ ፡ መርፌ ።

አስቶረበ ፤ አስወሰወሰ ፡ አሸደሸደ ፡ አሸ ለለ ፡ አሸከሸከ ።

አስቶራቢ ፤ ያስቶረበ ፡ የሚያስቶርብ ።

ማስቶረብ ፤ ማስወስወስ ፡ ማሸክሸክ ።

ማስቶረቢያ ፤ ማስወስወሻ ።

ተቶረበ ፤ ተሰፋ ፡ ተወሰወሰ ፡ ተሸደሸደ ፡ ተሸለለ ፡ ተሸከሸከ ።

ቱርብ ፤ የተቶረበ ፤ ውስውስ ፡ ሽድሽድ ፡ ሽልል ፡ ሽክሽክ ፤ መናኛ ፡ ስፌት ፡ ከጥብቅ ፡ ስፌት ፡ ቀዳሚ ።

አቷረበ ፤ አወሳወሰ ፡ አሸዳሸደ ።

ማቷረብ ፤ ማሸዳሸድ ።

አቶራረብ ፤ አሸዳሸድ ፤ መቶረብ ።

ተረገ ፤ ሠረገ ፡ ተንቀጠቀጠ ።

ትርግ ፡ ትርግ ፡ አለ ፤ ሥርግ ፡ ሥርግ ፡ አለ ፤ የልብ ፡ የርግብግቢት ።

ተረጐመ ፤ **(ተርጐመ)** ፤ ከቋንቋ ፡ ወደ ፡ ቋንቋ ፡ ገለበጠ ፡ መለሰ ፤ ፈታ ፡ ገለጠ ፡ አስረዳ ፤ መጽሐፍ ፡ አሰማ ፡ ኦለ ፡ ምን ፡ ነገረ ፤ አንድም ፡ አለ ፤ ዘረዘረ ።

ተርጓሚ ፡ (ሞች) ፤ የተረጐመ ፡ የሚተረ ጕም ፡ ሊቅ ፤ የብሉይ ፡ የሐዲስ ፡ የሊቃውንት ፡ (ያቡ ፡ ሻህር) ፡ የመጽሐፈ ፡ መነኮሳት ፡ መምር ።

ተርጓሚ ፡ ደርጋሚ ፤ ንባብን ፡ በትርጓሜ ፡ የሚያስተባብል ፡ (ፀጌጥ ፡ ፫ ፡ ፲፯) ።

መተርጐም ፤ መገልበጥ ፡ መመለስ ፡ መፍ ታት ፡ መግለጥ ፡ ማስረዳት ።

መተርጐሚያ ፤ መግለጫ ፡ ማስረጃ ፡ ወ ንበር ፡ ጉባኤ ።

አስተረጐመ ፤ አስገለበጠ ፡ አስፈታ ፡ አስ ገለጠ ፡ (አስደራጊ) ።

አስተረጐመ ፤ ተረጐመ ፡ አነጋገረ ፡ (አ ድራጊ) ።

አስተርጓሚ ፡ (ሞች) ፤ ያስተረጐመ ፡ የሚያስተረጕም ፤ አነጋጋሪ ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋቂ ፡ ስማ ፡

በለው ፡ መካከለኛ ፡ ሰው ፡ አምጃር ፡ (ዘፍ፴፪ ፡ ፳፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፳፭) ።

አስተርጓሚነት ፤ አነጋጋሪነት ።

ማስተርጐም ፤ ማስገልበጥ ፡ ማስፈታት ፤ መተርጐም ፡ ማነጋገር ።

ማስተርጐሚያ ፤ ማነጋገሪያ ፡ ችሎት ፡ አደባባይ ።

ተተረጐመ ፤ (ተተርጐመ) ፤ ተገለበጠ ፡ ተመለሰ ፡ ተፈታ ፡ ተገለጠ ።

ትርጉም ፤ (ትርጕም) ፤ የተተረጐመ ፡ የተፈታ ፡ የተገለበጠ ፡ የተገለጠ ፤ ግልጥ ፡ ንግግር ።

ትርጉማን ፤ ትርጁማን ፡ ተርጓሚ ፡ አስተርጓሚ ።

ተተራጐመ ፤ ተፋታ ፡ ርስ ፡ በርሱ ።

አተራጐመ ፤ አገላበጠ ፡ አማለሰ ፡ አፋታ ።

ማተራጐም ፤ ማማለስ ፡ ማፋታት ።

አተረጓጐመ ፤ አመላለሰ ።

ትርጐማ ፤ የመተርጐም ፡ ሥራ ፤ ግልበጣ ፡ ምለሳ ።

ትርጓሜ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ፍች ፡ ስለ ፡ ምን ።

አተረጓጐም ፤ አፈታት ፤ መተርጐም ።

ተራዳ ፤—የድንኳን ፡ ምሰሶ ፤—ረዳ።

ትርጁማን ፤ (ዐረ ፡ ተርጁማን) ፤ አስተርጓሚ ።

ተረወ ፤ ደረሰ ፡ መጣ ።

ትርው ፤ ዝር ፡ መድረስ ።

ትርው ፡ አለ ፤ ዝር ፡ አለ ።

ትርው ፡ አትበል ፤ አትድረስ ።

ተረከ ፤ አወጋ ፡ አወራ ፡ ያለፈ ፡ ነገርን ፡ አሳሰበ ፤ እንዲህ ፡ ነበር ፡ አለ ።

ተራኪ ፡ (ዎች) ፤ የተረከ ፡ የሚተርክ ፤ ወግ ፡ ዐዋቂ ።

ታሪክ ፡ (ኮች) ፤ ዜና ፡ ያለፈ ፡ ነገር ፡ በቃል ፡ በመጽሐፍ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ።

ታሪካም ፤ ባለታሪክ ፡ ታሪክ ፡ የሠራ ፡ የሚያወራ ።

ታሪከኛ ፡ (ኞች) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ታሪክ ፡ ያለው ፡ ባለዝና ፡ ስመ ፡ ጥር ።

ታሪክ ፡ ሙሴ ፤ የሙሴ ፡ ታሪክ ፤ ሙሴ ፡ ያደረገው ፡ ታምር ፤ የጻፈው ፡ መጽሐፍ ።

ታሪክ ፡ ነገሥት ፤ የንጉሦች ፡ ታሪክ ፡ የነገሥታትን ፡ ትውልድና ፡ ዘመን ፡ አገዛዛቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ ዕድሚያቸው ፡ በጊዜያቸው ፡ የሸነውን ፡ የተደረገውን ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ (ከ ብረ ፡ ነገሥት) ።

ታሪክ ፡ ዓለም ፤ የዓለም ፡ ታሪክ ፡ ጊዮ ርጊስ ፡ ወልደ ፡ ሐሚድ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ የጸፈው ።

ትረካ ፤ መተረክ ።

መተረክ ፤ ማውጋት ፡ ማውራት ፡ ማሳሰብ ።

መተረኪያ ፤ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፤ ገላጭ ።

አስተረከ ፤ አስወጋ ፡ አስነገረ ፡ አስወራ ፡ ታሪክን ።

አስተራኪ ፤ ያስተረከ ፡ የሚያስተርክ ።

ማስተረክ ፤ ማስነገር ፡ ማስወራት ።

ማስተረኪያ ፤ ጊዜና ፡ ስፍራ ።

ተተረከ ፤ ተወጋ ፡ ተነገረ ፡ ተወራ ።

አተራረከ ፤ የታሪክ ፡ አነጋገር ፤ መተረክ ።

ቱርክ ፡ (ኮች) ፤ የነገድ ፡ ስም ፤ በታናሽ ፡ እስያና ፡ ባውሮጳ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ የሚኖር ፡ ሕዝብ ።

ቱርክኛ ፤ የቱርክ ፡ ቋንቋ ።

ቱርክ ፡ ባሻ ፤ (የቱርክ ፡ ባሻ) ፤ በምጥጭ፡ የነበረ ፡ የቱርክ ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ አዛዥ ፡ ሻለቃ ፡ ባጤ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ዮናኤል ፡ የሚባል ፡ ሐርበኛ ፡ በሾተል ፡ ወግቶ ፡ የገደለው ፤ ከዚህ ፡ በ ኋላ ፡ ይህ ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የገባ ፡ ይመስላል ። ፓሻንና ፡ ባሻን ፡ ተመልከት ።

ቱርክ ፡ ባሻ ፡ ታምሬ ፤ ያጤ ፡ ምኒልክ ፡ ጋሻ ፡ ጐግሬ ። ቱርክ ፡ ባሻ ፡ ማዕርጋቸው ፤ ታምሬ ፡ ስማቸው ።

ትርኪ ፡ ምርኪ ፤ ቅባጥርሴ ፡ ቅራቅንቦ ፤ የማይረባ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ምናምን ፡ ነገር ። ትርኪ ፡ ከተረከ ፤ ምርኪ ፡ ከማረከ ፡ ይወጣል ።

ተረከበ ፤—ተቀበለ ፤—ረከበ ።

ተረከዘ ፤ (ዐረ ፡ ረከዘ ፤ አቆመ ፡ የ ብስ ፡ ረገጠ) ፤ ቀዘፈ ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ መርከብን ፡ መራ ።

ትርከዛ ፤ (ጎዳፍ) ፤ መቅዘፊያ ፡ የውሃ ፡ መግፊያ ፡ የባሕር ፡ ላይዳ ።

ተረከዝ ፡ (ዞች) ፤ የእግር ፡ ኋለኛ ፡ ጫፍ ፡ መርገጫ ፡ መቆሚያ ፡ ሰኰና ፡ (ግብ ፡ ሐዋ፲ ፡ ፯) ።

ተረከዘ ፡ ክት ፤ እግሯ ፡ የሚያምር ፡ ሴት ፡ ተረከዘ ፡ ዐጪር ።

ተረከዘ ፡ ሎሚ ፤ ተረከዙ ፡ ሎሚ ፡ የሚ መስል ፤ ማማው ፡ ንትብ ፡ ፈለግ ፡ ሥንጥቅ ፡ የሌ ለበት ፡ ሰው ።

ተረከከ ፤ ጠረቀቀ ፡ ሠነጠቀ ፡ ፈነከተ ።

ተርካኪ ፤ የተረከከ ፡ የሚተረከከ ፤ ጠር ቃቂ ፡ ሠንጣቂ ፡ ፈንካች ።

ትርከካ ፤ ሥንጠቃ ፡ ፍንከታ ።

መተርከክ ፤ መጠርቀቅ ፡ መሠንጠቅ ፡ መ ፈንከት ።

መተርከኪያ ፤ መሠንጠቂያ ፡ መፈንከቻ ፡ ምጣር ፡ ዱላ ።

አስተረከከ ፤ አስጠረቀቀ ፥ አሠነጠቀ ፥ አስፈነከተ ።

ማስተርከክ ፤ ማሠንጠቅ ፥ ማስፈንከት ።

ተተረከከ ፤ ተጠረቀቀ ፥ ተሠነጠቀ ፥ ተፈነከተ ።

ትርክክ ፤ የተተረከከ ፤ ጥርቅቅ ፥ ሥንጥቅ ፥ ፍንክት ።

ትርክክ ፥ አለ ፤ ሥንጥት ፥ አለ ፤ ተተረከከ ።

ተተራከከ ፤ ተፈናከተ ።

መተራከክ ፤ መፈናከት ።

መተራከኪያ ፤ መፈናከቻ ።

አንተረከከ ፤ አፈራ ፥ አበሰለ ። (ደረከከ) ፥ ብለኸ ፥ አንደረከከን ፥ እይ ።

አንተረከከ ፤ አሠባ ፥ አወፈረ ፥ መክትን ፥ ፍረዳን ።

ማንተርከክ ፤ ማፍራት ፥ ማብሰል ።

ማንተርከኪያ ፤ ማብሰያ ፥ ጎዳር ፥ ታጎ ማሥ ።

ተንተረከከ ፤ በሰለ ። እኽል ፥ በጊዜ ፥ ባይ ሰበሰብ ፥ የእንቡጡን ፥ መፈንዳትና ፥ የዛላውን ፥ መበተን ፥ ያሳያል ።

ተንተረከከ ፤ ሠባ ፥ ወፈረ ።

መንተርከክ ፤ በፀሓይ ፥ መብሰል ።

መንተርከኪያ ፤ መብሰያ ፥ የሰብል ፥ ጊዜ ፥ መከር ።

አተረካከከ ፤ አሠነጣጠቅ ፤ መተርከክ ።

(ተረከመ) ፤ ጠረቀመ) ፤ ተተራከመ ፤ ተሰበሰበ ፥ ተጠራቀመ ።

ትርክም ፤ የተሰበሰበ ፤ ጥርቅም ።

ትርክምክም ፤ ብዙ ፥ ትርክም ።

አተራከመ ፤ ሰበሰበ ፥ አጠራቀመ ።

አተራካሚ ፤ ያተራከመ ፥ የሚያተራክም ፤ ሰብሳቢ ፥ አጠራቃሚ ።

ተረከሰ ፤ ቀለሰ ፥ አጐበጠ ።

ተተረከሰ ፤ ተቀለሰ ፥ ጐበጠ ።

ተርካሳ ፤ ቀላሳ ፥ ጐባጣ ፥ ጉብር ።

ተረኰሰ ፤ ሰበረ ፥ ኩሰተረ ፥ አለማ ፥ መብራትን ።

ተርኳሽ ፤ የተረኰሰ ፥ የሚተረኰስ ፤ ኩስታሪ ።

ትርኰሳ ፤ ሰበራ ፥ ኩሰተራ ፤ የጠለሰ ።

መተርኰስ ፤ መስበር ፥ መኩሰተር ።

መተርኰሻ ፤ መኩሰተሪያ ፥ ማልሚያ ፥ ሠንጣቃ ፥ ዕንጨት ።

ተተረኰሰ ፤ ተሰበረ ፥ ተኩሰተረ ፥ ለማ ።

ትርኳሽ ፥ ሾ ፤ የተተረኰሰ ፤ ኩስታሪ ፥ (ዘካኮ ፥ ፪) ።

አተረኳኰስ ፤ አኩሰታተር ፤ መተርኰስ ። ተረኰሰና ፥ ኩሰተረ ፥ እንድ ፥ ዘር ፥ ናቸው ፤ ከመዛመር ፥ በቀር ፥ ልዩነት ፥ የላቸውም ።

ቲርማ ፤ ጅር ፥ የዝንጅሮ ፥ ጓዝ ።

ተረመሰ ፤—ተወሸቀ ፤—ረመሰ ።

(ተረመሰ) ፤ ተተራመሰ ፤ ተሸበረ ፥ ታወከ ፥ ታመሰ ፥ ተፋጀ ፥ ተበጠበጠ ፥ ተመሳቀለ ፤ ጨሰ ፥ እንደ ፥ ገባው ፥ ንብ ፥ ጉን ። ዘሩ ፥ ፀኛው ፥ ረመሰ ፥ ነው ።

ትርምስ ፤ ሽብር ፥ ፍጅት ፥ ሁከት ፥ ብጥብጥ ።

መተራመስ ፤ መታወክ ፥ መታመስ ፥ መመሳቀል ።

መተራመሻ ፤ መታወኪያ ፥ መመሳቀያ ።

ተተረማመሰ ፤ ተበጣበጠ ፥ ተመሰቃቀለ ።

ትርምስምስ ፥ ብጥብጥ ፥ ምስቅልቅል ።

ትርምስምስ ፥ አለ ፤ ምስቅልቅል ፥ አለ ።

መተረማመስ ፤ መበጣበጥ ፥ መመሰቃቀል ።

መተረማመሻ ፤ መበጣበጫ ።

አተራመሰ ፤ አወከ ፥ በጠበጠ ፥ አሸበረ ፥ ዐመሰ ፥ አፋጀ ፥ አመሳቀለ ።

አተራማሽ ፤ ያተራመሰ ፥ የሚያተራምስ ፤ አዋኪ ፥ በጥባጭ ፥ ዐማሽ ፥ አመሳቃይ ።

ማተራመስ ፤ ማወክ ፥ መበጥበጥ ፥ ማፋጀት ፥ ማመስ ፥ ማመሳቀል ።

ማተራመሻ ፤ ማወኪያ ፥ ማመሳቀያ ።

አተረማመሰ ፤ አበጣበጠ ፥ አመሰቃቀለ ።

አተረማማሽ ፤ ያተረማመሰ ፥ የሚያተረማምስ ፤ አበጣባጭ ።


ማተረማመስ ፤ ማበጣበጥ ፥ ማመሰቃቀል ።

ማተረማመሻ ፤ ማበጣበጫ ፥ ማመሰቃቀያ ።

አተረማመስ ፤ አበጣበጥ ፤ ማተራመስ ።

ታናሽ ፤ ትንሽ ፤—ያነሰ ፤—አነሰ ።

ተረን ፤ የሚዛን ፥ ቄጤ ፥ በገመድ ፥ የተንጠለጠለው ፥ ቋቱ ። ድንጋይም ፥ ተረን ፥ ይባላል ፤ ፻፲፫ ፥ ተኩል ፥ ግራም ፥ ያነሳል ። ፪ ፥ አበት ፥ ፩ ፥ ተረን ፥ ነው ።



ትርንጎ ፥ (ዎች) ፤ የተክል ፥ ስም ፤ ጣዕም ፥ ከመዐዛ ፥ ያለው ፥ ተክል ። ዛፉም ፥ ፍሬውም ፥ ትርንጎ ፥ ይባላል ።

ትርንጎ ፥

ቱሪናፋ ፤ የማይረባ ፣ ወታደር ፣ ሰነፍ ። (ሽለላ) ፤ ቱሪናፋ ፣ ቱሪናፋ ፣ በጦር ፣ ሜዳ ፣ አት ገኝ ፤ ከቀለቡ ፣ አትጠፋ ።

ተረንተራ ፤ (ተረን ፣ ተራ) ፤ ማፋዳ ፣ ቦርሳ ፣ ኩፋዳ ፣ የንበብ ፣ መያዣ ። በግእዝ ፣ ቍና ምት ፣ ይባላል ።

ተረፈ ፤ (ተርፈ) ፤ ዳነ ፣ ቀረ ፣ ተፈታ ፣ ተፈወሰ ፣ ተተወ ።

ተረፈ ፤ በዛ ፣ ከልከ ፣ ዐለፈ ፣ ከመጠን ፣ በ ለጠ ። ከሀብታም ፣ ይተርፈዋል ፣ እንዲሉ ። (ተረት) ፤ ላሳር ፣ የጣፈው ፣ ቢነግድ ፣ አይተርፈው ።

ተረፈ ፤ ኾነ ፣ ደረሰ ። ለኃጥአን ፣ የወረደ ፣ ለጻድቃን ፣ ይተርፋል ።

ተራፊ ፤ የሚተርፍ ፣ የሚቀር ፤ ዳኛ ፣ ቀሪ ።

ተረፍ ፣ ቅሬታ ።

ተረፈ ፣ ኤርምያስ ፤ የኤርምያስ ፣ መጽ ሐፍ ፣ ደረቅ ፣ ትንቢት ፣ የሚናገር ፣ (ማቴ፳፬ ፣ ፱) ።

ተረፈ ፣ ብንያም ፤ የብንያም ፣ ነገድ ፣ ቅ ሬታ ፣ የሞት ፣ ትራፊ ።

ተረፈ ፣ መሚዕት ፤ አኩቴት ።

ትራፊ ፤ (ትራፍ) ፤ የተረፈ ፣ የቀረ ፣ (ኢሳ ፲፩ ፣ ፲፩) ።

ትርፍ ፣ (ፎች) ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ ከስፍር ፣ ከቊጥር ፣ ውጭ ፣ የኾነ ፣ እኽል ፣ ገንዘብ ፤ ፋይዳ ፣ ጥቅም ፣ ሰው ፣ በድካሙ ፣ የሚያገኘው ፣ (ዘዳ፳ ፤ ፲፫ ። መክ፮ ፣ ፪) ። (ተረት) ፤ ካላረፉ ፣ መከራ ፣ ነው ፣ ትርፉ ።

ትርፌ ፤ የወንድና ፣ የሴት ፣ ስም ፤ የኔ ፣ ት ርፍ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ትርፍ ፣ የጋራ ፤ ትርፍ ፣ ያበዳሪና ፣ የተበ ዳሪ ፣ ነው ፤ ከኹለት ፣ ይከፈላል ።

ትርፍነት ፤ ትርፍቻ ፤ ትርፍ ፣ መኾን ፣ (ሮሜ፫ ፣ ፪) ።

ትሩፍ ፤ ሃይማኖቱ ፣ የጸና ፣ ምግባሩ ፣ የቀና ፣ ትርፍ ፣ የጽድቅ ፣ ሥራ ፣ የሠራ ፣ ሰው ፣ በግእዝ ፣ ትሩፍ ፣ ይባላል ፤ ፍጹም ፣ ማለት ፣ ነው ።

ትሩፍ ፤ የይሁዳ ፣ ነገድና ፣ የብንያም ፣ ቅ ሬታ ፣ ካሥሩ ፣ ነገድ ፣ ጋራ ፣ ያልተግረዘ ፣ (ነሐ ፩ ፣ ፪ ፣ ፫) ።

ትሩፍ ፤ በፋርስ ፣ በባቢሎን ፣ ከሰባ ፣ ዘ መን ፣ መከራና ፣ ሞት ፣ የቀረ ፣ የእስራኤል ፣ ወገን ።

ትሩፋን ፤ ቅሬቶች ።

ትሩፋን ፤ የተረፉ ፣ የቀሩ ፣ ወደ ፣ ኢየሩሳ ሌም ፣ ያልተመለሱ ፤ ከእስራኤል ፣ ተለይተው ፣ በ ፋርስ ፣ የኖሩ ።

ትሩፋን ፤ ዕዝራ ፣ ሱቱኤል ፣ ያያቸው ፣ መ ናኖች ፣ ፍጹማን ፣ በፍጻሜ ፣ ዘመን ፣ የሚገለጹ ።

ትሩፋት ፤ የሴቶች ፣ ሳድስ ፣ ቅጽል ።

ትሩፋት ፤ የበዙ ፣ የተረፉ ፣ የነፍስ ፣ ሥራ ዎች ፤ (በቂ) ። ባላገር ፣ ግን ፣ ትሩፋቶች ፣ ይላል ። ተረፍ ፣ ትራፍ ፣ ትሩፍ ፣ ትሩፋን ፣ ትሩፋት ፣ የ ግእዝ ፣ ናቸው ።

መትረፍ ፤ መዳን ፣ መቅረት ፣ መብዛት ።

መትረፊያ ፤ መዳኛ ፣ መቅሪያ ፣ መብዣ ።

አተረፈ ፤ (አትረፈ) ፤ አዳነ ፣ ፈታ ፣ ፈ ወሰ ፣ ተወ ፣ አስቀረ ።

አተረፈ ፤ አበዛ ፣ ትርፍ ፣ ሰጠ ፣ አከለ ፣ ጨመረ ፣ (ጀነገ ፣ ፬ ። ግፎ ፣ ፵፬ ። ኤርግጅ ፣ ፵፮) ። (ቂም ፣ አተረፈ) ፤ አቈየ ።

አተርፍ ፤ አበዛ ፣ አከል ፣ እጨምር ። አተ ርፍ ፣ ባይ ፣ አጮዳይ ፣ እንዲሉ ።

አትራፊ ፣ (ፎች) ፤ ያተረፈ ፣ የሚያተርፍ ፤ አዳኝ ፣ አብዢ ፣ ነጋዴ ።

ማትረፍ ፤ ማዳን ፣ መፈወስ ፣ ሙተው ፣ ማብዛት ።

ማትረፊያ ፤ ማዳኛ ፣ ማብዣ ፣ መድኀኒት ፣ ንግድ ።

አስተረፈ ፤ አስዳነ ፣ አስተወ ፣ አስቀረ ። (አላስተረፈኝም) ፤ እጅግ ፣ በጣም ፣ ጕድኛል ።

አስተራፊ ፤ ያስተረፈ ፣ የሚያስተርፍ ፤ አስቀሪ ።

ማስተረፍ ፤ ማስተው ፣ ማስቀረት ።

ማስተረፊያ ፤ ማስቀሪያ ።

አታረፈ ፤ አባለጠ ፣ አባዛ ።

ተትረፈረፈ ፤ የትርፍ ፣ ትርፍ ፣ ኾነ ።

የተትረፈረፈ ፤ ተርፎ ፣ የፈሰሰ ። መጽ ሐፍ ፣ ግን ፣ የተረፈረፈ ፣ ይላል ፤ እያሠኝም ፣ (ሉቃ፮ ፣ ፴፰) ።

ትርፍራፊ ፤ ፍርፋሽ ።

ትርፍርፍ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ።

ትርፍርፍ ፣ አለ ፤ ተትረፈረፈ ።

አተራረፍ ፤ አዳዳን ፤ መትረፍ ።

(ተረፋ) ፤ ተንተራፋ ፤ ተሰበረ ፣ ተጨፈ ለቀ ፣ ተጨማለቀ ፤ ፈሰሰ ፣ ውሃው ፣ ደሙ ።

መንተራፋት ፤ መሰበር ፣ መጨፍለቅ ፣ መጨማለቅ ።

አንተራፋ ፤ ሰበረ ፣ ጨፈለቀ ፣ አጨማ ለቀ ፣ ውሃ ፣ ያለበት ፣ እንስራን ፣ የሰውን ፣ ራስ ። (የዱሮ ፣ ግጥም) ፤ ድንጋይ ፣ ካፋፍ ፣ ወርዶ ፣ እሰ ብጥ ፣ ያርፋል ፤ አዎን ፣ ያርፋል ፤ ሰው ፣ ያገኘ ፣ እንደኹ ፣ ያንተራፋል ፤ አዎን ፣ ያንተራፋል ።

አንተርፋ ፤ የቅጠል ፣ ስም ፤ ለመጋኛ ፣ በጠጡት ፣ ጊዜ ፣ የሚያስቀምጥና ፣ የሚያስታውክ ፣ ወረፋ ፣ የሚያወጣ ፣ ዐረግ ።

ማንተራፋት ፤ መሰበር ፣ መጨፍለቅ ።

ተርፍ ፤ ድንጋጤ ፣ ዝላይ ፤ መደንገጥ ፣ መዝለል ፤ የልብ ።

ተርፍ ፡ አለ ፤ ደነገጠ ፣ ተከፈለ ፤ ዘለለ ፣ ፈሰሰ ።

(ተረፈፈ) ፤ **ደረበበ)** ፤ **አንተረፈፈ** ፤ መላ ፣ ቅዝ ፣ አደረገ ፤ አንደረበበ ። አንተረፈፈ ፣ የፈሳሽ ፤ አንደረበበ ፣ የደረቅ ፣ ነው ።

ማንተርፈፍ ፤ መምላት ፣ ማንደርበብ ።

ማንተርፈፊያ ፤ መምሊያ ፣ ማንደርበቢያ ።

ተንተረፈፈ ፤ ተመላ ፣ ተንደረበበ ፤ ቲፍ ፣ አለ ።

መንተርፈፍ ፤ መምላት ፣ መንደርበብ ።

መንተርፈፊያ ፤ መምሊያ ፣ መንደርበቢያ ።

ተረፈሰ ፤ አብዝቶ ፣ ዘገነ ፣ ዐፈሠ ፣ ተርፎ ፣ እስኪፈስ ፤ ቃመ ። ቸፈረን ፣ እይ ።

ተርፋሽ ፤ የተረፈሰ ፣ የሚተረፍስ ፤ ዘጋኘ ፣ ቃሚ ።

ተረፈሰ ፤ **ተርፋሳ** ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ።

ትርፈሳ ፤ ዘገና ፣ ዐፈሣ ።

መተርፈስ ፤ መዝገን ፣ ማፈሥ ፣ መቃም ።

መተርፈሻ ፤ መዝገኛ ፣ ማፈሻ ፣ መቃሚያ ፣ እጅ ፣ አፍ ።

አስተረፈሰ ፤ አዘገነ ፣ አሳፈሠ ፣ አስቃመ ።

ማስተርፈስ ፤ ማዘገን ፣ ማስቃም ።

አተረፋፈሰ ፤ አዘጋገን ፤ መተርፈስ ።

ተራቄተ ፤—ታረዘ ፤—ዐረቀ ።

ተረረ ፤ **(ትግ)** ፤ ጠና ፣ ጠነከረ ፣ በረታ ።

ተረረ ፤ ቀጥታ ፣ ኾነ ።

ተራራ ፤ ረዥምና ፣ ከፍተኛ ፣ ዐምባ ፤ ብርቱ ፣ ስፍራ ፣ የምድር ፣ ራስ ።



ተራራ ፣

ተራራማ ፤ ተራራ ፣ ያለበት ፣ የበዛበት ፣ አገር ፣ ባለተራራ ።

ተራራም ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ።

ተራሮች ፤ ዐምቦች ፣ (ዘፍ፱ ፣ ፭) ።

ተረረ ፤ ሠነቀ ፣ ከፈለ ፤ ረደፈ ፣ ደረ ደረ ። ጠረረ ፣ ብለኽ ፣ ጥራርን ፣ አስተውል ።

ተራሪ ፤ የተረረ ፣ የሚተርር ፤ ሠንጣቂ ፣ ደርዳሪ ።

ተረር ፤ የቅሞ ፣ ፍሬ ፣ ዘለላው ፣ በየረድፉ ፣ የሚንጠለጠል ።

ተረር ፡ አለ ፤ ሥንጥቅ ፣ አለ ።

ተራ ፤ ረድፍ ፣ ፊና ፣ ወረፋ ፣ (ዘፀጽጅ ፣ ፲፱ ፣ ጽ) ።

ተራ ፤ የሸቀጥ ፣ መደብ ፣ መደብር ፣ ስፍራ ። እኽል ፣ ተራ ፣ በግ ፣ ተራ ፣ ጌሾ ፣ ተራ ፣ አጣና ፣ ተራ ፣ ማእዘን ፣ ተራ ፣ ሰንጋ ፣ ተራ ፣ እንዲሉ ።

ተረኛ ፡ (ሞኝ) ፤ ዘቡ ፣ ሥራው ፣ የርሱ ፣ የኽነ ፣ ባለተራ ። ወርን ፣ እይ ።

ተራ ፡ መታ ፤ አተረተረ ፣ ተስደረ ፣ ተደረደረ ። (በተራ ፣ በተራ) ፤ በቅደም ፣ ተከተል ፣ በረድፍ ፣ በረድፍ ።

ተራ ፡ ቍጥር ፤ ኛኛ ፣ ፪ኛ ፣ እየተባለ ፣ የሚጸፍ ።

ተራ ፡ ሰው ፤ አልባሌ ።

ተርታ ፤ መናኛ ፣ ትሑት ፤ ተራ ፣ መደዳ ፣ (ጅነገ ፣ ፯ ። ፴፯ ። ፺ ፣ ፲፪ ። ዕብ፱ ፣ ፭) ።

ተርታ ፡ ነገር ፤ ቁም ፡ ነገር ፣ ያልኾነ ፣ ጉዳይ ።

ተርታ ፡ ሰው ፤ ሹመት ፣ ማዕርግ ፣ የሌለው ፣ ተራ ፣ ሰው ።

ተሬ ፤ ተራዊ ፣ ተራማ ፣ የተራ ፤ አንድ ፣ የወንድ ፣ ልጅ ፣ ሽሩባ ፣ በራስ ፣ አማካይ ፣ ከግንባር ፣ እስከ ፣ ግሹራት ፣ ያለ ፣ ዕሽም ፣ ተረተር ፣ መስሎ ፣ የሚታይ ።

ተሬ ፤ ታናሽ ፣ ጉባ ፣ ቍልልታ ።

ተር ፤ ቀጥ ።

ተር ፡ አደረገ ፤ ቀጥ ፣ አደረገ ።

ተር ፡ አሉ ፤ ቀጥ ፣ አለ ።

መተረር ፤ መሠንጠቅ ፣ መክፈል ።

መተረሪያ ፤ መሠንጠቂያ ፣ ምላር ።

አስተረረ ፤ አሠነጠቀ ።

ማስተረር ፤ ማሠንጠቅ ።

ማስተረሪያ ፤ ማሠንጠቂያ ።

ተተረረ ፤ ተሠነጠቀ ፣ ተከፈለ ።

ትርር ፤ የተተረረ ፤ ሥንጥቅ ።

አተራረር ፤ አሠነጣጠቅ ፤ መተረር ።

ትራስ፤—**የራስ ፡ ድጋፍ**፤—**ራስ ፡ ራስ** ።

ትርሽማ ፤ የወታደር ፡ ድንኳን ፡ ዐጪሯ ፡



ትርሽማ ፡

ትንሿ ። ጉይዲ ፣ ግን ፡ ባለመደረቢያ ፡ የንጉሥ ፡ ድንኳን ፡ ጌጣኛ ፡ ይለዋል ።

ተርሴስ ፤ በእስያ ፡ ክፍል ፡ ያለ ፡ አገር ፡ (መዝ፸፪ ፡ ፲) ።

ተረተ ፤ መሰለ ፤ ያለፈና ፡ የጊዜ ፡ ነገርን ፡ እውነት ፡ አስመስሎ ፡ አወጋ ።

ተራች ፡ (ኞች) ፤ የተረተ ፡ የሚተርት ፤ (ጥሳ) መሳይ ።

ተረት ፡ (ቶች) ፤ ልብ ፡ ወለድ ፡ ፈጠራ ፡ ነገር ፡ (ሉቃ፳፬ ፡ ፲፩) ። ተረት ፡ በምሳሌ ፤ ዜማ ፡ በሃሌ ፡ እንዲሉ ።

ተረታም ፤ ባለተረት ፤ የተረት ፡ ጌታ ፤ ተረት ፡ ዐዋቂ ፤ ተረተ ፡ ብዙ ።

ተረተኛ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የተረት ፡ ሰው ።

ተረት ፡ ተረት ፤ **የላም ፡ በረት** ፤ የተረት ፡ መቅድም ፡ ከተረት ፡ በፊት ፡ የሚባል ፡ የሚነገር ።

መተረት ፤ መመሰል ፡ ማውጋት ።

መተረቻ ፤ ተረት ፡ መናገሪያ ፡ ምሳሌ ፡ መመሰያ ፤ ከሰው ፡ ጥቅሪትን ፤ ከተራራ ፡ ፈንታሌን ፡ የመሰለ ።

መተረቻ ፡ ኾነ ፤ ተተረተበት ።

አስተረተ ፤ አስመሰለ ፡ አስነገረ ፡ አስወጋ ፡ (አውግዐ) ።

አስተራች ፤ ያስተረተ ፡ የሚያስተርት ።

ማስተረት ፤ ማስመሰል ፡ ማስወጋት ።

ማስተረቻ ፤ ጊዜ ፡ ስፍራ ።

ተተረተ ፤ ተመሰለ ፡ ተነገረ ፡ ተወጋ ፡ (ተወግዐ) ።

አታረተ ፤ ተረት ፡ አነጋገረ ፤ ምሳሌ ፡ አመሳሰለ ።

አተራረት ፤ አመሳሰል ፤ መተረት ።

ተርታ ፤—መናኛ ፤—ተረረ ።

ተረተረ ፤ (ተረረ) ፤ ስፈትን ፡ ጥምጥምን ፡ ፈታ ፡ ለየ ፤ ክርን ፡ ሚርን ፡ መዘዘ ፡ በጠሰ ። ተለተለን ፡ አይ ።

ተረተረ ፤ ሠነጠቀ ፡ ፈነከተ ፡ ዕንጨትን ፡ ራሰ ፡ ቅልን ።

ተረተረ ፤ ዕዳሪ ፡ አወጣ ፡ ጠጋ ፡ ጨፈለቀ ።

ተረተረ ፤ አቀና ፡ ቀጥ ፡ አደረገ ፡ ጐባጣን ።

ተረተረ ፤ ዘረዘረ ፡ ነጠለ ። አራት ፡ ያለውን ፡ ይተረትራል ፤ ትርጓሜ ፡ ሕዝቅኤል ፡ (፲፱ ፡ ፳፭) ።

ተርታሪ ፤ የተረተረ ፡ የሚተረትር ፤ ሠንጣቂ ፡ ፈንካች ፡ ጨፍላቂ ።

ተረተር ፡ (ሮች) ፤ የምድር ፡ ዝርባ ፤ የኰረብታ ፡ የተራራ ፡ መንገድ ፡ መንደርደሪያ ። የገደል ፡ ሲኾን ፡ ሸንተረር ፡ ይባላል ።

ተረተርማ ፤ የተረተር ፡ ባለተረተር ፡ ተረተራም ፡ ስፍራ ።

ትርተራ ፤ ልየታ ፡ ፍንከታ ፡ ጭፍለቃ ።

ትርታሮ ፤ ጭፍልቅ ።

መተርተር ፤ መፍታት ፡ መለየት ፡ መሠንጠቅ ፡ መፈንከት ፡ መጨፍለቅ ።

መተርተሪያ ፤ መርፌ ፡ ቦለድ ፡ በትር ፡ ማረሻ ።

ተራተረ ፤ ፈታታ ፡ ለያየ ፤ ሠነጣጠቀ ፡ ፈነካከተ ።

መተራተር ፤ መፈታታት ፡ መለያየት ፡ መሠነጣጠቅ ።

አተረተረ ፤ ዘር ፡ ዘር ፡ አደረገ ፡ በተራ ፡ አቆመ ፡ ሰደረ ፡ ደረደረ ፡ አሰለፈ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ ተገብሮ ፡ ነው ፤ (ተሰደረ ፡ ተደረደረ) ።

አተርትሮ ፤ ሰድሮ ፡ ደርድሮ ፤ (ተሰድሮ ፡ ተደርድሮ) ። ዐረፈ ፡ ብለኸ ፡ ምዕራፍን ፡ ተመልከት ።

አስተረተረ ፤ አስፈታ ፡ አስለየ ።

አስተረተረ ፤ አሠነጠቀ ፡ አስፈነከተ ።

አስተረተረ ፤ አስጨፈለቀ ።

አስተርታሪ ፤ ያስተረተረ ፡ የሚያስተረትር ፤ አሠንጣቂ ።

ማስተርተር ፤ ማስፈታት ፡ ማስፈንከት ፡ ማስጨፍለቅ ።

ተተረተረ ፤ ተፈታ ፡ ተለየ ።

ተተረተረ ፤ ተሠነጠቀ ፡ ተፈነከተ ፡ (ፈነገ ፡ ፲፫ ፡ ፭) ።

ተተረተረ ፤ ዕዳሪው ፡ ወጣ ፡ ተጨፈለቀ ።

ተተረተረ ፤ ቀና ፡ ቀጥ ፡ አለ ፤ የሰውነት ።

ተተረተረ ፤ ተዘረዘረ ፡ ተነጠለ ፡ ነገሩ ።

ተተርታሪ ፤ የሚተረተር ፡ ተሠንጣቂ ።

ትርትር ፤ የተተረተረ ፡ የተፈታ ፤ ሥንጥቅ ፡ ፍንክት ፡ ጭፍልቅ ።

ትርትር ፡ አለ ፤ ሥንጥቅ ፡ አለ ።

ትርታሪ ፤ ከስፈት ፡ የተፈታ ፡ ክር ።

(ጥርር)ትርትር ፡ አለ ፤ ርግብ ፡ ርግብ ፡ አለ ፤ ተንቀጠቀጠ ።

ተተራተረ ፤ ተፈናከተ ።

አተራተረ ፤ አፋታ ፡ አለያየ ።

አተራተረ ፤ አሠናጠቀ ፡ አፈናከተ ።

አተራተረ ፤ አጨፋለቀ ።

ማተራተር ፤ ማሠናጠቅ ፡ ማፈናከት ።

አተራተር ፤ አፈታት ፤ መተርተር ።

ተሰ ፤ የተደራጊና ፣ የተደራራጊ ፣ አንቀጽ ፣ ባዕድ ፣ መነሻ ። ከረከረ ፣ ተሰከረከረ ፤ ነገደ ፣ ተና ገደ ፣ ተሰተናገደ ።

ተሸ ፤ የደጊመ ፣ ቃል ፣ ተደራጊ ፣ አንቀጽና ፣ ቅጽል ፣ ባዕድ ፣ መነሻ ። ከረከረ ፣ ተሸከረከረ ፣ ተሸ ከርካሪ ፤ ቁጠቁጠ ፣ ተሸቁጠቁጠ ፣ ተሸቁጥቋጥ ፤ ቀረቀረ ፣ ተሸቀረቀረ ፣ ተሸቀርቃሪ ።

ቱስ ፣ አለ ፤—ተፈሳ ፤—ቶሰቶሰ ።

ተስቦ ፤—ክፉ ፣ በሽታ ፤—ሳበ ።

ትስብእት ፤ (ሰብእ) ፤ ሰውነት ፤ ሰው ፣ መኾን ።

ትስብእት ፤ ጌታችን ፣ ያለዘር ፣ የተፀነሰ በት ፣ ሥጋ ፣ የለበሰበት ፣ መጋቢት ፣ ኛ፱ ፣ ቀን ።

ተሲያት ፤ (ተስዐ) ፤ ከሠለስት ፣ በላይ ፣ ያለ ፣ ጊዜ ፣ ረፋድ ። አውራን ፣ አስተውል ።

ተሲያት ፣ ኾነ ፤ ረፈደ ።

ተሲያት ፤ (ተሱዓት ፣ ሰዓት) ፤ ዘጠኝ ፣ ሰዓት ። መንገደኛው ፣ በተሲያት ፣ መጣ ፣ እንዲሉ ። ሰዓትን ፣ እይ ።

ቶሰከ ፤ ሳይሰማ ፣ ተፈሳ ።

ቱስክ ፤ ድምፅ ፣ የለሽ ፣ ፈስ ።

ቱስኪያም ፤ ፈሳም ።

ቱስክ ፣ አለ ፤ ቶሰከ ።

አቶሰከ ፤ በቀስታ ፣ ፈሳ ።

ማቶሰክ ፤ መፍሳት ።

ተስከረከረ ፤—አደፈ ፤—ከረከረ ።

ተሸከረከረ ፤—ተንደረደረ ፤—ከረ ከረ ።

ተሻለ ፤—በለጠ ፤—ሻለ ።

ተሻማ ፤—ተናጠቀ ፤—(ጥማ) ሻማ ።

ተሸመለመለ ፤—ተሸበለለ ፤—መለ መለ ።

ተሳነ ፤—አቃተ ፤—(ሳነ) ።

ተስፋ ፤ (ሰፈወ) ፤ አለኝታ ፤ ወደ ፣ ፊት ፣ አገኛለኹ ፣ የማለት ፣ ጽኑ ፣ እምነት ።

ተስፋ ፤ ጢብኛ ፣ ስለ ፣ ሞቱ ፣ ሰዎች ፣ ለካ ሀናት ፣ የሚዘጋጅ ፣ ባዙቴ ።

ተስፋዬ ፤ የወንድና ፣ የሴት ፣ ስም ፤ የኔ ፣ ተስፋ ፣ ማለት ፣ ነው ። (በተስፋ) ፤ ባለኝታ ፤ በተ ስፋ ፣ እየኖረ ፣ ደጅ ፣ የሚጠና ። ባል ፣ ብለኽ ፣ ባለን ፣ ተመልከት ።

ተስፋ ፣ አደረገ ፤ ማማኘትን ፣ አመነ ።

ተስፋ ፣ ማርያም ፤ የሰውና ፣ የቀበሌ ፣ ስም ፤ በተጕለት ፣ ውስጥ ፣ ያለ ፣ አጥቢያ ።

ተስፋ ፣ ቈረጠ ፤ ተበሳጨ ፤ አላገኝም ፣ አለ ።

ተስፋ ፣ ሰጠ ፤ ይሰጥላል ፣ ታገኛለኽ ፣ አለ ።

ተሸቀነደረ ፤—ተቀናጣ ፤—ቀነደረ ።

(ተሰተሰ) ፤ አንተሰተሰ ፤ አነቃ ፣ ሠነጠቀ ፤ አስፈራ ።

ማንተሰተሰ ፤ ማንቃት ፣ መሠንጠቅ ፣ ማስ ፈራት ።

ተንተሰተሰ ፤ ነቃ ፣ ተሠነጠቀ ፤ ፈራ ።

ተሰተሰ ፤ ተስታሳ ፤ የተንተሰተሰ ፣ የሚ ንተሰተስ ፤ ፈሪ ።

ተሰተሰ ፣ አለ ፤ የፍራት ፣ ነገር ፣ ተናገረ ።

ቶሰቶሰ ፤ በድብቅ ፣ ሳያሰማ ፣ ፈሳ ። ቶሰ ከን ፣ እይ ።

ቶሰቶስ ፤ ቶስታሳ ፤ ፈሳም ፣ ፈሪ ፤ ነገር ፣ የማይችል ።

ቱስ ፣ አለ ፤ ተፈሳ ፤ በታች ፣ ተተነፈሰ ። ቱስ ፣ ያለ ፣ ዘረጥ ፣ ሳይል ፣ አይቀርም ፣ እንዲሉ ።

አቶሰቶሰ ፤ አቶከቶከ ፣ አሳበቀ ።

አቶስታሽ ፤ አሳባቂ ።

ተቸ ፤ (ሐተተ) ፤ ዐተተ ፣ የነገር ፣ ማስ ረጃ ፣ አመጣ ። (ተረት) ፤ ብዙ ፣ ቢተቹ ፣ ይሰለቹ ።

ተቺ ፣ (ዎች) ፤ የተቸ ፣ የሚተች ፤ ሐተ ተኛ ።

ተቺነት ፤ ተቺ ፣ መኾን ።

መተቸት ፤ ማተት ፣ ማስረዳት ።

መተቻ ፤ ማተቻ ፣ ማስረጃ ፣ ዐውድ ፣ ሽንጎ ።

አስተቸ ፤ አሳተተ ፣ ሐተታ ፣ አስነገረ ።

አስተቺ ፤ ያስተቸ ፣ የሚያስተች ።

ማስተቸት ፤ ማሳተት ።

ማስተቻ ፤ ማሳተቻ ።

ተተቸ ፤ ታተተ ፣ ተባለ ፣ ተነገረ ፣ ትቹ ።

ትች ፤ የተተቸ ፤ ከፈራጅ ፣ ሽማግሌ ፣ ከዳኛ ፣ አንደበት ፣ የሚወጣ ፣ የፍርድ ፣ የነገር ፣ ማስረጃ ። ሰው ፣ ፊት ፣ አይቶ ፣ ይፈርዳል ፤ እግዜር ፣ ግን ፣ ልብን ፣ ይመረምራል ። ሰው ፣ አየ ፤ እግዜር ፣ አየ ። እግዜር ፣ መንግሥትን ፣ ይጠብቅ ፤ ዐመፀኛን ፣ ያው ድቅ ፤ ሐሰተኛን ፣ ያርቅ ፤ ፍት ፣ ርት ፣ ይጠንቅቅ ፤ ማማለሻ ፣ ተቀብለው ፣ ፍርድ ፣ አድልተው ፣ በል ተው ፣ ጠጥተው ፣ ከብረው ፣ ብታያቸው ፣ አትቅና ባቸው ፣ እንደ ፣ ማለት ። የጠበቃ ፣ ትች ፣ ውርድ ፣ ይባላል ።

ትችት ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ መጨረሻው ፣ ት ፣ ምእላድ ፣ ነው ። ትች ፣ ቅጽልና ፣ ጥሬ ፤ ትችት ፣ ግን ፣ ጥሬ ፣ ብቻ ፣ ይኾናል ።

አተቻቸት ፤ አስተታተት ፤ መተቸት ።

ታቱ ፤ (ታሕቴ) ፤ ታቹ ፣ ሥሩ ። የቱ ፣ ዝርዝርነት ፣ አባትን ፣ ያያል ።

ታቱ ፡ ሥግራ ፡ አለ ፤ (ትግ ፡ ታተ) ፤ የልጅን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ መንገድን ፡ መራ ፤ መኼድን ፡ አስተማረ ። ዳግመኛም ፡ ታቱ ፡ (ተአቱ) ፡ ትገባለኽ ፡ ተብሎ ፡ ይተረጐማል ። አቱን ፡ አስተውል ።

ታታ ፤ (ተወተ) ፤ ትግ ፡ ተትዐ) ፤ ወን ፈትን ፡ መረብን ፡ ሠራ ፡ ዐልጋን ፡ ጠፈረ ፡ ጠለፈ ፡ አዋሰበ ፡ አያያዘ ፡ ፫ቱን ፡ ክር ፡ ወይም ፡ ገመድ ፡ ጐንጕን ። የተፈተለ ፡ ከኹለት ፤ የተታታ ፡ ከሦስት ፡ እንዲሉ ።

መታታት ፤ መጠፈር ፡ መጥለፍ ፡ ማዋሰብ ።

መታቻ ፤ መጠፈሪያ ፡ ማዋሰቢያ ።

አስታታ ፤ አስጠፈረ ፡ አስጠለፈ ።

ተታታ ፤ ተጠፈረ ፡ ተጠለፈ ፡ ተዋሰበ ፡ ተያያዘ ።

ትት ፤ (ቶታን) ፤ የተታታ ፤ ጥፍር ፡ ውስ ብስብ ፡ ጥልፍልፍ ፡ ቍልፍልፍ ፡ የስንደዶ ፡ የክር ፡ ገመድ ፤ ጠፍር ።



ትት ፡

ትት ፤ የወፍ ፡ ቤት ።

አንታታ ፤ በጠሰ ፤ ባለማቋረጥ ፡ ጥይት ፡ ተኰሰ ፡ አንጣጣ ።

ማንታታት ፤ መተኰስ ፡ ማንጣጣት ።

ታች ፤ (ታሕት) ፤ ተሐተ) ፤ ንኡስ ፡ አገ ባብ ፤ ጥግ ፡ ሥር ፡ ዝቅታ ፡ ግርጌ ። በና ፡ ከ ፡ ሲሰ ማሙት ፤ በታች ፡ ከታች ፡ ይላል ። (የሰው ፡ በታች) ፤ ሞኝ ፡ ወራዳ ። (የበታች ፡ በታች) ፤ መጨረሻ ፡ ታች ፤ ስፍራ ፡ ሞፍራ ።

ታቾች ፤ ጥጎች ፡ ሥሮች ፡ ግርጌዎች ።

ታቹ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ታች ፡ የሚል ።

ታች ፡ አለ ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ነዳ ፡ ቍል ቍል ፡ ወሰደ ።

ታች ፡ በላቸው ፤ ከብቶቹን ፡ ካፋፍ ፡ ወዳ ረቪ ፡ አውርዳቸው ።

ታች ፡ በላቸው ፤ ጠላቶቻችንን ፡ አዋርዳ ቸው ፤ እንተ ፡ የበላይ ፡ እነሱ ፡ የበታች ፡ ይኹኑ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ታች ፡ በሌ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ታች ፡ በል ። ታቹ ፡ የዚህ ፡ ከፈል ፡ ነው ።

ታች ፡ ቤት ፤ በታች ፡ ያለ ፡ ቤት ፤ በጉን ደር ፡ የበአታ ፡ አጥቢያ ፡ የሐዲስ ፡ መምህራን ፡ የነበሩበት ።

ታችኛ ፡ (ኞች) ፤ የታች ፡ የቈላ ፤ በታች ፡ የሚኖር ። ታችኛው ፡ ታችኛዋ ፡ ታኞዪቱ ፡ ታች ኞቹ ፡ እያለ ፡ ይዘረዝራል ።

ታችኞች ፤ ቈለኞች ፡ አጋንንት ፡ ጎጢኣ ተኞች ።

ታች ፡ ታቹን ፤ ጥግ ፡ ጥጉን ፡ ሥር ፡ ሥሩን ፡ ቈላ ፡ ቈላውን ።

(ቷቷ) ፤ **አንቷቷ** ፤ በጣጠሰ ። ታታን ፡ ተመልከት ።

ማንቷቷት ፤ መበጣጠስ ።

ተንቷቷ ፤ ተበጣጠሰ ።

ቷ ፡ አለ ፤ ጨ ፡ አለ ፤ ተበጠሰ ።

ቷ ፡ አለ ፤ ፈጥኖ ፡ ወጣ ፡ ፈሰሰ ፤ የሴት ፡ ደም ።

ቷ ፡ አለ ፤ ቦግ ፡ ቧ ፡ አለ ፤ ቶሎ ፡ በራ ።

መንቷቷት ፤ መበጣጠስ ።

ትቻ ፤ ዘጠነኛ ፡ የቀባርዋ ፡ ምት ።

ተተገ ፤ በክፋይ ፡ መታ ፡ ወጋ ፡ አቃጠለ ። ተገተገ ፡ አይ ።

ተታጊ ፡ (ዎች) ፤ የተተገ ፡ የሚተትግ ፤ ወጊ ፡ አቃጣይ ።

ትተጋ ፤ የአሳት ፡ ጨበጣ ፡ ውግ ።

መተተግ ፤ መውጋት ፡ ማቃጠል ።

መተተጊያ ፤ መውጊያ ፡ ማቃጠያ ።

አስተተገ ፤ አስመታ ፡ አስወጋ ።

ማስተተግ ፤ በትንታግ ፡ ማስወጋት ።

ተትጊ ፤ (ትግ) ፤ ፋደት ፡ ዐራጅ ፡ (ኢሳ ፴፬ ፡ ፲፩ ። ሶፎ፪ ፡ ፲፬) ።

ተተመከመከ ፤—ተድበሰበሰ ፤—ተመከ ።

ታተረ ፤ ተጋ ፡ ጣረ ፡ ለፋ ።

ታታሪ ፡ (ዎች) ፤ የታተረ ፡ የሚታትር ፤ ጣሪ ፡ ትጉህ ።

ታታሪነት ፤ ትጉህነት ።

መታተር ፤ መትጋት ፡ መጣር ፡ መልፋት ።

መታተሪያ ፤ መትጊያ ፡ መልፊያ ።

አታተረ ፤ አተጋ ፡ አለፋ ።

ማታተር ፤ ማትጋት ፡ ማልፋት ።

ቲቲቲ ፤ አውራ ፡ በግ ፡ ለማዋጋት ፡ አረኛ ፡ የሚያሰማው ፡ ድምፅ ።

ቲቲቲ ፡ አለ ፤ በጎችን ፡ ለውጊያ ፡ አዘዘ ፤ አተጣተመ ።

ቸ

ቸ ፤ ከተ ፡ የተዴቀለ ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ። ቸከለንና ፡ ቸኰለን ፡ ተመልከት ።

ቸ ፤ የጨ ፡ ወራሽ ። ጫጫታ ፡ ቻቻታ ።

ቸ ፤ የጎና ፡ የከ ፡ የጸና ፡ የቀ ፡ የጀ ፡ ተወራራሽ ። ጌር ፡ ቸር ፤ ከህለ ፡ ቻለ ፤ ጸፈቀ ፡ ቸፈገ ፤ ቃመ ፡ ቻመ ፤ ጀነነ ፡ ቸነነ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ።

ቹ ፤ የሩቅ ፡ ወንድ ፡ ዝርዝር ፡ በብዙዎች ፡ ስም ፡ ጫፍ ፡ የሚነገር ። በጎች ፡ በጎቹ ፤ ፍየሎች ፡ ፍየሎቹ ፤ የርሱ ፡ በጎች ፡ ፍየሎች ።

ቻ ፤ በስም ፡ መጨረሻ ፡ እየገባ ፡ ምእላድ ፡ ይኾናል ። ዳር ፡ ዳርቻ ፤ ዐፈር ፡ ዐፈርቻ ፤ ዐረም ፡ ዐራሙቻ ፤ ሥር ፡ ሥርቻ ፤ ጥል ፡ ጥላቻ ። ትርጓሜ ውም ፡ ዐይነትንና ፡ ኹኔታን ፡ ያሳያል ።

ቿ ፤ (ችዋ) ፤ የሩቅ ፡ ሴት ፡ ዝርዝር ። ቤቶች ፡ ቤቶቿ ፤ ላሞች ፡ ላሞቿ ፤ የርሷ ፡ ቤቶች ፡ ላሞች ።

ቼ ፤ (ችዬ) ፤ እኔ ፡ ለሚሉ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ባለቤትነትን ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ። ላሞች ፡ ላሞቼ ፤ ፈረሶች ፡ ፈረሶቼ ፤ የኔ ፡ ላሞች ፡ ፈረሶች ።

ቼ ፤ ፈረስን ፡ ለመከልከልና ፡ ለመንዳት ፡ ለመጋለብ ፡ የሚነገር ፡ ቃል ። ቼ ፡ ፈረሴ ፡ ቀና ፡ ገብሴ ፡ እንዲሉ ፡ ልጆች ።

ቼ ፡ በለው ፤ የከራር ፡ መቺ ፡ ዘፈን ፡ አዝማች ።

ቼ ፡ ቼ ፡ ቼ ፤ ሰንጋ ፡ ምት ፤ የፈረስ ፡ ምስጋና ፡ በማሲንቆ ። ና ፡ ቼ ፡ ቼ ፡ ቼ ፤ ና ፡ ቼ ፡ ቼ ፡ ቼ ። ከፈረሰኞች ፡ የምናውቃቸው ፡ በሻቸ ፡ አቦዬ ፡ ጎይሌ ፡ አንዳርጋቸው ። ቼቹን ፡ እይ ።

ች ፤—ስምን ፡ አብዢ ፤—ዎች ።

ች ፤ ለሩቅ ፡ ሴት ፡ የዘማችና ፡ የነባር ፡ አንቀጽ ፡ ዝርዝር ። በላች ፡ ጠጣች ፤ ኼደች ፡ መጣች ፤ ነች ። በግእዝ ፡ መሠረቱ ፡ ት ፡ ነው ።

ችቦ ፤—የጭራሮ ፡ መብራት ፤—ቸበቸበ ።

ችባሓ ፤ የዛፍ ፡ ስም ፤ እንደ ፡ ሾላ ፡ ያለ ፡ ዕንጨት ፡ ወተታም ።

ችባሓ ፤ በተጕለት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቀበሌ ፡ ችባሓ ፡ ያለበት ፡ የበቀለበት ። ችባሓ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንዲሉ ።

ችበችበ ፤ (ጨበጨበ) ፤ ጣለ ፡ መታ ፡ ደበደበ ፡ ወቃ ፡ እኽልን ፡ በለበቅ ።

ችበችበ ፤ እሳትን ፡ ባፈር ፡ በቅጠል ፡ አጠፋ ።

ችበችበ ፤ በርካሽ ፡ ሼጠ ።

ችበችበ ፤ ዐረደ ፡ ቈረጠ ።

ችብ ፡ አደረገ ፤ ጭብጠባ ፡ ገመረ ። ችብ ፡ አድርግ ፡ እንዲል ፡ ዘፋኝ ።

ችብ ፡ አደረገ ፤ በፍጥነት ፡ ሼጠ ፡ ለወጠ ።

ችብ ፡ ችብ ፡ አደረገ ፤ እጁን ፡ ጸፋ ፡ መላልሶ ፡ አጨበጨበ ።

ችብቻቢ ፤ የቸበቸበ ፡ የሚቸበችብ ፤ ወቂ ።

ችብችባ ፤ ውቂያ ፡ ጭብጠባ ።

ችብችቦ ፤ ራስ ፡ ካንጎት ፡ በላይ ፡ ያለ ። ዳሟት ፡ የጎልያድን ፡ ችብቸቦ ፡ በቈረጠ ፡ ጊዜ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ድል ፡ ኾነው ፡ ሸሹ ። ችብቸቦ ፡ ቀኝሮንና ፡ ቄንዳላንም ፡ ያስተረጕማል ።

ችብቸቦ ፤ የወረብና ፡ የቅኔ ፡ ጭብጠባ ፤ ከጭብጠባ ፡ ጋራ ፡ የሚባል ፡ ወረብ ።

መችብችብ ፤ መጣል ፡ መምታት ፡ መደብደብ ፡ መውቃት ፡ ማጨብጨብ ።

መችብችቢያ ፤ መምቻ ፡ መደብደቢያ ፡ መውቂያ ፡ በትር ፡ ሙጫ ።

ችባችበ ፤ ወቃቃ ፡ ደባደበ ።

መችባችብ ፤ መወቃቃት ።

አስችበችበ ፤ አስጣለ ፡ አስመታ ፡ አስደበደበ ፡ አስወቃ ።

አስችበችበ ፤ አሼጠ ፡ አስለወጠ ።

አስችበችበ ፤ አስጨበጨበ ።

አስችበችቢ ፤ አሳረደ ፡ አስቈረጠ ።

ማስችብችብ ፤ ማስመታት ፡ ማስወቃት ።

ተችበችበ ፤ ተጣለ ፡ ተመታ ፡ ተደበደበ ፡ ተወቃ ።

ተችበችበ ፤ ተሼጠ ፡ ተለወጠ ።

ተችበችበ ፤ ታረደ ፡ ተቈረጠ ።

ተችበችበ ፤ ተጨበጨበ ።

አንችበችበ ፤ ጠበሰ ፡ አበሰለ ፤ አቃጠለ ።

ማንችብችብ ፤ መጥበስ ፡ ማቃጠል ።

ማንችብችቢያ ፤ መጥበሻ ፡ ነዲድ ።

ተንችበችበ ፤ ተጠበሰ ፡ በሰለ ፤ ተቃጠለ ።

ችቦ ፤ የጭራሮ ፡ መብራት ፡ ዳቦት ፡ ቲሃ ።

መንችብችብ ፤ መጠበስ ፡ መቃጠል ።

መንችብችቢያ ፤ ምድጃ ፡ ፍም ።

አችባችብ ፤ አመታት ፡ አወቃቅ ፤ መችብ ችብ ።

ችግ ፤ በግን ፡ ለመከልከል ፡ የሚነገር ፡ ቃል ። ዘሩ ፡ ሸገገ ፡ ነው ።

ችማ ፡ **አለ** ፤ ከለከለ ፡ መለሰ ፡ በግን ።

ችግኝ ፤ (ተገነ) ፤ የሣር ፡ የቅጠል ፡ የዛፍ ፡ የተከል ፡ ፍል ፡ ከላይ ፡ በዳስ ፡ ከታች ፡ በጀጉል ፡ የሚተገን ። ጭቀኝንና ፡ ጭጉኝን ፡ ተመልከት ።

ችገረ ፤ ጠፋ ፡ ታጣ ፡ ጨነቀ ፡ ተሳነ ። (ተረት) ፤ የችገረው ፡ እርጉዝ ፡ ያገባል ፤ የባሰበት ፡ እመጣት ። ተገረን ፡ አስተውል ።

ችጋሪ ፤ የችገረ ፡ የሚችገር ፡ ልብስ ፡ ጕርሥ ።

ችግር ፤ ዕጦት ፡ የመፍቅድ ፡ ጥፋት ። አማረን ፡ አይ ።

ችግሬ ፤ የችግር ፤ መናኛ ፡ ሥራ ፡ ልብስ ፡ ጣራ ፤ ሥሥ ፡ የፈረንጅ ፡ ምላጭ ።

ችግረኛ ፡ (ኞች) ፤ የተችገረ ፡ ችግር ፡ የገባው ፡ የጸናበት ፡ ድኻ ።

ችግር ፡ አለው ፤ ጨነቀው ፡ ጠበበው ፤ የሚያደርገውን ፡ ዐጣ ።

ችጋር ፤ ራብ ፡ ጠኔ ፡ (ምሳኜ ፡ ፲ዩ) ።

ችጋረኛ ፡ (ኞች) ፤ ራብተኛ ፡ ቀጠና ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ይልሰው ፡ ይቀምሰው ፡ የሌለው ፡ (መዝ፱ ፤ ፲፰ ። ፲ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ። ፻፪ ፡ ፲፯ ። ኢሳ፴፪ ፡ ፯) ።

መችገር ፤ መጥፋት ፡ መታጣት ፡ መጭነቅ ።

አስችገረ ፤ አስጨነቀ ፡ አሳጣ ፡ አስራበ ።

አስችጋሪ ፡ (ሮች) ፤ ያስችገረ ፡ የሚያስችገር ፤ አስጨናቂ ፡ (፪ነገ ፡ ፪ ፡ ፲) ።

አስችጋሪነት ፤ አስጨናቂነት ።

ማስችገር ፤ ማስጨነቅ ፡ ማሳጣት ፡ ማስራብ ።

ማስችገሪያ ፤ ማስጨነቂያ ።

ተችገረ ፤ ተጨነቀ ፡ ተራበ ፡ ተጠማ ፡ ታረዘ ፤ ዐጣ ፡ ነጣ ፡ ደኸየ ፡ ገራ ፡ ገባው ፡ (ግብ ፡ ሐዋ፲ ፡ ፲፯ ። ያዕ፪ ፡ ፪) ።

ተችጋሪ ፤ የሚችገር ፤ ተጨናቂ ።

ችጉር ፤ የተችገረ ፤ ችጋረኛ ፡ ራብተኛ ፡ ዕርዝተኛ ።

(ጥቸ) **መችገር** ፤ መጨነቅ ፡ ማጣት ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ መታረዝ ።

መችገሪያ ፤ መጨነቂያ ።

ችግሮ ፤ ገዶ ፡ ጨንቆ ፡ ተስኖ ።

አይችግረው ፤ የሰውና ፡ የበሬ ፡ ስም ፤ አይገደው ፡ አይሳነው ።

ቢችግርሽ ፤ ባታውቂ ፡ ቢሳንሽ ፡ ቢጨን ቅሽ ፡ ባትችዪ ። ገረዘን ፡ እይ ።

አችጋገር ፤ አጨናነቅ ፤ መችገር ።

ችሃ ፤ ያገር ፡ የነገድ ፡ ስም ፤ ከኔ ፡ ቤት ፡ ጕራጌ ፡ አንዱ ፡ ችሃ ፡ ይባላል ።

ችው ፤ የሩቆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ዝር ዝር ። እሱ ፡ እነሱን ፡ ዐወቃቸው ፡ ወደዳቸው ። በጥሬም ፡ ሲገባ ፡ ቤታቸው ፡ ሥራቸው ፡ ይላል ።

ቻይ ፤—የሚችል ፤—ቻለ ።

ችከ ፤ (ስሕከ) ፤ አደፈ ፡ ለመመ ፡ ደገደገ ።

ችክ ፤ **ችኸ** ፤ የጥርስ ፡ አድፍ ፡ ልማም ፡ ስሓ ፡ ሳካ ።

ችክ ፤ የገብስ ፡ ስም ።

ችካም ፤ በጥርሱ ፡ ላይ ፡ ችክ ፡ ያለበት ፡ የበዛበት ።

ችክታ ፤ ያፍላ ፡ የውበት ፡ ተቃራኒ ፤ አለ ማማር ፤ የፊት ፡ መብረድ ፤ ችክ ፡ ማለት ።

ችክ ፡ አለ ፤ ሙዝዝ ፡ አለ ።

ችክ ፡ ምንችክ ፡ አለ ፤ ሞዘዘ ። መነቾ ከን ፡ እይ ።

ችኮ ፤ ሞዛዛ ፡ ሙዝኝ ፡ መንቻካ ።

ቼክ ፤ ልዩ ፡ ወረቀት ፡ ከባንክ ፡ ገንዘብ ፡ ማዘዣ ።

ችኹ ፤ የቅርቦች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የአንቀጽና ፡ የስም ፡ ዝርዝር ። እሱ ፡ እናንተን ፡ ዐወቃችኹ ፤ አጃችኹ ፡ እግራችኹ ።

ችከለ ፤ ተከለ ፡ ቀበቀበ ።

ችካይ ፤ የችከለ ፡ የሚችከል ፤ ቀብቃቢ ።

መችከል ፤ መትከል ፡ መቀብቀብ ።

መችኪያ ፤ መትኪያ ፡ መቀብቀቢያ ፡ ጋጣ ፡ ሜዳ ።

አስችከለ ፤ አስተከለ ፡ አስቀበቀበ ።

አስችካይ ፤ ያስችከለ ፡ የሚያስችከል ፤ አስቀብቃቢ ።

ማስችከል ፤ ማስተከል ፡ ማስቀብቀብ ።

ተችከለ ፤ ተተከለ ፡ ተቀበቀበ ፡ እመሬት ፡ ገባ ።

ችክል ፤ የተችከለ ፡ የተቀበቀበ ፤ ቅብቅብ ።

ችካል ፤ የንጨት ፡ የብረት ፡ ቅብቃብ ፡ (መሳኜ ፡ ፭፯) ።



ችካል ፡

ችካሎች ፤ ቅብቃቦች ፡ (ዘጉ፭ ፡ ፴፪) ።

አቻከለ ፤ አታከለ ፡ አቀባቀበ ።

ማቻከል ፤ ማታከል ፡ ማቀባቀብ ።

አቸካከል ፤ አቀባቀብ ፤ መቸከል ።

ቸኰለ ፤ ጠደፈ ፣ ፈጠነ ፣ በሥራ ፣ በነገር ። (ተረት) ፤ የቸኰለች ፣ አፍሳ ፣ ለቀመች ።

ቸኰል ፤ የሰው ፣ ስም ፤ ቶሎ ፣ ተወለደ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ቸኳይ ፣ (ዮች) ፤ የሚቸኵል ፤ ጠዳፊ ።

ችኵል ፣ (ሎች) ፤ የቸኰለ ፤ ጥዱፍ ፣ (መክፂ ፣ ፱ ። ፪ጢሞ ፣ ፫ ፣ ፬) ። የሽብ ፣ ችኵል ፣ ቀንድ ፣ ይነክሳል ፣ እንዲሉ ።

ችኵልነት ፤ ጥዱፍነት ።

ችኰላ ፤ ጥድፊያ ፣ ፍጥነት ፣ (ዘዳ፲፮ ፣ ፫ ። ገላ፮ ፣ ፭) ።

መቸኰል ፤ መጥደፍ ፣ መፍጠን ።

መቸኰያ ፤ መጥደፊያ ፣ መፍጠኛ ፣ ትዛዝ ።

አቸኰለ ፤ አፈጠነ ፣ ጉተጉተ ።

ማቸኰል ፤ ማፍጠን ፣ መጉትጉት ።

አስቸኰለ ፤ (አትከለ) ፤ አስጠደፈ ፣ አስጉተጉተ ፣ አስፈጠነ ።

አስቸኳይ ፣ (ዮች) ፤ ያስቸኰለ ፣ የሚያስቸኵል ፤ አስጠዳፊ ፣ አስጉትጓች ፣ (ዘፀ፭ ። ፮ ። ፲) ።

አስቸኳይነት ፤ አስጉትጓችነት ።

ማስቸኰል ፤ ማስጠደፍ ፣ ማስጉትጉት ።

ማስቸኰያ ፤ ማስጠደፊያ ፣ ማስጉትጉቻ ።

ተቸኰለ ፤ (እምከመ ፣ ጕጕአ) ፤ መን ገደኛው ፣ ተ(ከ) ቸኰለ ፣ ቶሎ ፣ ይቺድ ። ተ ፣ በከ ፣ ሞከሼነት ፣ የተነገረ ፣ ወቢይ ፣ አገባብ ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ የመደረግ ፣ ልማድ ፣ አለመኾኑን ፣ አስተውል ።

ተቻኰለ ፤ ተጣደፈ ፣ ተፋጠነ ፤ ተጕታ ጕተ ።

ተቻኳይ ፤ የሚቻኰል ፤ ተጣዳፊ ፣ ተፋጣኝ ።

መቻኰል ፤ መጣደፍ ፣ መፋጠን ።

መቻኰያ ፤ መጣደፊያ ፣ መፋጠኛ ።

አቻኰለ ፤ አጣደፈ ፣ አፋጠነ ፤ አጕታጕተ ፣ አዳፋ ።

አቻኳይ ፤ ያቻኰለ ፣ የሚያቻኵል ፤ አጣዳፊ ፣ አፋጣኝ ፣ አጕታጓች ።

ማቻኰል ፤ ማጣደፍ ፣ ማፋጠን ።

ማቻኰያ ፤ ማጣደፊያ ፣ ማፋጠኛ ።

አቸኳኰል ፤ አጠዳደፍ ፤ መቸኰል ። ተከለ ፣ የግእዝ ፤ ቸከለና ፣ ቸኰለ ፣ ያማርኛ ፣ ናቸው ።

ቺኮሮ ፤ የተክል ፣ ስም ፤ የባሕር ፣ አገር ፣ ተክል ።

ቸከቸከ ፤ ወጋ ፣ ነቀሰ ፣ ጠቀጠቀ ።

ቸከ ፤ ውግት ።

ቸከ ፣ አደረገ ፤ ጠቅ ፣ አደረገ ።

መቸክቸክ ፤ መንቀስ ፣ መጠቅጠቅ ።

አንቸከቸከ ፤ ሥጋን ፣ በቅቤ ፣ በዘይት ፣ ጠበሰ ። ተከተከ ፣ ብለሽ ፣ አንተከተከን ፣ እይ ።

አንቸከቸከ ፤ ሸነ ፣ አንፎከፎከ ።

ማንቸከቸከ ፤ መጥበስ ፣ መሸን ።

ማንቸከቸኪያ ፤ መጥበሻ ፣ ድስት ።

ተንቸከቸከ ፤ ተሸነ ፣ ተንፎከፎከ ።

ተንቸከቸከ ፤ ተጠበሰ ።

መንቸከቸከ ፤ መጠበስ ፣ መንፎከፎከ ።

መንቸከቸኪያ ፤ መጠበሻ ፣ መንፎከፎኪያ ።

አቸካቸከ ፤ አወጋግ ፤ መቸከቸከ ።

ቻለ ፤ (ከሀለ) ፤ ተሸከመ ፣ ወሰነ ፣ ያዘ ፣ አገመረ ፣ ጨረሰ ፣ ታገሠ ።

ቻይ ፤ (ከሃሊ) ፤ የቻለ ፣ የሚችል ፤ ተሸካሚ ፣ ወሳኝ ፣ ታጋሽ ፤ ልበ ፣ ሰፊ ፣ ነገር ፣ ዐላፊ ።

ቻይ ፤—ተክል ፤—ሻይ ።

ቻል ፤ (ከሀል) ፤ አትተው ፤ ሚስት ፣ አድርግ ። ልጃገረድን ፣ ለጠለፈና ፣ ለደፈረ ፣ ይነገራል ።

ቻል ፤ ዐሥረ ፣ ፈጅ ፣ ጋን ።

አይቻል ፤ ትልቅ ፣ ቶፋ ።

አይችሉኽ ፤ አይችሉሽ ፤ የወንድና ፣ የሴት ፣ ስም ።

መቻል ፤ መሸከም ፣ መወሰን ፣ መጨረስ ፣ መታገሥ ፣ (ጾሳሙ ፣ ፳፮ ፣ ፳፰) ።

መቻል ፤ የፈታውራሪ ፣ ሀብተ ፣ ጊዮርጊስ ፣ ፈረስ ፣ ስም ። ኣባን ፣ እይ ።

መቻያ ፤ መወሰኛ ፣ መታገሻ ።

መቻያ ፤ በባላገር ፣ ላይ ፣ የሚደረግ ፣ የወታደር ፣ ምሪት ፤ ወይም ፣ ሥራት ።

መቻያ ፤ ቅጣት ፣ መከራ ፣ ሥቃይ ፣ መቅሠፍት ፣ አደጋ ፣ (ሔኖ፲፩ ፣ ፴፱) ።

አስቻለ ፤ (አከሀለ) ፤ አሸከመ ፣ አስወሰነ ፣ አስታገሠ ። (ያስችልኽ) ፤ ትግሥት ፣ ይስጥኽ ። (አያስችለውም) ፤ አይታገሥም ።

አስቻለ ፤ ልጃገረድን ፣ በጠለፋት ፣ ሰው ፣ ሚስትነት ፣ እንድትኖር ፣ አስደረገ ።

አስቻለ ፤ በችሎት ፣ ተቀመጠ ፤ ከሳሽ ፣ ተከሳሽን ፣ አንጋገረ ፣ አቆሞት ፣ አነጣጠረ ፣ አከራከረ ፣ አበጣጠረ ።

አስቻይ ፤ ያስቻለ ፣ የሚያስችል ፤ አቆጋች ፣ አንጋጋሪ ፣ ዳኛ ።

ማስቻል ፤ ማሸከም ፣ ማስወሰን ፣ ማስጨረስ ፣ ማስታገሥ ።

ማስቻል ፤ ማነጋገር ፣ ማቆገት ።

ማስቻያ ፤ ማነጋገሪያ ፣ ማሳገቻ ፣ ስፍራ ፣ ጊዜ ።

ተቻለ ፤ (ተከሀለ) ፤ ተወሰነ ፣ ተጨረሰ ።

ተቻለ ፤ ተመቸ ፣ ጎነ ፣ ደላ ፣ ተደረገ ። ዛሬ ፣ አይቻለኝም ፤ በተቻለኝ ፣ ጊዜ ፣ እመጣለኹ ።

ተቻይ ፤ የሚቻል ።

(ጥቻ) መቻል ፤ መወሰን ፣ መጨረስ ።

ተቻቻለ ፤ (ተካሀለ) ፤ ተሸካከመ ፣ ተወሳሰን ፤ ተጣወረ ፣ ተጋገሠ ፣ (ኤፌ፬ ፣ ፪) ።

ተቻቻይ ፤ የሚቻቻል ፤ ተጣዋሪ ።

ተቻቻይ ፤ የቅኔ ፣ አገባብ ።

ተቻቻይነት ፤ ተቻቻይ ፣ መኾን ።

መቻቻል ፤ መሸካከም ፣ መወሳሰን ፣ መጣወር ።

መቻቻያ ፤ መወሳሰኛ ፣ መጣወሪያ ።

አቻቻለ ፤ (አስተካሀለ) ፤ አሸካከመ ፣ አወሳሰን ፣ አስተጋገሠ ።

አቻቻለ ፤ አጣጣ ፣ አማላ ፣ ዕዳን ።

አቻቻለ ፤ አጣወረ ፣ አካልን ፣ ሰውነትን ።

አቻቻይ ፤ ያቻቻለ ፣ የሚያቻችል ።

አቻቻይነት ፤ አቻቻይ ፣ መኾን ።

ማቻቻል ፤ ማወሳሰን ፣ ማጣወር ፣ ማሳላት ።

ማቻቻያ ፤ ማወሳሰኛ ፣ ማጣወሪያ ።

ችሎት ፤ (ከሂሎሁ) ፤ ታግሦት ።

ችሎት ፤ (ክሂሎት) ፤ ዳኝነት ፣ ሙግት ፣ ክርክር ። የዳኝነት ፣ ሥራ ፣ ብዙ ፣ ትዕግሥትና ፣ ዕውቀት ፣ ስለሚፈልግ ፣ ችሎት ፣ መቻል ፣ ተባለ ።

ችሎት ፤ ሥልጣን ፣ መብት ፣ (ዕዜና ፣ ፹፱ ፣ ፲፩ ። የሐ፲ ፣ ፲፰) ።

ችሎት ፤ ሸንጎ ፣ አደባባይ ፣ ዐውድ ።

ችሎቶች ፤ ሥልጣኖች ፣ መብቶች ።

ችሎተኛ ፣ (ኞች) ፤ በችሎት ፣ የሚቀመጥ ፣ ነገረተኛ ።

ችሎት ፣ ተመለሰ ፤ ዳኛ ፣ ተነሣ ፣ ጉባኤው ፣ ተበተነ ።

ችሎታ ፤ የሥራ ፣ ዕውቀት ። (ይቻላል) ፤ ይኾናል ፤ ይደረጋል ። (አይቻልም) ፤ አይኾንም ፤ አይደረግም ። (አልተቻለውም) ፤ አልተመቸውም ፤ አልደላውም ፤ ዕረፍት ፣ አላገኘም ።

አቻቻል ፤ አወሳሰን ፤ መቻል ።

ቸለለ ፤ (ጸለለ) ፤ ተወ ፤ ለገመ ። ተለለን ፣ ተመልከት ።

ቸል ፤ ቸለል ፤ መተው ፤ መጥመም ፣ መለገም ፤ ዝም ፣ ግለት ፣ (ዘዳ፴፩ ፣ ፮ ፣ ፰) ።

ቸል ፣ አለ ፤ ቸለል ፣ አለ ፤ ጠመመ ፣ ለገመ ፤ ዝም ፣ አለ ።

ቸልታ ፤ ቸል ፣ ግለት ፤ ጥመት ፣ ልግም ፣ ዝምታ ፣ (ኤርሚ፵ ፣ ፲) ።

ቸልተኛ ፣ (ኞች) ፤ ቸል ፣ የሚል ፣ (መዝ ፲፩ ፣ ፬ ። ምሳ፩ ፣ ፴፪ ። ፲ሮ ፣ ፲፭) ።

ቸልቻ ፤ ንኡስ ፣ አገባብ ፤ ና ። ብሉና ፣ ጠጡ ፤ ሙቱና ፣ ዕረፉ ።

ቸልቻ ፤ ቦዝ ፣ አንቀጽ ። ሰው ፣ ወርሶ ፣ ወይም ፣ ነግዶ ፣ ያድራል ።

ችላ ፤ ቸል ፣ ተወት ፤ ሀኬት ። (ከፉን ፣ ችላ) ፤ የውሻ ፣ ስም ።

ችላ ፤ አይቶ ፣ እንዳላዩ ፣ ሰምቶ ፣ እንዳልሰሙ ፣ መኾን ። መግዛት ፣ ቢያምርሽ ፣ ችላ ፤ ጥጋብ ፣ ቢያምርሽ ፣ ጠላ ፣ እንዲሉ ።

ችላ ፣ አለ ፤ ቸል ፣ አለ ፤ ተከየ ።

ችላ ፣ ባይ ፤ ችላ ፣ የሚል ፤ ቸልተኛ ፣ ሀኬተኛ ።

ቸለሰ ፤ ከነበለ ፣ ደፋ ፣ ገለበጠ ፣ ጨርሶ ፣ አፈሰሰ ፣ ብዙ ፣ ውሃን ፣ ደምን ።

ቸለሰ ፤ በቀንድ ፣ አስተኛ ፤ ማንቀሮትን ፣ ዐንገትን ፣ ወደ ፣ ላይ ፤ ማዥራትን ፣ ወደ ፣ ታች ፣ አደረገ ፤ ዘለሰ ፣ ለማረድ ።

ቸላሽ ፣ (ሾች) ፤ የቸለሰ ፣ የሚቸልስ ፤ አፍሳሽ ።

ችለሳ ፤ ከንበላ ፣ ግልበጣ ።

መቸለስ ፤ መከንበል ፣ መገልበጥ ፣ ማፍሰስ ።

መቸለሻ ፤ ማፍሰሻ ፣ ዐቦሬ ፣ ገበቴ ፣ መሬት ።

አስቸለሰ ፤ አስከነበለ ፣ አስገለበጠ ፣ አስፈሰሰ ።

ማስቸለስ ፤ ማስከንበል ፣ ማስፈሰስ ።

ተቸለሰ ፤ ተከነበለ ፣ ተገለበጠ ፣ ተደፋ ፣ ፈሰሰ ።

ተቸለሰ ፤ በማዥራት ፣ ተኛ ፤ ተዘለሰ ።

ቸላሳ ፤ ችልስ ፤ የተቸለሰ ፣ የፈሰሰ ፤ ከንቧል ፣ ዝልስ ።

ችልስ ፣ አደረገ ፤ ድፍት ፣ አደረገ ፤ ቸለሰ ።

ችልስ ፣ አለ ፤ ግልብጥ ፣ አለ ፤ ተቸለሰ ።

ችልስ ፣ ችልስ ፣ አለ ፤ ፍስስ ፣ ፍስስ ፣ አለ ።

አቻለሰ ፤ አከናበለ ፣ አጻፋ ፣ አፋሰሰ ።

አቻላሽ ፤ ያቻለሰ ፣ የሚያቻልስ ፤ አፋሳሽ ።

ማቻለስ ፤ ማጻፋት ፣ ማፋሰስ ።

አቸላለስ ፤ አከነባበል ፤ መቸለስ ።

(ቸለቸለ) ፤ ተለተለ) ፤ አንቸለቸለ ፤ በፍጥነት ፣ አነበበ ፣ አንበለበለ ።

ማንችልችል ፤ ማንበብ ፡ ማንበልበል ።
ቻመ ፤ ቃመ ። ቸፈረን ፡ እይ ።
መቻም ፤ መቃም ።
መቻሚያ ፤ መቃሚያ ።
አቻመ ፤ አቃመ ።
ማቻም ፤ ማቃም ።
አስቻመ ፤ አስቃመ ።
ማስቻም ፤ ማስቃም ።
አቻቻም ፤ አታቃም ፤ መቻም ።
ቶሜ ፤ ጐረጐማ ።
ችመችመ ፤ (ተመተመ) ፤ ደመደመ ፡ ቸረችመ ፡ አጠረሰ ፡ አስተካከለ ።
ችመችመ ፤ አብዝቶ ፡ ሠራ ፡ ዘራ ፡ ቤትን ፡ እኽልን ፤ አቆመ ፡ ጦርን ።
ችምቻሚ ፤ የችመችመ ፡ የሚችመችም ፤ አብዣ ።
አስችመችመ ፤ አስቸረችመ ፡ አስጠረሰ ።
አስችመችመ ፤ አስበዛ ።
ተችመችመ ፤ ተቸረችመ ፡ ጠረሰ ፡ ተደመደመ ።
ተችመችመ ፤ ተሠራ ፡ ተዘራ ፤ ቆመ ፡ በዛ ።
ችምቻማ ፤ ቸርቻማ ፡ ደምዳማ ።
ችምችም ፤ የተችመችመ ፤ ችርችም ፡ ስለት ፤ መንደር ፡ ብዙ ፡ ጦር ።
ችምችም ፡ ለፎ ፤ ዘንጋዳ ፡ አበቃቀሉ ፡ ብዛት ፡ ያለው ።
ችምችም ፡ ለፎ ፤ ብዙ ፡ ሰራዊት ። ለፎን ፡ ተመልከት ።
ችምችም ፡ አለ ፤ በዝቶ ፡ ታየ ።
ችምችም ፡ ያለ ፤ ጭፍቅ ፡ ችፍግ ፡ ያለ ።
ችምችሞ ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ምግብ ።
አችማችም ፤ አችረችም ፤ መችምችም ።
ቺን ፤—ያገር ፡ የነገድ ፡ ስም ፤—ሺን ።
ችን ፤ እኛ ፡ የሚሉ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የአንቀጽና ፡ የጥሬ ፡ ዝርዝር ። እሷ ፤ እኛን ፡ ዐወቀችን ፤ ዐይናችን ፡ ጐሯችን ።
(ችነቧ) ፤ ሐመግ) ፤ **አችነቧ** ፤ ረገጠ ፡ መታ ።
አችናቧ ፤ አጣታ ፡ አንቦጫረቀ ፡ ውሃን ፡ በእግሩ ።
አችናቧ ፤ አጨናፈረ ፡ ገላን ።
ማችናቧት ፤ ማማታት ፡ ማንቦጫረቅ ።
ችንቧ ፡ ችንቧ ፡ አለ ፤ ቡጭርቅ ፡ ቡጭርቅ ፡ አለ ።

ችነከረ ፤ (ነከረ ፡ ተከለ) ፤ ሰመረ ፤ በችንካር ፡ ከንጨት ፡ ጋራ ፡ ወጋ ፡ መታ ፡ አያያዘ ፡ አጣበቀ ፡ አገናኘ ፡ አጠነከረ ።
ችንካሪ ፤ የችነከረ ፡ የሚችነከር ።
ችንከራ ፤ የመችንከር ፡ ሥራ ።
ችንካር ፡ (ሮች) ፤ አራት ፡ ማእዘን ፡ ያለው ፡ የዱሮ ፡ ምስማር ፡ ልብ ፡ ውጋት ፤ በቁመትም ፡ በውፍረትም ፡ ከዛሬው ፡ ይበልጣል ፤ በማእዝ ፡ ቀኖት ፡ ይባላል ፡ (ኢሳ፳፪ ፡ ፳፭) ።



ችንካር ፡

ችንካር ፤ ከደንጊያ ፡ የሚገኝ ፡ ማዕድን ፡ ሙጫ ፡ መጣብቅ ፡ የተሠራውን ፡ የተሰበረውን ፡ የንሐስና ፡ የመዳብ ፡ የብር ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ጥቂት ፡ ክብረ ፡ ሰማይ ፡ ተጨምሮበት ፡ ማያያዣ ፡ ማጎኛ ።
ችንካር ፤ ሳንቃን ፡ ከሳንቃ ፡ የሚያገናኝ ፡ ውሳጣዊ ፡ የንጨት ፡ ቅርቃር ፡ ሰፊና ፡ ቀጪን ፡ (ዘፀ፳፮ ፡ ፲፯) ።
መችንከር ፤ መሰመር ፡ መውጋት ፡ መምታት ፡ ማያያዝ ፡ ማጣበቅ ።
መችንከሪያ ፤ መሰመሪያ ፡ መውጊያ ፡ መምቻ ፡ ማጣበቂያ ፡ ችንካር ፡ መዶሻ ።
አስችነከረ ፤ አስመታ ፡ አስወጋ ፡ በምስማር ።
አስችንካሪ ፤ ያስችነከረ ፡ የሚያስችነከር ።
ማስችንከር ፤ ችንካር ፡ ማስመታት ።
ተችነከረ ፤ ተሰመረ ፡ ተወጋ ፡ ተመታ ፡ ተጣበቀ ፡ (መክ፲፪ ፡ ፲፩) ።
ችንከር ፤ የተችነከረ ፡ የተወጋ ፡ የተጣበቀ ፡ ዕንጨት ፡ ብረት ፤ የጌታችን ፡ እጅና ፡ እግር ።
(ጥች) **መችንከር** ፤ መወጋት ፡ መጣበቅ ።
መችንከሪያ ፤ መወጊያ ፡ መጣበቂያ ።
አችናከረ ፤ ችንካርን ፡ ልብ ፡ ውጋትን ፡ አማታ ፡ አታከለ ።
ማችናከር ፤ ማማታት ፡ ማታከል ።
አችነካከር ፤ አወጋግ ፤ መችንከር ።
ችንማ ፤ ከርሳስ ፡ የተበጀ ፡ የገበጣ ፡ ጠጠር ።
ችነነ ፤ ጀነነ ፡ አኰራ ፡ ቄነነ ፡ አጓደደ ።
ችነነ ፤ ወነጎ ፡ ወሰጠ ።

ቸናኝ ፤ የቸነነ ፣ የሚቸንን ፤ ጀናኝ ፣ ቈናኝ ።

መቸነን ፤ መጀነን ፣ መቈነን ።

አስቸነነ ፤ አስጀነነ ፣ አስኰራ ፣ አስቈነነ ።

ማስቸነን ፤ ማስጀነን ፣ ማስቈነን ።

ተቸነኔ ፤ ተጀነነ ፣ ኰራ ፣ ተቈነነ ፣ ተጓደደ ።

ተቸነነ ፤ ተወነጎ ፣ ተወሰጠ ።

ተቸናኘ ፤ የሚቸነን ፤ ተጀናኘ ፣ ተጓዳጅ ።

ቸነኔ ፤ ቸናና ፤ ችንን ፤ የተቸነነ ፤ ጅነን ፣ ኵሩ ፣ ቊንን ፤ የተወነገ ፣ ውንግ ።

አቸናነን ፤ አጀናነን ፤ መቸነን ።

ቸነፈር ፤ (ነፈረ) ፤ የበሽታ ፣ ስም ፤ ዕል ቂት ፣ መቅሠፍት ፤ ከጦርነት ፣ በኋላ ፣ የሚመጣ ፣ ሰውን ፣ እያጨናፈረ ፣ ፈጥኖ ፣ የሚገድል ፣ ዕመም ፤ በግእዝ ፣ ብድብድ ፣ ይባላል ። ዐባር ፣ ቸነፈር ፣ እንዲሉ ፣ (ዕንፎ ፣ ፭ ። ማቴ፳፬ ፣ ፯) ።

ቸንች ፤ ድድ ፤ የድድ ፣ መሥመር ።

ቸንቻም ፣ (ሞች) ፤ ድዳም ፤ ቸንቹ ፣ ያፈጠጠ ።

ችንች ፤ ሽንቶ ፣ ሽንክ ፣ ነጭ ፣ አባ ፣ ጨንፈ ፣ ከመከር ፣ በኋላ ፣ የእንቡስንና ፣ የትለምን ፣ ዛፍ ፣ ቅጠል ፣ ከታች ፣ እስከ ፣ ላይ ፣ በልቶ ፣ የሚፈርስ ።

ችፌ ፤—ቊስል ፤—ቸፈቸፈ ።

ቸፈገ ፤ (ጸፈቀ) ፤ ጨፈቀ ፣ ጠቀጠቀ ፣ አቀራረበ ፤ አበዛ ፣ ጅብ ፣ አደረገ ።

ተቸፈገ ፤ ተጨፈቀ ፣ ተጠቀጠቀ ።

ችፍግ ፤ (ጸፉቅ) ፤ የተቸፈገ ፤ ጭፍቅ ፣ ጥቅጥቅ ፣ ዱር ፣ (መዝ፤ ፱ ። ኤር፬ ፣ ፮ ። ሕዝ፤፱ ፣ ፤፩) ።

ችፍግነት ፤ ጥቅጥቅነት ፣ (ኢሳ፤ ፵፩ ። ሕዝ፤፩ ፣ ፫) ።

ችፍግ ፣ አለ ፤ (ተጸፍቀ) ፤ ጥቅጥቅ ፣ አለ ፤ ደን ፣ ዎግ ፣ ኾነ ።

ቸፈነነ ፤ (ቸነነ) ፤ ጀነነ ፣ አኰራ ።

ተቸፈነነ ፤ ተጀነነ ፣ ኰራ ፤ ቸል ፣ አለ ፣ ትዛዝን ።

ቸፈረ ፤ (ሰፈረ) ፤ ቃመ ፣ ባፍ ፣ መላ ።

ቸፋሪ ፤ የቸፈረ ፣ የሚቸፍር ፤ ቃሚ ።

መቸፈር ፤ መቃም ።

መቸፈሪያ ፤ አፍ ፣ ዐውድማ ፣ መቃሚያ ።

አስቸፈረ ፤ አስቃመ ።

ማስቸፈር ፤ ማስቃም ።

አቸፋፈር ፤ አቃቃም ፤ መቸፈር ።

ችፍርግ ፤ (ቸፈገ) ፤ ቁመተ ፣ ዐጪር ፣ ዐጽቀ ፣ ብዙ ፣ ዕንጨት ፣ ችፍግ ፤ ር ፣ ስሯጽ ፣ ነው ።

ቸፈቸፈ ፤ (ተፈተፈ) ፤ ጨቀጨቀ ፤ ጨፈጨፈ ፣ ሸፈሸፈ ።

ቸፈቸፈ ፤ አዠ ፣ አካፋ ።

ቸፍቻፊ ፤ (ተፍታፊ) ፤ የቸፈቸፈ ፣ የሚቸፈችፍ ፤ ጨቅጫቂ ፣ ጨፍጫፊ ።

ቸፈቸፍ ፤ ጨፈጨፍ ።

ቸፍቻፋ ፤ ጨቅጫቃ ፣ ነገረኛ ።

ችፍ ፤ ሐሩር ፣ ረቂቅ ፣ ዕከክ ።

ችፌ ፤ (ችፋዊ) ፤ የቊስል ፣ ስም ፤ ዅል ፣ ጊዜ ፣ የሚያዥ ፣ የጨፈጨፍ ፣ ዐይነት ፣ ቊስል ፣ ዐልፎ ፣ ዐልፎ ፣ ሽፍ ፣ የሚል ፣ (ዘዳ፳፰ ፣ ፳፯ ። ዘሌ፲፬ ፣ ፶፭) ። መድኀኒቱም ፣ የተወቀጠ ፣ ኮሶ ፣ በማር ፣ ለውሶ ፣ መቀባትና ፣ ቅጠል ፣ ለጥፎ ፣ በጨርቅ ፣ ማሰር ፣ ነው ።

ችፍ ፣ አለ ፤ እዥ ፣ አሳየ ፤ ሸፈፈ ።

ችፍ ፣ ችፍ ፣ አለ ፤ ጭፍጭፍ ፣ ከፍክፍኮ አለ ፤ በረቂቅ ፣ ዘነመ ።

ችፍችፍ ፤ ጭቅጭቅ ፣ ንዝንዝ ።

ችፍችፋም ፤ ጭቅጭቃም ፣ ንዝንዛም ።

ተቸፋቸፈ ፤ ተጨቃጨቀ ፣ ተነዛነዘ ።

መቸፋቸፍ ፤ መጨቃጨቅ ፣ መነዛነዝ ።

መቸፋቸፊያ ፤ መጨቃጨቂያ ።

አቸፋቸፈ ፤ አጨቃጨቀ ፣ አነዛነዘ ።

ማቸፋቸፍ ፤ ማጨቃጨቅ ፣ ማነዛነዝ ።

አቸፋቸፍ ፤ አጨቃጨቅ ፤ መቸፍቸፍ ።

ቸረ ፤ ቼረ ፤ (ጎየረ ፣ ጌረወ) ፤ ሰጠ ፣ ናኘ ፣ ለገሰ ።

ቸር ፤ ቼር ፤ (ጌር) ፤ ደግ ፣ ጸድቅ ፣ ሰው ፤ ሰጪ ፣ ለጋስ ፣ አባ ፣ መስጠት ፣ እጅ ፣ ሰፊ ፣ ለነገ ፣ የማይል ፤ ለድኻ ፣ ቁርሶ ፣ ያጐርሣል ፤ ቀዶ ፣ ያለ ብላል ፣ (ዮሐ፮ ፣ ፲፱ ። ፲ ፣ ፲፩) ።

ቸር ፤ በጎ ፣ ደኅና ። ቸር ፣ ያውልኽ ፣ ቸር ፣ ያሳድርኽ ፣ ቸር ፣ ያሰማኽ ፣ እንዲሉ ።

ቸሮች ፤ (ጌራን) ፤ ሰጪዎች ፣ ለጋሶች ፣ ደጎች ፣ ሰዎች ፣ ጸድቃን ።

ቸሩ ፤ ደጉ ፣ ለጋሱ ፣ ዶልዲሌ ፣ ሳይሰሙ ኑት ፣ ዝናምን ፣ ለዘር ፣ ጠልን ፣ ለመከር ፣ የሚሰጥ ፣ መጋቤ ፣ ዓለማት ። ስለ ፣ ቸሩ ፣ እግዚሐር ፣ እንዲል ፣ ተማሪ ።

ቸሪቱ ፤ ቸሪት ፤ ደጊቱ ፣ ደጊት ።

ቸሬ ፤ የሰው ፣ ስም ፤ የኔ ፣ ቸር ፣ ማለት ፣ ነው ።

ቸሬ ፤ ቸሬ ፣ የሚባል ፣ ሰው ፣ ካ፲፱፻፩፰ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በፊት ፣ ባዲስ ፣ አበባ ፣ ይሠራው ፣ የነበረ ፣ ጥይት ፣ ክልስ ።

ቸርነት ፤ (ኀርውና) ፤ ቸር ፥ መኾን ፤ ለጋስነት ፥ (ልሳሙ ፥ ጽ ፥ ፲፩ ፡ ሉቃ፮ ፥ ፵፩ ፡ ፪ቆሮ ፥ ፮ ፥ ፮) ፡፡

ቸርነት ፤ የሰው ፥ ስም ፡፡

ቸር ፥ አገር ፤ የቸር ፥ አገር ፤ ግነት ፥ መንግሥተ ፥ ሰማይ ፥ ደግ ፥ አገር ፡፡

ቸር ፥ አገር ፥ ኼደ ፤ ሞተ ፤ ነፍሱ ፥ ወደ ፥ ሰማይ ፥ ዐረገች ፡፡

መቸር ፤ መስጠት ፥ መናኘት ፥ መለገስ ፡፡

መቸሪያ ፤ ስፍራ ፥ ጊዜ ፡፡

አቸረ ፤ (አኄረመ) ፤ ቸር ፥ አደረገ ፡፡

አስቸረ ፤ አሰጠ ፥ አስናኘ ፥ አስለገሰ ፡፡

ማስቸር ፤ ማሰጠት ፥ ማስለገስ ፡፡

ችሮታ ፤ (ኀሩት) ፤ አገኘዋለኹ ፥ ይመለስ ልኛል ፥ የማይባል ፥ ስጦታ ፥ ቸርነት ፡፡ (ሲፈራ ፥ ሲቸር) ፤ ልስጥ ፥ አልስጥ ፥ ላድርግ ፥ አላድርግ ፥ ልምታ ፥ አልምታ ፥ እያለ ፥ የሞት ፥ ሞቴን ፡፡

ተቻቻረ ፤ ችሮታን ፥ ተቀባበለ ፡፡

(ጥር) ቸር ፤—መር ፤—ቸረረ ፡፡

ችርንችር ፤ አራት ፥ ማእዘን ፥ ያለው ፥ ዕንጨት ፥ በትረ ፥ ሙሴ ፡፡

(ቸረፈፈ) ፤ ተረፈፈ) ፤ አንቸረፈፈ ፤ አስኰረፈ ፥ በተገብርነትም ፥ ይፈታል ፡፡

አንችርፍ ፤ ያንቸረፈፈ ፥ የተንቸረፈፈ ፥ ያኰረፈ ፡፡

ማንቸርፈፍ ፤ ማስኰረፍ ፡፡

ተንቸረፈፈ ፤ አኰረፈ ፥ አልናገር ፥ አለ ፡፡

ቸረፈፍ ፤ ቸርፋፋ ፤ የተንቸረፈፈ ፥ የሚንቸረፈፍ ፤ አሰራፊ ፥ አንችርፍ ፡፡

መንቸርፈፍ ፤ ማሰረፍ ፥ ኩፍ ፥ ማለት ፡፡

(ቸረረ) ፤ ሰሪር ፥ ሰረረ ፡፡ ትግ ፥ ጠረረ) ፤ አንቻረረ ፤ አንሻረረ ፥ አዘለለ ፡፡

አንቻሮ ፤ በወሎ ፥ ከፍል ፥ ያለ ፥ አገር ፤ አዘልሎ ፥ ግለት ፥ ነው ፡፡

ማንቻረር ፤ ማዘለል ፡፡

ተንቻረረ ፤ ተንሻረረ ፥ ተንሻለለ ፥ ዘለለ ፡፡

መንቻረር ፤ መንሻረር ፥ መዝለል ፡፡

መንቻረሪያ ፤ መዝለያ ፥ ፈፋ ፥ ጉድባ ፡፡

(ጥር) ቸር ፤ መር ፡፡

ቸር ፥ አለ ፤ መር ፥ አለ ፥ እባቡ ፥ ነብሩ ፡፡

ቸረቸመ ፤ ሰበረ ፥ ሸረፈ ፥ ዐጠፈ ፥ አጠረሰ ፥ ሰለት ፥ አሳጣ ፡፡

ቸርቻሚ ፤ የቸረቸመ ፥ የሚቸረችም ፤ ሸራፊ ፥ አጥራሽ ፡፡

መቸርቸም ፤ መሰበር ፥ መሸረፍ ፥ ማጥረስ ፥ ማጠፍ ፡፡

መቸርቸሚያ ፤ ድንጋይ ፥ ብረት ፡፡

አስቸረቸመ ፤ አሰበረ ፥ አሸረፈ ፥ አሰጠረሰ ፥ አሳጠፈ ፡፡

ማስቸርቸም ፤ ማሰበር ፥ ማስጠረስ ፡፡

ተቸረቸመ ፤ ተሰበረ ፥ ተሸረፈ ፥ ጠረሰ ፥ ታጠፈ ፡፡

ቸርቻማ ፤ ሰባራ ፥ ሸራፋ ፡፡

ችርችም ፤ የተቸረቸመ ፤ ስብር ፥ ሽርፍ ፡፡

ችርችም ፥ አለ ፤ ጥርስ ፥ አለ ፡፡

አቸራቸም ፤ አሰባበር ፤ መቸርቸም ፡፡

ቸረቸፈ ፤ ቸረቸመ ፡፡

ተቸረቸፈ ፤ ተቸረቸመ ፡፡ ፈ ፥ የመ ፥ ለውጥ ፥ ነው ፡፡

ቸረቸረ ፥ (ተረተረ) ፤ ፈታ ፥ በተነ ፥ ተነተነ ፥ ዘረዘረ ፤ በጥቂት ፥ በጥቂቱ ፥ ሼጠ ፥ ዕቃን ፥ ከመደብር ፥ ገዝቶ ፥ በሚዳ ፥ ተቀምጠ ፡፡ ዘሩ ፥ ቸረረ ፥ ነው ፡፡

ቸርቻሪ ፥ (ሮች) ፤ የቸረቸረ ፥ የሚቸረችር ፤ በታኝ ፥ ተንታኝ ፥ ዘርዛሪ ፥ ከመደብር ፥ ውጭ ፥ ሸያጭ ፡፡

ቸርቻሪነት ፤ ቸርቻሪ ፥ መኾን ፡፡

ችርቸራ ፤ መቸርቸር ፡፡

ችርቻሪ ፤ ችርቻሮ ፤ ዝርዘራ ፥ ብተና ፥ ትንተና ፤ የብትን ፥ የትንትን ፥ ዕቃ ፥ አሻሻጥ ፡፡

መቸርቸር ፤ መበተን ፥ መተንተን ፥ መሼጥ ፡፡

መቸርቸሪያ ፤ መበተኛ ፥ መተንተኛ ፥ መሼጫ ፥ መደብ ፥ ተራ ፡፡

አቸረቸረ ፤ (ቸረረ) ፤ ላይ ፥ ላዩን ፥ ዐለፈ ፥ ተንደረደረ ፥ ሳይወጋ ፤ የጦር ፥ ያንካሴ ፡፡

አቸርቻሪ ፤ ያቸረቸረ ፥ የሚያቸረችር ፡፡

ማቸርቸር ፤ መሳት ፥ ማለፍ ፥ መንደርደር ፡፡

ማቸርቸሪያ ፤ የነብር ፥ የጐርት ፥ የሌላም ፥ አውሬ ፥ ዝርባ ፡፡

አስቸረቸረ ፤ አስበተን ፥ አስተንተን ፥ አዘረዘረ ፤ በጅርዝር ፥ አሼጠ ፡፡

አስቸርቻሪ ፤ ያስቸረቸረ ፥ የሚያስቸረችር ፡፡

ማስቸርቸር ፤ ማስበተን ፥ ማስተንተን ፥ ማዘርዘር ፥ ማሼጥ ፡፡

ማስቸርቸሪያ ፤ ጊዜ ፥ ገበያ ፡፡

ተቸረቸረ ፤ ተበተነ ፥ ተተነተነ ፥ ተዘረዘረ ፥ ተሼጠ ፡፡

አቸራቸረ ፤ አተናተነ ፥ አዘራዘረ ፤ በችርቻሮ ፥ አሻሻጠ ፡፡

አቸራቻሪ ፤ ያቸራቸረ ፥ የሚያቸራችር ፤ አሻሻጭ ፡፡

ማቸራቸር ፤ ማባተን ፣ ማተናተን ፣ ማሻሻጥ ።

አቸራቸር ፤ አተናተን ፤ መቸርቸር ።

ቸሰረ ፤ ረፈቀ ፣ ደነሰረ ።

ቸሳሪ ፤ የቸሰረ ፣ የሚቸስር ፤ ደንሳሪ ።

ችሰራ ፤ ድንሰራ ።

መቸሰር ፤ መረፈቅ ፣ መደንሰር ።

መቸሰሪያ ፤ መረፈቂያ ፣ መደንሰሪያ ።

አስቸሰረ ፤ አስረፈቀ ፣ አስደነሰረ ።

ማስቸሰር ፤ ማስደንሰር ።

ተቸሰረ ፤ ተረፈቀ ፣ ተደነሰረ ።

ቸሳራ ፤ **ችስር** ፤ የተቸሰረ ፣ ደንሳራ ፣ ድንስር ።

ችስር ፣ አለ ፤ ድንስር ፣ አለ ፤ ተቸሰረ ።

አቸሳሰር ፤ አደነሳሰር ፤ መቸሰር ።

(ቸሰቸሰ) ፤ **አንቸሰቸሰ** ፤ አጨሰ ፣ ዐረፋና ፣ እንፋሎት ፣ እወጣ ።

ተንቸሰቸሰ ፤ ጨሰ ፣ ተነሣ ፣ ላበቱ ፤ ወጣ ፣ ዐረፋው ።

ቸሰቸስ ፤ **ቸስቻሳ** ፤ የተንቸሰቸሰ ፣ የሚንቸሰቸስ ፤ ርጥበት ፣ ያለው ፣ ዕንጨት ።

ችስቸስ ፣ አለ ፤ አጉበጉበ ።

ችስ ፣ አለ ፤ ፍም ፣ ወይም ፣ ትኩስ ፣ ቁሎ ፣ ውሃ ፣ በገባበት ፣ ጊዜ ፣ የጪስ ፣ የላበት ፣ ድምፅ ፣ አሰማ ።

ችስችሳ ፤ የቁላ ፣ የበረሓ ፣ ጉንዳን ፣ ምሥጥ ፣ በል ፣ ሺሾ ።

(ቻቻ) ፤ **ጫጫ)** ፤ **አንቻቻ** ፤ አንጫጫ ፣ አስጮኽ ።

ማንቻቻት ፤ ማንጫጫት ።

ማንቻቻ ፤ ማንጫጫ ።

ተንቻቻ ፤ ተንጫጫ ፣ ጮኸ ።

ቻቻታ ፤ ጫጫታ ፣ የጉባኤ ፣ ጩኸቴ ።

ቻቻቼ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ ጫጫቴ ።

መንቻቻት ፤ መንጫጫት ፣ መጮኽ ።

መንቻቻ ፤ መንጫጫ ፣ መጮኺያ ። ጨና ፣ ች ፣ ተወራራሽ ፣ መኸናቸውን ፣ ልብ ፣ እድርግ ።

ቻች ፤ **(ተሐተ)** ፤ ታናሽ ፣ ጥዋ ፣ የመንቀል ፣ ዐይነት ። መስቴን ፣ ቡዪትን ፣ ቡግሪትን ፣ ተመልከት ።

ቼቼ ፤ ማዘል ፣ እንቡቡ ፤ በታች ፣ መኾን ።

ቼቼ ፣ አለ ፤ ዐዘለ ፣ በዣርባ ፣ ተሸከመ ። ቼን ፣ ተመልከት ።

ቸቸረ ፤ ገፈረ ፣ ቃመ ።

ቸቻሪ ፤ የቸቸረ ፣ የሚቸቸር ፤ ገፋሪ ፣ ቃሚ ።

ችቸራ ፤ የመቸቸር ፣ ኹኔታ ።

መቸቸር ፤ መገፈር ፣ መቃም ።

መቸቸሪያ ፤ መገፈሪያ ፣ መቃሚያ ፣ አፍ ፣ ግርግም ።

አስቸቸረ ፤ አስገፈረ ፣ አስቃመ ።

ማስቸቸር ፤ ማስገፈር ፣ ማስቃም ።

ተቸቸረ ፤ ተገፈረ ፣ ተቃመ ።

ችችር ፤ የተቸቸረ ፣ የተቃመ ፣ በጉንጭ ፣ ውስጥ ፣ ያለ ፣ ጥሬ ።

ቻቻታ ፤—ጫጫታ ፤—(ቻቻ) ።

ቻቻቼ ፤—ጫጫቴ ፤—(ቻቻ) ።

ጰ

ጰ ፤ የበ ፣ ዲቃላ ፤ በግእዝ ፣ አልፍ ፣ ቤት ፣ በአበገደ ፣ ተራ ፣ ቍጥር ፣ ጽፅኛ ፣ ፊደል ። ጰን ፣ ጽፅኛ ፣ ማለት ፣ ከታች ፣ የጠን ፣ ፱ኛነት ፣ ለጎ ፣ የቀን ፣ ፲፱ኛነት ፣ ለጸ ፣ ሰጥቶ ፣ በማፈጋፈግ ፣ መኾኑን ፣ አስተውል ። በፊደልነት ፣ ስሙ ፣ ጰይት ፤ አኃዝ ፣ ሲኾን ፣ ጰ—፸፤ ይባላል ።

ጰ ፤ በበና ፣ በጥ ፣ ፈንታ ፣ ይነገራል ፤ የኹሉ ቱም ፣ ተወራራሽ ፣ ነው ። መዝገበ ፣ ፊደል ፣ ተመልከት ።

ጰጉሜ ፤ የወር ፣ ስም ፤ ፲፫ኛ ፣ ወር ፣ ተረፈ ፣ ዓመት ፣ በነሐሴ ፣ መጨረሻ ፣ በ፫ ፣ ዓመት ፣ ፭ ፣ ፭ ፤ ባራተኛ ፣ ዓመት ፣ ግን ፣ ፮ ፣ ቀን ፣ ይኾናል ። ትርጓሜውም ፣ ጭማሪ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ጰውሎስ ፤ የሰው ፣ ስም ፤ አስቀድሞ ፣ መምህረ ፣ አሪት ፣ የነበረ ፣ ኋላም ፣ መምህረ ፣ ወንጌል ፣ የኾነ ፤ ቍጥሩ ፣ ከአርደአት ፣ ሲኾን ፣ ማዕርጉ ፣ እንደ ፣ ጴጥሮስ ፣ ነው ፤ ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ ያገራችን ፣ ሰዎች ፣ ጴጥሮስ ፣ ጰውሎስ ፣ የሐዋርያት ፣ አለቆች ፣ ይሏቸዋል ።

ጴጥሮስ ፤ ካ፲፪ቱ ፣ ሐዋርያት ፣ አንዱ ፤ አለቃቸው ፣ ጌታ ፣ ከትንሣኤ ፣ በኋላ ፣ በጎቼን ፣ ጠብቅ ፣ ብሎ ፣ በቤተ ፣ ክሲያን ፣ ላይ ፣ የሾመው ። ጴጥሮስ ፣ ኩሎሐዊ ፣ አለቃዊ ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ይላሉ ፤ ኩሎሕ ፣ የተባለም ፣ ክርስቶስ ፣ ነው ።

ጴጥሮስ ፣ ጰውሎስ ፤ የታቦት ፣ ስም ፤ በጴ


ጥሮስና ፣ በጳውሎስ ፣ ስም ፣ የተቀረጸ ፣ ጽላት ፤ ይኸ ውም ፣ በሐምሌ ፣ ፭ ፣ ቀን ፣ በያመቱ ፣ ይነግሣል ።

ጳይት ፤ የፊደል ፣ ስም ፣ ጳ ፤ ቤት ፣ ማለት ፣ ነው ።

ጳኩሚስ ፤ በምንዙስና ፣ ለአንጦንስ ፣ ፫ኛ ፣ ለመቃርስ ፣ ፪ኛ ፣ የኾነ ፣ ጻድቅ ።

ጲላጦስ ፤ በጌታችን ፣ ጊዜ ፣ ኢየሩሳሌምን ፣ ይገዛ ፣ የነበረ ፣ የሮማ ፣ መስፍን ።

ጳልቃን ፤ የርኩምና ፣ የመረቡ ፣ ወይነት ፣ አሞራ ፣ ባንገቱ ፣ ሥር ፣ ሥጋ ፣ መያዣ ፣ ከረጢት ፣ ያለው ፤ የውዳሴ ፣ ማሪያም ፣ ተርጓሞች ፣ ያዳምን ፣ መከራ ፣ የተቀበለ ፣ የጌታችን ፣ ምሳሌ ፣ ያደርጉታል ። ፊደን



ጳልቃን ፣

ጆችም ፣ ፔሊካን ፣ ይሉታል ፤ የጥርስ ፣ ሐኪም ፣ መሣሪያም ፣ በርሱ ፣ ስም ፣ ይጠራል ።

ጳንጤን ፤ ያገር ፣ ስም ።

ጳንጤናዊ ፤ የጳንጤን ፣ ተወላጅ ፣ ጲላጦስ ።

ጳንጠቄስጤ ፤ ከትንሣኤ ፣ እስከ ፣ ጰራቅሊጦስ ፣ ያለው ፣ ወምሳ ፣ ቀን ።

ጰራቅሊጦስ ፤ የመንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅጽል ፤ (መጽንዒ ፣ መንጽሒ) ፣ የሚያጸና ፣ የሚያነጻ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ጰራቅሊጦስ ፤ አማላጅ ፣ አስታራቂ ፣ (፩ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፩)

ጵጵ ፤ የክንፈር ፣ ድምጥ ።

ጳጳስ ፣ (ሶች) ፤ ቁስ ፣ ካህን ፣ የሚሠልስ ፣ የሚቀድስ ፣ (ቲቶ፩ ፯ ። ፩ጢሞ ፫ ፣ ፭) ። ጳጳስን ፣ (ፓፓስን) ፣ ቁስ ፣ ማለት ፣ በጽርእ ፣ ነው ።

ጳጳስ ፤ የቤተ ፣ ክሲያን ፣ አባት ፣ ማዕርጉ ፣ ከሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ በታች ፣ ከኤጲስቆጶስ ፣ በላይ ፣ የኾነ ፣ አቡን ።

ጳጳስ ፣ ኤጲስቆጶስ ፤ የጠቅላይና ፣ ያውራጃ ፣ ግዛት ፣ አቡኖች ፣ የሃይማኖት ፣ አባቶች ።

ጵጵስና ፤ ጳጳስ ፣ መኾን ።

ጳጳስነት ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ። ጵጵስና ፣ የግእዝ ፤ ጳጳስነት ፣ ያማርኛ ፣ ነው ።

ጵጳሳ ፤ ዝኒ ፣ ዓዲ ፣ ከማሁ ።

አጳጳሰ ፤ ጳጳስ ፣ አደረገ ፣ ሾመ ።

አጳጳሸ ፤ ያጳጳሰ ፣ የሚያጳጵስ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ።

ማጳጳስ ፤ ጵጵስና ፣ መስጠት ።

ተጳጳሰ ፤ ጳጳስ ፣ ኾነ ፣ ተሾመ ።

መጳጳስ ፤ ጳጳስ ፣ መኾን ።

አጳጳጳስ ፤ በአንብሮተ ፣ እድ ፣ መሾም ፣ ማጳጳስ ።

ፐ

ፐ ፤ የጳ ፣ ዲቃላ ፤ በግእዝ ፣ አልፍ ፣ ቤት ፣ በአበገደ ፣ ተራ ፣ ቍጥር ፣ ፭ኛ ፣ ፊደል ። በፊደልነት ፣ ስሙ ፣ ፒ ፤ በአንዝነት ፣ ፐ—ጅያ ፣ ይባላል ።

ፐ ፤ የፈ ፣ ድርብ ፤ ጳ ፣ በበ ፣ ፈንታ ፣ እንዲነገር ፣ ፐም ፣ በፈ ፣ ፈንታ ፣ ይነገራል ። መዝገበ ፣ ፊደል ፣ አስተውል ።

ፐ ፤ የበ ፣ ወራሽ ። ካባ—ካፐ ።

ፒ ፤ የፊደል ፣ ስም ፣ ፐ ፤ ፈ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ፔንሙ ፤ ፭ኛው ፣ ያጋንንት ፣ አለቃ ።

ፓሪስ ፤ ባውሮጳ ፣ ውስጥ ፣ ያለች ፣ የፈረንሳዮች ፣ ዋና ፣ ከተማ ።

ፓሪስ ፤ በሐሜር ፣ ታሪክ ፣ የተጻፈ ፣ የጢሮአዳ ፣ ንጉሥ ፣ ልጅ ።

ፓሻ ፤ የማዕርግ ፣ ስም ፤ አበ ፣ ጋዝ ፣ አዝማች ፤ ፓሻ ፣ ቱርክኛ ፣ ነው ። ባሻን ፣ እይ ።

ፓሲፊክ ፤ በእስያና ፣ ባሜሪካ ፣ መካከል ፣ ያለ ፣ ውቅያኖስ ፤ ስፋቱ ፣ ዐሥር ፣ ሺ ፣ ማይል ፣ (መቶ ፣ ስሳ ፣ ሺ ፣ ዘጠኝ ፣ መቶ ፣ ኪሎ ፣ ሜትር) ፣ ነው ። ፓሲፊክ ፣ ሰላማዊ ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ይላሉ ።

ፓስታ ፤ **(ቦስጣ)** ፤ ደብዳቤ ፣ ዥሉ ፣ የሚገባበትና ፣ የሚወጣበት ፣ የሚታደልበት ፣ ስፍራ ፣ ቦታ ፤ ወይም ፣ ርሱ ፣ ራሱ ፣ ደብዳቤው ። ፓስታ ፣ ቤት ፣ እንዲሉ ።

ፓፓ ፤ የሮማ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፤ ጳጳስ ፣ አባት ፣ ማለት ፣ ነው ።

ፓፓያ ፤ የተክል ፣ ስም ፤ ፍሬው ፣ እንስተኛ ፣ እንኮላ ፣ የሚያኽል ፣ ጣፋጭ ፣ ተክል ፤ የተገኘውም ፣ ባፍሪቃ ፣ አገር ፣ ነው ፣ ይባላል ።

ተፈጸመ ።

አነሣሥቶ ፣ ላገሥመረን ፣ አዝምሮ ፣ ላስፈጸመን ፣ እግዚአብሔር ፣ ክብር ፣ ምስጋና ፣ ይግባው ፤ በውነት ፣ እንበለ ፣ ሐሰት ።

የዋና ፡ ዋና ፡ ግድፈትና ፡ ስሕተት ፡ ማረሚያ ።

ገጽ ፡	ዐምድ ፡	መሥመር ፡	ግድፈትና ፡ ስሕተት ፡	የታረመ ፡
፴፩	—	፬	ተደራራጊ ፡	ተደራጊ ፡
»	—	፯	መስማን ፡	መሰማን ፡
፵	፩	፲፩	ዋማምት ፡	ዋጣምት ፡
፵፱	፪	፵፱	ፈጸየ ፡	ፈደየ ፡
፶፯	—	፵፫	የለሌው ፡	የሌለው ፡
፻፴፭	፩	፲፫	ጐረደማኞች ፡	ጐረደማኖች ፡
፻፵፯	፩	፳፱	የታጋጠመ ፡	የተጋጠመ ፡
፻፶፯	፪	፳፱	ሐኖ ፡	ሔኖ ፡
፻፷፱	፪	፲፮	ሠነተፈ ፡	ሠነተረ ፡
፻፸፫	፩	፳፯	ብጫ ፡	ብጣ ፡
፻፹፯	፩	፵፱	ቲቱ ፡	ቂቱ ፡
፻፻፱	፪	፲፯	ማጭ ፡	ማጭድ ፡
፻፻፳፱	፩	፲፫	ገብርዬኣ ፡	ገብርዬ ፡
»	»	፲፱	በ ፡	ቢኣቸው ፡
፻፻፵፩	፩	፫	መረከካስ ፡	መረካከስ ፡
፻፻፶፱	፪	፵፭	ግልግል ፡	ግልገል ፡
፻፻፷	፩	፩	ከሣርር ፡	ከሣር ፡
፫፻፩	፪	፳፯	ማከሡ ፡	ከማሡ ፡
፫፻፯	፪	፲፫	ከለለው ፡ ሰውረው ፡	ከለለው ፡ ሰወረው ፡
፫፻፲፩	—	አርእስት ፡	(ገርጣዋ) ፡	ገርጣዋ ፡
፫፻፲፯	፪	፳	በትግሪኛ ፡ ጉውሽ ፡ ይባላል ፡	አታንብብ ፡
፫፻፶፩	፪	፵፩	የተንዶሸዶሽ ፡	የተንዶሸዶሸ ፡
፫፻፶፱	፪	፵፱	ሚዳ ፡	ሚዳ ፡
፭፻፳	፩	፳፯	ካዚህም ፡	ከዚህም ፡
፭፻፳፫	፩	፵፯	አባል ፡	አባለ ፡
፭፻፶፩	፩	፵፪	ጻዕራዊ ፡	ጻዕራዊ ፡
፮፻፭	፩	፵፭	ትንሽሽ ፡	ትንንሽ ፡
፮፻፳፫	፪	፵፯	አፋፈቀ ፡	አፋፋቀ ፡
፯፻፳	፩	፵፪	ሙዘቀኛ ፡	ሙዚቀኛ ፡
፲፻፲፯	፩	፵፫	ቁሾች ፡	ቁሶች ፡
፲፻፻፪	፪	፲	ከባባ ፡	ካበባ ፡
፲፻፻፵፫	፩	፲፱	ሸኒ ፡	ሸኚ ፡

Welcome to the very last page of this book, the largest book in our web library!! I trust it has been a real help to your Amharic language skills!!

And there is something else very special about this book. If you promise not to tell another person, I will let you in on the secret! Ok?

Well, here it is. My wife. Although born in the State of Florida, she got to Texas as soon as she could. And, she has taken good care of me now, for 61 years. She has given me five daughters and one son. She is not only an excellent flute player and flute teacher, but to top it all off ---

SHE SCANNED THE LAST NINE PAGES OF THIS BOOK, JUST FOR YOU AND ME!!!

So -- here's to Betty Ross Lapsley!!! HIP!! HIP!! HOORAY!!

BRL 8/3/13